ነበር። እንዴት ሊሆን ቻለ? ፊኛዋ ስለሞላ ለምርምር ጊዜ አልሰጣትም። ፍንጥር ብላ ከመኝታዋ ተነስታ ሽንት ቤት ገባች። ሆዷን የቁርጠት ስሜት ተሰማት ተጸዳድታ ተነሳች። የወር አበባዋ መጥቶ በማየቷ ደስ ብሏት ውሃውን ለቀቀችበት። ፒ! ብሎ ቀይ አረፋ ደፍቆ እየሳቀባት ወደ ውስጥ ወደዋሻው እየተልጉመጉመ ገባ።

ስልኳ ከመኝታ ቤት አሁንም ተንቃጨለ። ዘላ ያዘችው ሃሎ! አሁንም የሕፃን ድምፅ ሰማች ደግማ ሃሎ አለች ሳታውቀው ተቆጥታ።

«እድለኛ ነኝ አገኘሁሽ» ከማዶ የአንዲት የሴት ድምፅ።

«የምን እድል ነው ከየት ነው?»

«ከአሜሪካ ሎሳንጀለስ እኔ ቤቲ እህትሽ ነኝ።»

«ውይ አፈር በሆንኩት እውነት አንቺ ነሽ ቤቲ?»

«ገና ከእንቅልፌ ስለተነሳሁ የሕፃን ድምፅ ሰምቼ ግራ ተጋባሁ።»

«ነኝ ደስታዬን በወለድኩት ልጅ ድምፅ ልገልጽልሽ ፈልጌ ነው መጀመሪያ የሱን ለቅሶ ድምፅ ያቀረብኩልሽ።»

«እልልል! እንኳን ማርያም ማረችሽ መቼ ወለድሽ?»

«አምስት ቀን አለፈ ብደውል ብደውል ላገኝሽ አልቻልኩም። አዲሳባ ደውዬ እማዬም አባዬም ሰምተው ተደስተዋል። ጤናማ ወንድ ልጅ ነው ሲያምር ባየሽው»

«ይገርምሻል ቤቲ! አሁን በሕልሜ ልጅ ስገላገል ነበር ያየሁት ወይ ታምር። የኔን አጥፍቶ ላንቺ መስጠት እንኳን ደስ ያለሽ ቤትዬ ማርያም በሽልም ታውጣሽ» ብላ ስልኩን ዘጋችው። የበሯ ደወል ተሰማ። ክላውዝ የርጉዝ ልብስና እቅፍ አበባ ይዞላት መጣ።






# ክፍል አሥራ አንድ

የፀሐይ ብርሃን ተፈንጥቆ እንደባትሪ ብርሃን አይሞቅም። ባለፉት ሁለት ወራት አረንጓዴ መልክ የነበራቸው ዛፎችና ልዩ ልዩ ተክሎች መልካቸው ተለውጦ በጭጩዋል።

ጥቅር አፈር፣ አረንጓዴ ሣር በየተክሎቹ ሥርቻ ጨርሶ አይታይም። አንድ ላይ ተደራርበው የወደቁ ቢጫ የዛፍ ቅጠሎች ተከምረዋል። አረንጓዴ ቅጠል ያጡ ዛፎች በእሳት የተለበለበ ጭራሮ፣ ለደመራ ቃጠሎ የቀረቡ ግንዶች መስለዋል።

የዓመቱ ወቅት ይሄን መልክ ይዞ በልግ ከገባ ቆይቷል። የዛሬው እለት ነፋሻማ ሆኖ አየሩ በመቀዝቀዙ ትንሽ ይበርዳል።

የየቤቱ የሙቀት መስጫ ሂተር በዚህ ብርዳማ ወቅት መከፈት ጀምራል። ሁለት ፍቅረኞች ባሉበት አካባቢ ግን ሁኔታው ተረስቷል። ፋጡማና ጆኒ አብረው ተቃቅፈው ተኝተዋል። የጆኒ ቤት የቤት ማሞቂያ ሂተር እስካሁን አልተከፈተም። የሁለቱ የፍቅር ወላፈን በአካባቢው ስለሰፈነ የውስጡ ብርድ የደጁ ቅዝቃዜ ጨርሶ አልተሰማቸውም። የፍቅር አውድማ በሰፈነበት አካባቢ ምን ጊዜም ደስ የሚል የሙቀት ስሜት ስላለ አይበርድም።

ባለፈው ጊዜ ታጥበው የፀዱት የጆኒ ልብሶች ደርቀው ሊተኮሱ ፎቴው ላይ ተከምረዋል። ሳሎኑ እንደወትሮው አልፀዳም። ማድቤቱ (ኪችኑ) ውስጥ ያልታጠቡ ብዙ ቁሳቁሶች እንዳሉ አሉ። የመታጠቢያው ክፈል ገንዳ መልኩን እንደ ወቅቱ በልግ አበጭጮ ተለውጧል። ወለሉም ቢሆን ጨቅይቷል። በአጠቃላይ የአንድ ሰነፍ ወንደላጤ ቤት መስሏል።

ፋጡማ ያደረችው ከእሱ ጋር በመሆኑ ለሊቱን የሰላም እንቅልፍ አላገኘችም። እሱም እንደሷ ሰውነቱ ደካክሟል። እስከ እረፋዱ ሰዓት ድረስ ተቃቅፈው ሳይበርዳቸው ተኝተዋል።

ከማዶ የኮሪደር መተላለፊያ አካባቢ የቤቱ ስልክ ተደውሎ ተንቃጨለ። ጆኒ በቅድሚያ ከመኝታው ባኖ ተነሳ። ፋጡማ በጆኒ መራቅ ደንግጣ ተወራጨች። ከእንቅልፏ ነቅታ የስልኩን ሹክሹክታ አዳምጣ ተመልሳ ተጋደመች። ጆኒ የደወለችለትን ሴት በትህትና አናግሮ ተመልሶ ፋጡማን ሳይነካ ተጠቅልሎ ፊቱን አዙሮ ተኛ። ፋጡማ በሁኔታው ተገርማ የጆኒን የዞረ ጀርባ ገላምጣ በስልክ ከሴት ጋር ያደረገውን ሹክሹክታ አዳምጣ፤ ቀናች። ሰውነቷ የሚያደርገውን አጥቶ ተቅበጠበጠ። አከላቷን በቅናት ሞቆ የጋለ ሰውነቷን በቀዝቃዛ ሻወር ሳታበርደው፣ ቢላ ጨብጣ ጆኒን ሳታርደው፣ እልኋን በቀና መንገድ በሴትነት ሙያዋ ቁና ቁና እየተነፈሰች ተወጣችው። ቤቱን ጠቅላላ ሙልጭ አድርጋ አጽድታ የተከመሩትን ልብሶች አንድ በአንድ መተኮስ ጀመረች።

ክፍሉ የወንደላጤነት ጠረኑን እየለቀቀ ሄዶ ሴት የዋለችበት የትዳር መአዛ አገኘ። በጋለው ካውያ የጆኒን ነጭ ሸሚዝ እየተኮሰች አጥፋ እየዳመጠች የሀገሯን ዘፈን ማንጐራጐር ጀመረች።

ጆኒ በድምጿ ቃና ካሸለበበት መኝታ ነቅቶ አዳመጣት። በእርግጥ ቃናው ልብ ይነካል። ትራሱን አመቻችቶ በጀርባው ተንጋሎ ዜማውን አዳምጦ እሱም እንደሷ አብሮ ዘፈነ። ድምጹ ባያምርም በእንጉርጉሮው ፋጡማ ደስ አላት።

የሚጠጣ ነገር እንድትሰጠው ተለማምጦ ጠየቃት። ፋጡማ የጋለ ካውያውን ወዲያ ትታ ብርጭቆ ወተት ሞልታ ሰጠችው። ወተቱን በቀኝ እጁ ተቀብሎ በግራ እጁ የፋጡማን እጅ ጨብጦ እመኝታው ላይ ጐተታት። ወተቱ መሬት ወድቆ ተደፋ። ፋጡማ ደረቱ ላይ ወደቀች። እቅፍ አድርጐ ሳማት። ፋጡማ እየተፈራገጠች አልሳምም ብላ አስቸገረች። በመሃል የጋለው ካውያ ነጭ ሸሚዙን አቃጥሎ ክፍሉ በጭስ ተሞላ።

ሁለቱም ደንግጠው ከመኝታቸው ዘለው ተነሱ። ተቃጥሎ ሊነድ የተቃረበውን ሸሚዝ ጠቅልለው ባኞ ገንዳ ውስጥ ጥለው ቀዝቃዛ ውሃ ለቀቁበት። ፋጡማ ካውያውን ያለቦታው ትታ በመሄዷ አዘነች። ጆኒ በሸሚዙ መቃጠል አልተቆጣም። ይልቁንስ በጊዜ ተነስታ ያከናወነችውን የጽዳት ሥራና የልብስ መተኮሷን ጅማሬ አይቶ ተደሰተ።



የሴትነት ወግና ሙያውን በመያዝዋ ከልብ አመስግኖ አደነቃት። «የኔ ብትሆኚ» ብሎ ለትዳር ተመኛት።

ፋጡማ የክፍሉን መስኮቶች ከፋፍታ አናፈሰችው። ከውጪ የገባው ቀዝቃዛ አየር ክፍሉን እንጂ የልቧን የቅናት ጭስ አራግቦ አላቀዘቀዘውም። ፋጡማ የነገሩን ሁኔታ በደንብ ሳትረዳ ጆኒ ከሆነ ሴት ጋር ባወራ ቁጥር በቶሎ ትቀናለች። ቅድም ለጆኒ የደወለችለት ሴት ወዳጁ ሳትሆን በወር ሁለት ጊዜ እየመጣች ቤቱን የምታፀዳለት ሠራተኛ ነበረች። ሰላምታ ተለዋውጠው «ዛሬ ከእንግዳ ጋር ነኝ ነገ ከሰዓት በኋላ ገደማ እንድትመጪ አደራ» ብሎ ብቻ ስልኩን ስለዘጋው ነበር የቀናችው። ጆኒ ግን አሁን የቤቱን ጽዳት ተመልክቶ ሠራተኛዋ በከንቱ እንዳትደክም መልሶ በመደወል ሲነግራት ፋጡማ ሰምታ ቅናቷ ከንቱ መሆኑን አወቀች። እራሷን በራሷ ታዝባ ሁኔታው እንዳይታወቅባት ጆኒን እቅፍ አድርጋ ሳመችው። በተቃጠለውም ሸሚዝ ይቅርታ ጠይቃ ካሣውን እከፍልሃለሁ ብላ እጁን ጐትታ መኝታ ክፍል አገባችው።

ስልኩ ቅናት ያለበት ይመስል ባልተፈለገበት ወቅት ተደውሎ አባረቀ። እጫጉላው ክፍል ያሉት ፍቅረኞች ጩኸቱን ሰምተው ጆሮ ዳባ ብለው ተውት።

የደወለችው ሮዚ ነበረች። ባለፈው ጊዜ የሙሽሮች ሹፌር ሆና ለበዓሉ ድምቀት እንደሰጠች የሚያትት ዜና ከነፎቶግራፏ በትልቁ ጋዜጣ ላይ መውጣቱን ልትነግረው ፈልጋ ነበር። ልጃቸውን የዳሩት የትራፊክ መገናኛ ሴናተር የሮዚን እጅ ጨብጠው ከሙሽሮቹ ጋር በጋዜጣ·በመውጣታቸው «ዘረኛ ያልሆኑ ተራማጅ» ተብለው ጥሩ ዝናን አተረፉ። ሮዚም በዚሁ ጋዜጣ በአበሻ ቀሚስ ሞድ አምራ በመታየቷ ብዙ የሞድና የማስታወቂያ ድርጅቶች ለሥራቸው ለውጥ ቅንብር ተመኟት።

ፋጡማና ጆኒ ሰፊው አልጋ ላይ ተጋድመው ሁለቱም የድሮ የፍቅር ታሪካቸውን ሳይደባበቁ ትዝታቸውን ቀስቅሰው እየሰለቁ አብረው ይጨዋወታሉ።

ጆኒ ብሬመን እንደገባ የመጀመሪያ ፍቅረኛው ጀርመናዊት ነበረች። እድሜዋ ወደ 28 ገደማ የሚጠጋ ቆንጆ ባለትዳር። በትርፍ ጊዜዋ የሕዝብ ከፍተኛ ት/ቤት (Volkshochschule) ተቀጥራ የጀርመንኛ ቋንቋ

ታስተምራለች። ታሪኩ አሳዛኝ ቢሆንም ስለቆየ ጆኒ ስሜቱን እንብዛም አልረበሸውም። ግን ለአዲስ ፍቅረኛው ለፋጡማ ይህንን አሮጌ ታሪክ መንገሩን አልፈለገም ነበር። ፋጡማ ግን «ካልነገርከኝ ሞቼ እገኛለሁ ብላ ወጥራ ያዘችው። ጆኒ ታሪኩን ባጭር ባጭሩ ሊነግራት ወሰነ። አጠገቡ ጉድሎ የተቀመጠውን ውሃ ተጎነጨ። ትራሱን አመቻችቶ ድምጹ እንዲሰማለት ማጅራትና ጀርባውን አስደገፈ። ዓይኖቹ ጣራው ላይ ተተከሉ። የፋጡማ ጆሮዎች ታሪኩን ለመስማት ጓጉተው ወደላይ አቀነቀኑ።

«ይሄውልሽ ፋጡማ ይቺን ሴት ያወቅኋት ጀርመን በገባሁ በሰባተኛው ወር ገደማ ነበር ሬናት (Renate) ትባላለች። ያኔ የምኖረው መንግሥት የተከራየልኝ አንድ የሆነ ሆቴል ውስጥ ነበር። ቋንቋ ለመማር አመልክቼ እንዳጋጣሚ እሷ የምታስተምርበት ክፍል ደረሰኝ። ሬናት ባለትዳር የደስ ደስ ያላት ቆንጆዬ ናት። በሳምንት ሦስት ጊዜ በቀን ሁለት ሰዓት ነበር ትምህርቱ በክፍል ውስጥ ያለነው ከልዩ ልዩ ሀገሮች የመጣን በእድሜም በጾታም የተለያየን በአጠቃላይ አሥር ወይም አሥራ ሁለት ብንሆን ነው። ሬናት ውበቷ የትምህርት አሰጣጧ በጣም ደስ ስለሚል ሁላችንም ወደድናት። እሷ ግን አላውቅም እንዳጋጣሚ ጥሎባት እኔን ብቻ ወዳ ሙዝዝ አትልልሽም። ለነገሩ በክፍል ውስጥ ያለሁት አንድ ጥቁር እኔ ብቻ ነበርኩና ምናልባት ቀለሜ ማርኳት የሆን ብዬ ገመትኩ። የትምህርቱ ክፍለ ጊዜያት አልቆ ስንበታተን እኔን ለይታ ጠርታ የሆነ ነገር እንደሚያስረዳ እክፍል ውስጥ ታቆየኛለች።

ተማሪዎቹ ተበታትነው ሲያልቁ «ቆይ ላድርስህ» ብላ በመኪናዋ የሆነ ቦታ ትወስደኛለች። ቡና ጋብዛ ሆቴሌ ታደርሰኛለች።

ፋጡማ የጆኒን ንግግር አቋርጣ ብስጭት ባለ የቅናት ስሜት «እንዴ! ባለትዳር ሆና ይሄን በግልጽ ለማድረግ እንዴት ደፈረች?» ብላ ሲጋራዋን ለኮሰች። ጆኒ ነቅነቅም አላለ ትዝታ ባሕር ውስጥ ሳያስበው ገብቷል። ዓይኖቹ አሁንም እጣራው ላይ እንዳሉ ናቸው። የሩቁን ትዝታ ፊልም ከኮርኒሱ ላይ የሚያዩ ይመስላሉ። «ፍቅር ነዋ ሌላ ምን ትይዋለሽ? የሰመመን ፍቅር» ብሎ መለሰላት።

ፋጡማ ትንሽ ተረጋግታ «የምትለኝ ምንም ነገር አላደረጋችሁም ነው? ማለቴ በሰመመን ፍቅር ተያይቶ መለያየት ብቻ» ብላ «አዎ» የሚለውን ቃል ከጆኒ አፍ ቸኩላ እየጠበቀች።



ጆኒ እረጋ ባለድምፅ «አየሽ ፋጡማ ታሪኩን ጀመርኩልሽ እንጂ ገና አልጨረስኩም። እንዲህ በጥያቄ የምታቋርጭኝ ከሆነ ባልነግርሽ ይሻላል» ብሎ በአንሶላ ፊቱን ተሸፋፈነ። ፋጡማ ደንግጣ «ወላሂ ዑስማን ይሙት አላቋርጥህም ጆንዬ» ብላ የተሸፋፈነበትን አንሶላ ገላልጣ ግንባሩን ሳመችው። ጆኒ ብርጭቆ ውስጥ የተረፈችውን ውሃ ጨልጦ ባዶ ብርጭቆውን አስቀመጠው።

«ይሄውልሽ ፋጡማ የሚገርመው ሁለታችንም ማለት ሬናትና እኔ በቋንቋ አልተግባባንም።» ፋጡማ ደስ ብሏት ሳታስበው «እንዴት?» ብላ ልትጠይቅ ቃላቱ ካፏ ሳይፈተለክ በእጇ አፏን እፍን አድርጋ አስቀረችው።

«እኔ ከአንዳንድ ቃላት በስተቀር በወቅቱ ጀርመንኛ አልችልም። ሀሳቤን እንድትረዳልኝ የማናግራት በእንግሊዘኛ ብቻ ነበር። እሷ ደግሞ እንግሊዘኛ ጨርሶ አትችልም። ብቻ ፍቅር የያዘው ሰው ስለሚግባባ በጥቅሻም በዲክሽነሪ (Dictionary) በምኑም በምኑም ተግባባን።»

ፋጡማ «በምኑም በምኑም» የሚለው አባባል የተረጎመችው በወሲብ ስለሆን ትንሽ በስጨት ብላ ሌላ ሲጋራ ለኮሰች።

«በእንደዚህ አይነት ሁኔታ ከመሳሳም በስተቀር ያደረግነው ሌላ ግንኙነት አልነበረም። ሁለት ወር አልፎ በሦስተኛው ገደማ እኔም እንደሷ ይገርምሻል ፋጡማ ሙች ፍቅር ያዘኝ። እያደር የጀርመንኛም ቋንቋዬ ቢሻሻልም ደፍሬ የልቤን ማጫወት ተሳነኝ። ለካስ ፍቅር ሰውን ጅል ያደርጋል የሚሉት እውነት ነው። እያደር በሁለታችን መሐከል የቋንቋ ችግር ባይኖርም ምስጢሩ ያልታወቀ የዝምታ ጥላ ረበበብን። ስንገናኝ አንዳንዴ አንድም ቃል ሳንለዋወጥ ተሻሽተን በፍቅር ተቃቅፈን ተሳስመን በመለቃቀስ እንለያያለን። ያረፍኩበት ትንሽ ሆቴል ይሄት እንዳልገባ እንብዛም ጽዳት የሌለው እንደኔው የስደተኛ መሰብሰቢያ በመሆኑ ይሉኝታ ያዘኝ።

የሆነ ቀን እሷም ትንሽ ገንዘብ ሰጥታኝ ከኔም ጨማምሬ ጥሩ ሆቴል ይዘን አብረን አመሸን» ብሎ ጆኒ የፋጡማ ስሜት በቅናት እንዳይነካ ተጠንቅቆ የወሲቡን ጉዳይ አድበስብሶ ነገራት። ፋጡማ ግን ልቧ ጠርጥሮ ባለማመን ቅናቷ ከፊቷ ላይ ይነበብ ነበር።

ጆኒ ታሪኩን እዚሁ ላይ አቁሞ ከመኝታው ለመነሳት ሞከረ። ፋጡማ የጆኒን ሰፊ ደረት ተጭና መልሳ በጀርባው አስተኛችው። ታሪኩን እንዲጨርስላት ከመለማመጥ ይልቅ ሌላ ዘዴ ፈጠረች። ግንባሩን ስማ ከንፈሩን ዝቅ እያለች አንገቱን በከንፈሮቿ እየዳሰሰች ወረድ ብላ ደረቱን ስማ ቀና አለች። «ጆንዬ ያን የምትወደውን ነገር እንዳረግልህ ታሪኩን ጨርስልኝ» ብላ በስሜት ጉቦ ደለለችው። ጆኒ ስሜቱ ሞቆ ተቅበዘበዘ። ዞር ብሎ እቅፍ አድርጉ ያዛት። ፋጡማ ካልጨረስክልኝ ብላ ተወራጨች።

ጆኒ ሳይወድ በግድ ያረጀ ያፈጀ የፍቅር ታሪኩን ማውራት ቀጠለ።

«ከሬናት ጋር የመጀመሪያ የጫጉላ ግንኙነታችን ያልኩሽ ሆቴል ተፈፀመ። ፍቅራችን ጨምሮ እጅግ ተስማማን። በሷና በኔም ጥረት ከዛች ሆቴል ወጥቼ የግል ቤት ተሰጠኝ። አሁን የእለት እለት ግንኙነታችን ከበፊቱ በለጠ። በመሐሉ ሬናት ቅሪት ሆነች።»

ፋጡማ ጆኒን አቋርጣ «ወይ መከራ ከባል ጋር ሆኖ መቅበጥ ይሄውልህ የሚያመጣው ጣጣ ታዲያ ምን አደረጋችሁ?»

«ምን እናደርጋለን ብለሽ ነው? ተያይዞ ማልቀስ ብቻ ሆነ ሥራችን።»

«የምን ለቅሶ? አስወጣችው እንዴ?»

«እኔማ እንደሱ ብያት ነበር እሷ ግን ሞቼ እገኛለሁ አለች።»

«የማናት ደደብ ከባል ጋር ሆና ከሌላ ማርገዝ ያውም ከጥቁር።»

«ፋጡማ እንዲህ የምትሳደቢ ከሆነ ታሪኩን አቆማለሁ።»

«መሳደቤ አይደለም አትሊስት ከሌላ ነጭ ቢሆን ባሏን በዘዴ ለመሸወድ አመችነቱን ለመግለጽ ፈልጌ ነው።»

የሚገርምሽ ደግሞ የሕግ ባልዋ የልጅ ጉጉት ነበረው። ሬናት ሳትደብቅ እርግዝናዋን «ያንተ ነው» ብላ ነገረችው። ባል በደስታ ቦርቆ ከበፊቱ ይበልጥ እንክብክቦ ያዛት በየጊዜው የሚሸልማት ልዩ ልዩ ስጦታዎች በረከቱ። የሐኪም ምርመራዋም በወጉ ተጠበቀ።

«ምን ዓይነት ሞራል የሌላት ይሉኝታ ቢስ ሴት ናት? ውይ በዚህ ዓይነት ሴት ሆኜ መፈጠሬን ጠላሁት» ብላ ፋጡማ ፊቷን አንገሸገሸች።



እየሽ ፋጡማ ፍቅር ከሞራልና ከይሉኝታ ይበልጣል። አትፍረጅባት እኔም እንደሷ ፍቅር ስለያዘኝ በኋላ የሚመጣብኝ መዘዝ ጉልቶ አልታየኝም ነበር። ባለችው ሀሳብ ተስማምቼ ሬናት የስድስት ወር እርጉዝ ሆነች።

«እኔ እንደዚህ ያለ መላቅጡ የጠፋ ፍቅር አይገባኝም።»

«እያድርስ ነው ፋጡማ እንደሱ አትበይ» ብሎ ጆኒ ሌላ የሚጠጣ ነገር እንድታመጣለት ነግሮ ጀርባውን አገላበጠ።

«ሬናት የመውለጃዋ ጊዜ ደርሶ ሆስፒታል ገባች።»

«ባል የሚወለደውን ሕፃን ናፍቆ ተጨነቀ። ሚስት የሚወለደውን የኔን ልጅ አምጣ ወለደች» ብሎ ጆኒ የቀረበለትን ቀዝቃዛ ሶዳ ውሃ ጅው አድርጎ ጠጣው።

የፋጡማ ባል የተወለደውን ጥቁር ሕፃን አይቶ ሚስቱን አንቆ እንደሚገላት በሀሳቧ ታይቷት ዝግንን ብሏት ተገላበጣ፣

«ታዲያ ምን አደረገ?» ብላ ጆኒን ጠየቀችው።

ጆኒ ከመፋታት አልፈሽ ከሌላ ወልደሻል ብሎ በቅናት ስሜት ተውጦ ጩቤ አልመዘዘባትም።

ፋጡማም በነገሩ በመገረም፣ «ይሄኔ ቱርኮች ቢሆኑ ሬናተ የቁራ ጠቦት በሆነች ነበር። ለዚህ ለዚህ ጀርመኖች ይሻላሉ» አለች።

ጆኒም የሀገሩን የቅናት አድራጐት ቢያውቀውም ደብቆ፣ «በሴት ጉዳይ ኢትዮጵያውያን እንደ ጀርመኖች ናቸው። ግን ሀገራቸው በጠላት ከተደፈረች ይቀናሉ። አይጣል ነው ጉዱ። እስከ ሕይወት ፍጻሜ ይጋደሉባታል» አላት፤ የቅርቡን የኤርትራና የኢትዮጵያን ጦርነት፣ የቀድሞውን የአባቶቻችንን የአድዋን ድል በአንክሮ እያስታወሰ።

«ሕፃኑስ አንተን ይመስላል?»

አዎ፣ የተወለደችው ሕፃን ሴት ነበረች፣ እንደኔ ጠይም ጥቁር ፀጉር ያላት። ደግነቱ ሁኔታው ግድያ ላይ አላደረሳቸውም ግን ትዳራቸው ፈረሰ። ሬናተ ለተወሰነ ጊዜ ከእናቷ ጋር ተቀምጣ የግል ቤቷን ያዘች። ሰውየውን በመፍራት የሁለታችን ግንኙነት በሚስጥር ሆነ። የኋላ ኋላ ስንሰማ የድሮ ባሏ ከብሬመን መቀየሩን ሰማን። ከእዛ አብረን መኖር ጀመርን። እያደር ፍቅራችን ባልታወቀ ምክንያት ቀዘቀዘ።

ፋጡማ ደስ ብሏት ፈገገች።

ቢሆንም ከመንግሥት በሚሰጠን የመተዳደሪያ ገንዘብ ልጃችንን ለማሳደግ ተቻችለን ሦስት አመት አብረን ኖርን። እያደር ሬናት ማጨስና መጠጣት ጀመረች። በሁለታችን መሐከል ዘወትር ጭቅጭቅና ጠብ ተፈጠረ። አብረን መኖር አልቻልንም። ቤቱን ለቅቄላት ወጣሁ። እሷም ሰካራም እየሆነች በመሄዷ እኔም ያኔ የዩኒቨርስቲ ተማሪ በመሆኔ ልጃችን ማኑኤላ (Manuela) በመንግሥት ድርጅት ተወስዳ የሕፃናቶች አዳሪ ት/ቤት ገባች።

«ሃይም! እሱማ ተበላሸች ማለት ነው» አለች ፋጡማ።

«ለተወሰነ ጊዜ እዛ ቆይታ በኋላ ለአንድ ጥሩ ቤተሰብ እንዲያሳድጓት ተደረገ።»

«አሁን እንዴት ነው ግንኙነታችሁ?»

«ከማን?» «ከሬናትም ከልጅህም።»

«ከሬናተ ምንም ግንኙነት የለኝም። የት እንደምትኖር አላውቅም። እንደምሰማው አገር ቀይራለች አሉ። ከልጄ ከማኑኤላ ጋር ግን ጥሩ ግንኙነት አለኝ። አሁንማ አድጋለች አንድ ቀን አስተዋውቃችኋለሁ» ብሎ ታሪኩን ጨርሶ ፋጡማን አቀፋት።

ፋጡማ ልቧ በታሪኩ አዝኖ ስሜቷ ቀዝቅዟል። ጆኒ ስሜቷን ለመለወጥ እራስጌ ያለውን ሬዲዮ ከፍቶ ሙዚቃ አሰማት። ሰውነቷን ደባብሶ ቅድም ቃል የገባችለትን ያን የሚወደውን ነገር እንድታደርግለት አስታውሶ ጠየቃት።

«እባክህን ጆኒ ሌላ ቀን ባደርግልህ ይሻላል።»

«ፕሮሚስ ፕሮሚስ ነው የምፈልገው አሁን ነው።»

«አንት ደግሞ አንዴ ችክ ካልክ አትመለስም» ብላ ከመኝታ ላይ ፍንጥር ብላ ተነሳች። ከመታጠቢያ ክፍል ቅባት ይዛ መጣች።

ጆኒ ብርድልብሱን ገላልጦ ገላውን ሰጣት። ፋጡማ ከግሮቹ ጣቶች ጀምራ በጣቶቿ እያሻሸች ታፋውን፣ ጉልበቱን አልፋ እጭኑ ደረሰች። ጆኒ ሰውነቱ እየተፍታታ በመሄዱ ደስ አለው። ፊቱን አዙሮ በሆዱ ተኛ። ፋጡማ በእጆቿ ዝቃ ያወጣችውን የመታሻ ቅባት ጀርባው ላይ ለድፋ



እያበሰች ጫን ብላ አፍተልትላ አሸችው። የአከርካሪ አጥንት የወረደበትን ቦይ የመሰለ ክፍያውን ተከትላ ወደግራና ወደቀኝ በጣቶቿ እየቧጠጠች የጆኒን ስሜት አነዘረችው። የወገቡን ጡንቻዎች እጆቿን ጨብጣ በቀስታ ደበደበችው። ቱርኮች በጀርባ ማሸት (Massage) የሚወዳደራቸው የለም። ፋጡማ ይህን ችሎታ ከቤተሰቦቿ ተምራ የሆን ቀን ጆኒን ስላቀመሰችው «ያችን የምወዳትን ነገር አድርጊልኝ» እያለ ለዚህ ነው ለታሪኩ ጉቦ ፋጡማን ያስቸገራት።

«ፋጡዬ አንቺም እንደኔ የፍቅር ትዝታ ካጫወትሽኝ በእርግጥ የምትወጅውን አረግልሻለሁ» ብሎ አቅፎ ስሟት ከመኝታው ተነሳ።

ሰዓቱ እረፍዶ ከቤት ሳይወጡ መሸ።

የሚበላ ነገር ማቀዝቀዣ ውስጥ ቢኖርም አልተሰናዳም። ለዚህም በቂ ጊዜ አልነበራቸውም። ውጪ ለመብላት ተስማሙ። ቡና ጠጥተው ሁለቱም ተያይዘው ወደለሊት የታክሲ ሥራቸው ተሰማሩ።

ጊዜው ስለመሸ የሮላንድ የቀን ፈረቃ ታክሲዎች ከየቦታው እየመጡ ሰፊ ግቢ ውስጥ ተጠራቅቀመዋል። ባዝል የሚባለው ቦታ የሮላንድ ድርጅት የታክሲዎች ማቆሚያ ሥፍራ ነው። ይህ ቦታ ሲነጋና ሲመሽ እንደ ደራ ገበያ ይደምቃል። የቀን ሹፌሮች ሥራቸውን ጨርሰው መኪናቸውን ናፍጣ ሞልተውና አጥበው ለሌላው የፈረቃ ሹፌር ለማስረከብ ይጣደፋሉ። ቀኑን ተኝተው ለሊቱን ለመሥራት በሰዓታቸው ተገኝተው አዳራሹን ሞልተውታል።

የታክሲዎቹ ባለንብረት ቢሮአቸው ተቀምጠዋል። ታላቅ ልጃቸውና ዋና ፀሐፊዋ የመጣና የቀረውን ሹፌር እየተቆጣጠሩ መዝግበው የመኪና ቁልፎችን ያድላሉ። አዳራሹ በሲጃራ ጪስ ታፍኖ ሁካታና ጫጫታ በተለያየ ቋንቋ ይሰማል። ደጁም የመኪናዎች የናፍጣ ሽታ የያዘ ጠረን አለበት። አካባቢው የሞተር ጩኸት በርከቶ ግርግር ያለበት አውድማ መስሏል። አንድ ሲገባ ሌላው ይወጣል ይህ በየእለቱ የሚደረግ የባዝል ትርኢት በመሆኑ ተለምዷል።

ጆኒ በግል መኪናው ፋጡማን ይዞ በሰዓቱ ደረሰ። እሷን አውርዶ ቀድማ ሥራ ገባች። እሱ መኪናውን የሚያቆምበት ሥፍራ በመፈለግ ዘግይቶ ትንሽ ቆየ። በእርግጥ ቦታ አጥቶ ሳይሆን ከፋጡማ ጋር ተያይዞ መግባቱን ይሉኝታ ይዞት ነው። የታክሲ ሹፌሮችን ሀሜት በደንብ ያውቀዋል።

ገና እንደ ገባ ማዶ የሆነ ኢትዮጵያዊ አጕንብሶ መኪና ሲወለውል አይቶ ደስ አለው። ደርቤ ፀጋው ነበር። ፈተናውን አልፎ የቀን ፈረቃ የታክሲ ሹፌር ሆኖ ተቀጥሯል።

ጃኒ የደርቤን ጀርባ ከኋላው ነካ አድርጐ አስደነገጠው። ሁለቱም በፈገግታ ተያይተው የሞቀ ሰላምታ ተለዋወጡ።

«እንኳን ደስ አለህ ደርቤ ምነው ሥራ መጀመርህን ሳትነግረኝ?»

«አንት መቼ እቤት ትገኛለህ ደውዬ ነበር» አለው።

«መቼ ነው ሥራ የጀመርከው?»

«ሦስተኛ ቀን ሆኖኛል።»

«ታዲያ እንዴት አገኘኸው?»

«ጥሩ ነው። ግን ከፉንከሩ ጋር አልተስማማንም።»

«እንዴት?»

«እባክህ የውጪ ሀገር ሰው አይወድም በተለይ ጥቁር እንደሚመስለኝ ዘረኛ ሳይሆን አይቀርም።»

«ደርቤ በዚህ አትበሳጭ። ገና አዲስ ነህ ለሁሉም ሥራውን እስከምትለምደው ትዕግሥት ማድረግ ነው። እኔም ያኔ ሥራውን ገና ስጀምር ያንተ ዓይነት ሁኔታ ገጥሞኛል ግን በመቻል አልፌዋለሁ። ለማንኛውም ሌላ ቀን በደንብ እንጫወታለን በርታ» ብሎ የደርቤን ትከሻ በጁ መታ መታ አድርጐ ብዙ ጊዜ ስለሌለው ውይይቱን አቋርጦ ሥራ ጀመረ።

ሮዚ ደርቤን ከሩቅ አይታ ስሜቷን ቀፈፋት። እንዳላየ ዓይታ ሰላም ሳትለው መኪናዋን ይዛ ከግቢው ተፈተለከች። ለምን እንደሆን እንጃ እሷ በምትሠራበት አካባቢ ከጃኒ በስተቀር ጨርሶ ሌላ ኢትዮጵያዊ ማየት አትፈልግም። ምቀኝነት ይሁን ወይም ከእሱ ጋር ያላቸው የቆየ ጠብ ብቻ ደርቤን ጨርሶ አትወደውም። አልፎ አልፎ መንገድ በአጋጣሚ ሲገናኙ ከሰላምታ በስተቀር በሀገር ተወላጅነት ስሜት በባህላቸው ወግና ልማድ የጠበቀ ውይይት የላቸውም።

እለቱ የሳምንቱ መሐከል እረቡ በመሆኑ የታክሲ ገበያ አልቀዘቀዘም። ሁሉም የለሊት ሹፌሮች እንደ እድልና ጥረታቸው ከወዲያ ወዲህ ተሯሩጠውና ከፉንክም በር አግኝተው የተለያየ ገቢ ይዘዋል። መሸ እንጂ ገና ለሊቱ አልተገባደደም።



ጃኒ የሆነ ጥሩ በር አግኝቶ ከከተማ እራቅ ወዳለ ሥፍራ ሄዷል። ከላውዝ በእለቱ ሥራ አልገባም። ሙራት፣ በእረፍቱ ጊዜ ለሮዚ ከሀገሩ ገዝቶ ያመጣላትን ስጦታ እስካሁን አልሰጣትም። እሷም ሰሞኑን ሥራ ስላልገባች ናፍቆ ዓይኗን ለማየት ቸኩሏል። ስጦታውን እስካሁን በኪሱ ይዞ ጥሩ አጋጣሚ እየፈለገ ተጨንቋል።

ፋጡማ ገና ሥራ እንደ ጀመረች ታክሲዋን ይዛ የሄደችው መኖሪያ ቤቷ ነበር። ሥራ እንደ ጨረሱ የዛሬውን አዳር ከጃኒ ጋር እሷ ቤት ለማድረግ ተስማምተዋል። አንዳንድ ነገር ለማዘጋጀትና ልብሷንም ለመቀየር ፈልጋ ያደረገችው ነበር።

ሮዚ የለሊቱን ሥራ በቅልጥፍና አከናውና እረፍት ከማድረጓ በፊት አንድ ሁለት በሮች ለመሥራት ፈልጋ መኪናዋን ፈርፌልድ (Fehrfeld) የታክሲዎች መቆሚያ ቦታ አሰልፋ ሙዚቃዋን ከፍታ ታዳምጣለች። ብዙም ሳይቆይ ተራዋ ደርሶ እፊት ደረሰች። አለባበሱ እጅግ ያማረ አረማመዱ የተመጠነ፣ በእድሜው እጅግ ያልገፋ ሙሉ ሰው ከወዲያ መጥቶ መኪናዋ ውስጥ ጥልቅ አለ።

በአጭር ጊዜ ጡሩ ተሳፋሪ በማግኘቷ ተደስታ ሰውዬው ሲገባ ፈገግ አለች።

«እንደምን አመሸሽ ወይዘሪት ወደ ሄሜሊንጋን ለመሄድ እፈልጋለሁ። አትስጊ፣ ዛሬ ቋሚ ዋጋ አርጊልኝ ብዬ አልጠይቅሽም» አላት።

«ምንድነው ዛሬ ብሎ ነገር። እንተዋወቃለን? ከአሁን በፊት ከእኔ ጋር አብረው ሄደዋል?»

«አዎን አውቅሻለሁ። ሮዚ ትባያለሽ ፣ከኢትዮጵያ ነው የመጣሽው!» አላት ፈገግ ብሎ።

«እርግጥ ነው፣ ከየት ነው እኔን የሚያውቁኝ? እርሶን ጨርሶ አይቼዎት አላውቅም» አለች በአድናቆት ዓይን ዓይናቸውን እያየች።

«መጀመሪያ መኪናውን አስነሺና እንሂድ። በኋላ እነግርሻለሁ» ብሏት ጉዞ ጀመሩ።

«ጊዜው በርግጥ መቼ እንደ ሆነ በርግጥ አላውቅም። ከግምት ከሦስት ወር በፊት ይሆናል። የያኔ ሁኔታዬና አለባበሴ ሮከር ወይም ጃንኪ በአጠቃላይ ዱርዬ እመስል ነበር።»

«አ! ልክነው። አሁን አስታወስኩኝ። ነጭ ለባሽ ፖሊስ ነህ። ሲያዩህ በጣም ተለውጠሀል። ይገርማል የጆሮ ጉትቻዎችህ፣ ንቅሳቶችህ የፀጉርህ ዥጉርጉር ቀለም የት ደረሱ?»

«ማስኩ ከእንግዲህ ወዲያ አላስፈለገኝም። አሁን የምሠራው ሌላ ቦታ ነው።»

«ምን ታደርጋለህ ሥራህ ምንድነው?»

«አሁን የምሠራው አዜልበስህውዞር ከሚባለው ቀበሌ የሴቶች እሥር ቤት ኃላፊ ሆኜ ነው።»

«አይ ጉድ ሙሉውን ቀን ከሥረኛ ጋር እየሠሩ አብሮ ታሥሮ መዋል? እኔስ እንዳንተ ብሆን ምርጫዬ ነፃነት አግኝቼ ነፃነት እንዳለው ሰው በነፃነት መኖርን እመርጣለሁ።»

«በዳሬክተርነት ሹመት እሥር ቤትም ሆኜ ነፃነት አለኝ።»

«እንዲህ ከሆን እንኳን ደስ ያለህ እላለሁ።»

«ጊዜ ካለሽና ከተመቸሽ በእኔ መልካም ፍቃድና ትእዛዝ የሆነ ምሽት እራት ልጋብዝሽ እወዳለሁ።»

«እሥር ቤት ይቅርብኝ አመሰግናለሁ።»

«ሃ! ሃ! ሃ! ቀልደኛ ነሽ በርግጥ ግብዣዬ እሥር ቤት ሳይሆን ፓራዳይስ ከተባለው ታላቅ ምግብ ቤት ነው።»

«ጊዜ ካለኝ ግብዣውን እቀበላለሁ» ብላ ፈገግታዋን መግባ የተባለውም ሥፍራ አደረሰችው።

«የታክሲ ሂሳቡና የስልክ ቁጥሬ ካርድ ይሄውልሽ የምንዛሪው መልስ ላንቺ ይሁን። ሲመችሽ ደውይልኝ። መልካም እድል ቻው!» ብሏት ከመኪናው ወጥቶ ሄደ።



ፋጡማና ጆኒ እረፍት አድርገው ኪስሜት ምግብ ቤት እራት በልተው ጨርሰው ሻይ ይጠጣሉ። ሮዚም ከሄሚሊንገን እንደ ተመለሰች እዚሁ ምግብ ቤት ቸኩላ ጥልቅ አለች። ጆኒንና ፋጡማን ሰላም ብላ «ፍቅር ያዳብር» ብላ በማሽሟጠጥ ወደ መጸዳጃ ክፍል ገባች። የክፍሉ ጽዳት ደስ ስላላላት ተመልሳ ወጣች። ሙራት ስትገባ ከሩቅ አይቷት ወደዛ ሲገባ እሷ ስትወጣ በራፍ ላይ ተጋጩ። ይቅርታና ሰላምታ ተለዋወጡ። ሙራት ለጥቂት ጊዜ ሊያናግራት እንደሚፈልግ በፍርሃት ተንተባትቦ ጠየቃት። ሮዚ ፊኛዋ ስለተወጠረ «በኋላ ትነግረኛለህ አሁን ቸኩያለሁ» ብላው ጥላው ሄደች። ሙራት እዛው በራፍ ላይ ፈዞ እንደቆመ ከውስጥ ቸኩሎ የወጣ ሌላ ሰው በድጋሚ ገጭቶ ጣለው።

ሮዚ ከዛው ከድንጋይ በር ቀበሌ ብዙ ሳትርቅ አንድ ጥሩ ቡና ቤት ገብታ ኮላ አዛ ተፀዳዳች። ባይጠማትም ያዘዘችውን ኮላ ተጐንጭታ ሂሳቧን ከፍላ ወጣች። እዛ የሚሠሩት ሁለት ጀርመናዊ ሴቶች እርስ በእርሳቸው ተንሾካሾከው አሟት።

«ይህችን አሁን የወጣችውን ጥቁር ታውቂያታለሽ?»

«አዎ አውቃታለሁ። ታክሲ ሹፌር ናት።»

ጠባይዋ ነጭናጫ ነው። ሰው ታመናጭቃለች። ባለፈው ጊዜ አሳፍራኝ አርባ ሳንቲም ጉርሻ ብሰጣት «እኔ ለማኝ አይደለሁም» ብላ ሳንቲሞቹን እፊቴ ላይ በተነችው። የየት ሀገር ሰው መሰለችሽ? ይሄ ዘወትር በቲቪ የምናየው የድሃዋ ሀገር ከኢትዮጵያ ነው የመጣችው። ምንም ሳይዙ ኩራት አሁን ምን ይባላል? ደደብ» ብላ ሰደበቻት።

ፋጡማና ጆኒ እራታቸውን በልተው ከኪስሜት ምግብ ቤት ወጡ። ለሊቱ ገና አልተጋመሰም። ፋጡማ መኪናዋን ይዛ ጐቴ ( ) ከሚባለው የታክሲ ማቆሚያ ቦታ ተራዋን አሲዛ ሲጃራዋን ለኩሳ ጠበቀች። ጆኒ የሄደው እሷ በሄደችበት አቅጣጫ አልነበረም። ከዲስኮ ዲስኮ እየተዟዟረ ተሳፋሪ መፈለጉን መርጦ መኪናውን ሚሞሪ ከሚባለው የታወቀ ዲስኮቴክ በራፍ ላይ ገተረው።

ፋጡማ ብዙም ሳትቆይ በፉንክ አንድ በር ማለት የታክሲ አገልግሎት ሥራ ደረሳት። ያስጠሯት ሁለት ፍቅረኛሞች ነበሩ። ተቃቅፈው ስታያቸው ደስ ብሏት የቧም ስሜት ተዝናና። ተሳፋሪዎቹ መልካቸው ይንጣ እንጂ ጀርመኖች አልነበሩም። እርስ በእርሳቸው የሚነጋገሩት በራሳቸው ቋንቋ ነበር። ራት በልተው ከሆን ምግብ ቤት መውጣታቸው ነው። የሚኖሩት አንድ ላይ አይደለም።

ሴቷ ተሳፋሪ በፓለንሽ ቅላጼ (አክሰንት) በጀርመንኛ ቋንቋ እሷ ቀደም ብላ አዲሱ ከተማ (Neustadt) እንደምትወርድና ወንዱ ጓደኛዋ ግን ከዛ እርቆ ሁክቲንግ (Huchting) እንድታደርሰው ለፋጡማ ነግራ ሁለቱም ኋላ ተቃቅፈው ተቀመጡ።

ፋጡማ ጉዞ ጀምራ እንደተነገራት መጀመሪያ ሴቲቱን በተባለው ቦታ ለማድረስ እንብዛም ጊዜ አልፈጀባትም። ፊቷን ወደ ተሳፋሪዎች መለስ አድርጋ ሴቲቱ እንድትወርድ ነገረች። ተሳፋሪዎቹ እርስ በእርሳቸው ተቃቅፈው ለመሰነባበት በቋንቋቸው እየተነጋገሩ ይሳሳማሉ። ፋጡማ እንዳያፍሩ ብላ ፊቷን ወደፊት መልሳ ወደታች አቀረቀረች። የመኪናዋ በር ተከፍቶ መልሶ ሲዘጋ እንኳን ሰምታ ገልመጥም ብላ አላየችም። መኪናዋን አስነስታ ወንድየውን ለማድረስ ወደፊት ተፈትልካ ሄደች።

ጉዞው እራቅ ስላለ ተሳፋሪው እንዳይሰለች ልታስወራው ፈልጋ ምናልባት ጀርመንኛ አይገባውም ብላ ሳታናግረው ተወችው። እሱማ እንኳን መናገር ትንፋሽም አይሰማ። የታክሲው ሂሳብ እየጨመረ 25.60 ዲኤም ደርሷል። ሁክቲንግ መሐከለኛ ሥፍራ እንደ ደረሰች ተሳፋሪው ሰው ትክክለኛውን አድራሻ እንዲነግራት ጠይቃ ፊቷን ወደኋላ በጥቂቱ አዙራ አየች። ሰውየው እመኪናዋ ውስጥ የለም። ፋጡማ ክው ብላ መኪናዋን ዳር አሲዛ አቆመች። ደግማ ብትመለከት ተሳፋሪው ሰውዬ የለም። ምን ሰላቢ ነገር ወሰደው? ብላ ደነገጠች። የታክሲውን ሂሳብ አጥፍታ በነገሩ ግራ ተጋባች። እዳው ሳይሆን ይሄን ሁሉ ጉዞ ብቻዋን መምጣቷ ገርሟት እራሷን ታዘበች። እዛው ሆና ሳትንቀሳቀስ የነገሩን ሁኔታ እየመላለሰች እንዴት ሊሆን እንደቻለ



በጥንቃቄ አሰበች። አዎ ተሳፊሪዎቹ ሲሳሳሙ ፊቷን ወደፊት አዙራ ወደታች አቀርቅራ ነበር። ታዲያ ሴቷ ስትወጣ ወንድ ተከትሎ እበራፍ ድረስ ለመሸኘት ፈልጐ አብረው ነበር የወጡት። ፋጡማ ግን ከበሩ ተከፍቶ መዘጋት ድምፅ ሌላ ዞር ብላ ስላላየች ሴትየዋ ብቻዋን የወጣች መስሏት ነበር የሄደችው።

ሮዚ በእለቱ ገቢ እንብዛም አረካችም። ቦርሳዋ ካልሞላ አይርባትም። መጀመሪያ ቦርሳዋን አጥግባ ነው እሷ የምትበላው። ጠባይዋም እንደገበያው ሁኔታ ተለዋዋጭ ነው። ስታገኝ ትደሰታለች ስታጣ ትከፋለች። በደንብም ተኝታ ካላደረች ትንሹ ነገር ያበሳጫታል። ሰዓቷን አይታ ገና ብዙ የቀረ የሥራ ሰዓት እንዳላት አውቃ በተስፋ ተዝናናች። እንዳ ጀኒ ከቦታ ቦታ ከመንቀራጠጥ መኪናዋን ፈርፈልድ የታክሲዎች ማቆሚያ ቦታ አድርጋ ተሳፋሪ ከፉንክ የሚሰጣትን ጥሪ መጠበቅ መረጠች። ከፊቷ የተደረደሩ ሌላ ብዙ የሮላንድ ታክሲዎች ቢኖሩም ቦታው ገበያ ስላለበት በምርጫዋ ሳትከፋ ተራዋን በትዕግሥት ጠበቀች።

ሙራት ከወዲያ መኪናውን እየነዳ አልፎ ሲሄድ በድንገት ሮዚን ስላያት ደስ ብሎት ከኋላዋ አቆመ። ከመኪናው ወርዶ ሮዚ መኪና ውስጥ ይቅርታ ጠይቆ ተቀመጠ። ሮዚ የእሱ መምጣት ደስ ስላላላት ሲጃራዋን ለኩሳ መኪናዋን በጭስ ሞላችው። ሙራት ሲጃራ ስለማያጨስ ቀኬው ተነስቶ አሳለው። የመኪናዋን መስኮት በቀኝ በኩል ከፍቶ ትንሽ ተነፈሰ። ጭሱን ቢጠላውም ከሮዚ ጋር ጐን ለጐን አብሮ መቀመጡ ደስ ብሎት ተዝናና።

«ይቅርታ ሮዚ ቅድም እነግርሻለሁ ያልኩትን ላጫውትሽ ነው የመጣሁት» ብሎ ወሬ ጀመረ። «ምን» ብላ ስትጠይቀው

ሙራት ነገሩን ከየት እንደሚጀምር ግራ ተጋብቶ ተርበተበተ።

«ባለፈው ጊዜ ለዓመት እረፍት ሀገሬ ቱርክ ሄጄ ነበር። ታዲያ ያኔ ያልሸኘን ስጦታ ገዝቼ አምጥቼልሻለሁና ተቀበይኝ» ብሎ ከኪሱ በወረቀት የተጠቀለለ የወርቅ ሐብል እጁ እየተንቀጠቀጠ ሊሰጣት ሞከረ።

ሮዚ «ስለስጦታህ አመሰግናለሁ ግን ሙራት ይቅርታ አድርግልኝና አልቀበልም» አለች ኮስተርተር ብላ።

«ለምን ሮዚ የኔ እህት ከልቤ ስለምወድሽ ነው ያልሽኝን የተመኘሽውን ሳልዘነጋ የገዛሁት እባክሽን ተቀበይኝ»

«በጭራሽ አላደርገውም ለሚስትህ ወስደህ ስጣት። ድሮም የቀረብኩህ አንተ በምታስበው መንገድ ሳይሆን በንጹህ ወንድምነትህ ነበር እያደር ግን ሳይህ ሁኔታህ ስላላማረኝ ካንተ ጋራ መራራቁን መርጫለሁና ይብቃን»

«ሮዚ በአላህ ይገፍሻለሁ አትራቂኝ። ለአንቺ ታላቅ አክብሮትና ፍቅር አለኝ። ከአኮረፍሽኝ እለት ጀምሮ ጤንነት የለኝም። እህል በቅጡ አልበላም። እጄ እየተንቀጠቀጠ ሥራ እንኳን በደንብ መሥራት አልችልም ታምሜአለሁ። ያንቺ ነገር አይሆንልኝም አፈቅርሻለሁ» ብሎ ተንዘፍዝፎ አለቀሰ።

«ምን ማለትህ ነው ሰውዬ አብድሃል እንዴ? አንተ እኮ አባቴ ልትሆን የምትችል ሰው ነህ እንዲህ ስትል ትንሽም አታፍርም። ቀላል ሽማግሌ አትሞላቀቅ! እባክህ ውጣልኝ ሥራዬን ልሥራበት»

«አፈቅርሻለሁ የምልሽ በእህትነት እንጂ በሌላ አይደለም እኮ ሮዚ እንደ ድሮአችን እንሁን ማለቴ ነው። እባክሽን የእኔ እህት በፈጠረሽ ይቅር በይኝ» ብሎ እጉልበቷ ላይ ተደፋ። ሮዚ ብስጭትጭት ብላ እራሱን ከጉልበቷ አንስታ ወደ ኋላ ገፈተረችው።

ደሟ ፈልቶ እየተሳደበች ከመኪናዋ አስወጣችው። ሙራት ውሃ ውስጥ የገባች ድመት መስሎ እያለቀሰ ተጐትቶ ወጣ።

ሮዚ መኪናዋን አስነስታ ተራዋን መጠበቁን ትታ ከዛ አካባቢ እርቃ ሄደች።

ሙራት ከሮዚ ጋር ተጣልቶ እንደ ወጣ ሥራ መሥራት አልቻለም። መኪናውን ባዝል አቁሞ የሮዚን ስጦታ እንደጨበጠ እቤቱ ገባ። ሚስትና ልጆቹ እቤት የሉም። ባለፈው የዓመት እረፍቱ ጊዜ አብረው ቱርክ እንደሄዱ አልተመለሱም። ቤቱ ቀፈፈው። ብቸኝነቱ ተሰምቶት ሆዱ ባብቶ ዓይኖቹ አነቡ። ፍርሃትና ጭንቀቱን ለማባበል ጠርሙስ አረቄ ከፍቶ ከውሃ ጋር ደባልቆ እየደጋገመ ጠጣ። ከሮዚ ጋር ለመታረቅ



ያደረገው ሙከራ ስለከሸፈበት በሀሳቡ ሌላ የተንኮል መረብ ዘረጋ። ሽጉጥ ገዝቶ እሷንና ከላውዝን ለመግደል ወሰነ። የጠጣው መጠጥ ሰውነቱን አግሎት አሁን አሁን እየመሰለው በንዴት እየተወራጨ ተቁነጠነጠ። አይጣል እንጂ በርግጥም የሮዚ ፍቅር ሰውነቱን ደቁሶ አክስቶታል። በዛ ላይ የእድሜም ጉዳይ ተጨምሮ ደካክሟል። ተስፋው መንምኖ ኑሮ ጨልሞበታል። በአሰበው ተንኮል እነሱን አጥፍቶ ለመጥፋት የቆረጠ ውሳኔ አድርጐ የመንጋጋ ጥርሶቹን እያፏጨ ተጠቅልሎ ተኛ።

ሮዚ ከሙራት እርቃ የታክሲ ተራዋን ትታ ከቦታ ቦታ ስትዟዟር ወደመንጋጋቱ አካባቢ ከብሬመን ውጪ እራቅ ያለ ቦታ በመሄድ የእለት ገቢዋ ዳብሯል። ንዴትና ብስጭቷ በሥራ ትጋቷ ተውጦ ለጊዜው ጠፍቷል። «ላለው ይጨመርለታል» እንደሚባለው ሆኖ አሁንም ከፉንክ ሌላ ጥሪ (በር) ደረሳት። ያስጠራት የፋጡማ ደንበኛ የነበረው የአንድ ትልቅ የቦሊንግ መጫወቻ ክበብ ባለንብረት ከበርቴ ነበር። ዝናውን ከፋጡማ ስለሰማች እመኪናዋ ውስጥ ገብቶ ሲቀመጥ ከሰላምታ በስተቀር ተጨማሪ ፈገግታ አላሳየችውም። ሰውየው ግን ከፋጡማ የበለጠች የጠይም ቆንጆ ሹፌር በማግኘቱ ደስ ብሎት ተዝናንቶ ተቀመጠ። ጉዞ ጀምረው ሲሄዱ የቆጥ የባጡን እያወራ ብቻውን ከት ብሎ ሣቀ ሁኔታው መጠጣቱን ይመሰክርበታል።

«ቆንጅዬ ሹፌር ነሽ ማን ትባያለሽ?»

«አመሰግናለሁ ሮዚ።»

«ሮዚ ደስ የሚል ስም ነው እውነት ከአንቺ ጋር ከተማውን ስዞር ባድር ደስታውን አልችለውም።»

«እኔ ደግሞ ዓላማ የሌለው ሰው ደስ አይለኝም። በዚህ ላይ ለሊቱ አልቆ እየነጋ ነው። ወዴት ልውሰድዎ?»

«አንቺን ደስ ወዳለሽ ሥፍራ ሮዚ።»

«እንዴት ነው ደስ ያለሽ ሥፍራ ብሎ ነገር ታክሲ ሲያዙ የሚሄዱበትን ቦታ አልወሰኑም?»

«ብወስንም ሮዚ ሀሳቤን የመለወጥ መብት አለኝ ፍቃድሽ ከሆነ ቁርስ ልጋብዝሽ።»

«አመሰግናለሁ አሁን ግን ጊዜ የለኝም።»

«እንዳው ልጠይቅሽና ሮዚ ለምንድነው የታክሲ ሹፌር የሆንሽው እንደዚህ ያለ ቁንጅና ይዘሽ?»

«ሥራ ሥራ። ነው በግንባሬ ላብ ገንዘብ ለማግኘት።»

«ታዲያ ሮዚ ገንዘብ ከፈለግሽ ችግር የለም የናጠጥኩ ከበርቴ ነኝ። እኔ ልቅጠርሽ» ብለው ከኪሳቸው ብዙ ገንዘብ አውጥተው አሳይዋት።

ሮዚ ቆጣ ብላ «እኔ ሹፌር እንጂ ሸርሙጣ አይደለሁም ገንዘብህ እንዳንተ ይሸታል ውጣልኝ!» ብላ አንቱታውን ትታ በመናቅ ከመኪናዋ ገፍትራ አስወጣቻቸው።

ሊነጋጋ አካባቢ ጆኒ ከፉንክ አንድ በር ደረሰው። የተባለው ቦታ ደርሶ ታክሲ ያዘዙትን የሴት ስም ተጭኖ ደወለው።

ፀጉራቸው እረዥም እድሜያቸው መሐከለኛ የሆኑ ጀርመናዊት ሴት የአጥቢያ ኮከብ መስለው ከቤቱ ብቅ አሉ። ገና ሳይነጋ የፀሐይ ጥቁር መነጽር ማድረጋቸው ጆኒን ገረመው። በእጃቸውም ነጭ ዘንግ ብጤ ይዘዋል። ደንበርበር እያሉ ከበሩ ወጥተው ደረጃው ላይ ቆሙ።

ጆኒ ሴትየዋ እውር መሆናቸውን አውቆ ሮጦ ደግፎ እየመራ መኪና ውስጥ አስገባቸው። በእርዳታው አመስግነው የሚሄድበትን ቦታ በትህትና ነገሩት።



ጆኒ መጀመሪያ የመኪናውን ኋላ ማርሽ አስገብቶ ትንሽ ከተንቀሳቀሰ በኋላ መሪውን ወደ ግራ ጠምዝዞ ወደፊት ሲነዳ ከግቢው አጥር ጋር ተላትሞ ተጋጨ። ሴትየዋ ከው ብለው ደንግጠው በረገጉ። ጆኒ ግጭቱ መጠነኛ መሆኑን አይቶ ሲመለስ ሁኔታው ለሴትየዋ ገልጾ አባበላቸው «እውርን አውር ቢመራው» ሆኖበት የተሳፋሪዋን ድንጋጤ በልዩ ጭውውት ለመለወጥ ፈልጐ « ጆሮ ያለው ሁሉ አዳማጭ አይደለም» ዓይንም ቢቁለጨለጭ ሁሉን አያሳይም፣ ልቦና ይበልጣል ከሁሉም ከሁሉም» ብሎ ሴትየዋን አጽናናቸው።

እውሯ ሴትዮ በግጥሙ ተማርከው «ታዲያ አሁን የእርሶን ልቦና ማን ወሰደው?» ብለው ጠየቁት እንደቀልድ እየሳቁ። «ሸጋ ውበትዎ» ለማለት ፈልጐ ተወው። በምትኩ «የለሊት ሥራ ልቦና አሳጥቶ ቀልብ



ይገፋል። በዛ ላይ ድካም ሲጨመር እንደ አሁኑ ያለ ግጭት ይፈጥራል።» አላቸው ፊቱን ወደ ሴትየዋ አዙሮ ጥቁር መነጽራቸውን እያየ።

«የለሊቱን ሥራ ከጠሉ ለምን በቀን አይሠሩም?» አሉ ቃላቶችን እንጂ ማለት የቀንና ጭለማን ልዩነት አንብዛም የማያውቁት እውር ሴት ወይዘሮ።

«እሜትዬ ወድጄ አይደለም የንጀራ ጉዳይ ሆኖብኝ ነው። የታክሲ ገበያ ከቀን ይልቅ በምሽት ይበልጣል። ሁሉንም ሞክሬ አይቸዋለሁ። ለእርሶስ፣ የትኛው ይሻላል? ብሎ እውር መሆናቸውን ዘንግቶ አፉ እንዳመጣለት ጠየቃቸው።

እኔማ ኑሮዬ ዘላለም ጥቁር ጭለማ ነው። እንደ እርሶ የቀንና የጭለማ ምርጫ የለኝም። አሉ እያዘኑ።

«ይቅርታ እሜትዬ።»

«ለምኑ ነው ይቅርታ። »

«ሳላስበው ስሜትዎን የሚጐዳ ጥያቄ በማቅረቤ እንዳልከፋዎት አሁንም የማስተዋል ልቦና ይጐለኛል» ብሎ በራሱ አዘነ።

«አይ እንዲህ ያለው ጥያቄ ጨርሶ ስሜቴን አይጐዳኝም። ዝም ብሎ መኪና ከሚነዳ ሹፌር ይልቅ እንደርሶ ያለ ተጫዋች ሰው እወዳለሁ። ለኔ ዝምታ ከጭለማ የባሰ ሲኦል ነው። ድምፅ ውይይትና ጫወታ ለእኔ እንደ ብርሃን የምቆጥራቸው የአካሌ መዝናኛ የስሜቴ አውታር ሙዚቃ ናቸው። ለመሆኑ የየት ሀገር ሰው ነዎት?»

«ከየት የመጣሁ ይመስልዎታል እስቲ ገምቱ።»

«ይቅርታ አድርግልኝና መኪናውን ወደዳር አቁመው» ብለው የጆኒን ከርዳዳ ፀጉር በለሰለሰ እጃቸው ዳሰሱት ጆኒ ደስ አለው። ፊቱን ቀጥ ያለ አፍንጫውን ስስ ከንፈሩን ነካክተው ደባበሱት። መኪናውን አስነስቶ ሲጓዙ—

«ከፁጉርዎ በስተቀር ገጽታዎ እንደኛው ጀርመኖች ነዎት። አነጋገርዎ የጠራ ቢሆንም የሆነ ቅላጼ አለበት። ጆኒ ንግግራቸውን አቋርጦ «ፈስ ያለበት» ሆኖበት «የቆዳዬስ ቀለም እንዴት ነው?» አላቸው።

«በዚህ በኩል ያለውንማ ጨርሶ አላውቅም። ለኔ ሁሉም እኩል ነው የቀለም ልዩነት ጨርሶ ስለማላውቅ ጥያቄዎን ልመልስ አልችልም» ብለው ሲመልሱ ጆኒ እነዚህ የቀለም ልዩነት እያደረጉ የሚሳደቡትን

ዘረኛ ጀርመኖች ሁሉ እንደሳቸው እውር በሆኑ ብሎ በሆዱ ተመኘ። ሴትየዋ ንግግራቸውን ቀጥለው የመጀመሪያውን ጥያቄ ለመመለስ ሞከሩ። ምናልባት ከመሐከለኛው ምስራቅ ሀገሮች ወይም ከምስራቅ አፍሪካ የመጡ ሰው መሆን አለብዎት ብለው ገመቱ።

«እሜቴ ልክ ነዎት። የመጣሁት ከምስራቅ አፍሪካ ከኢትዮጵያ ነው» ብሎ አደነቃቸው። በልቡም ስንቱ ዓይኖቹ ያፈጠጡ ጀርመኖች ለይተው ያላወቁትን እኚህ እውር ሴት በዳበሳ በማወቃቸው ተገረመ። «ለመሆኑ እንዴት ሊያውቁ ቻሉ?» ብሎ ጠየቃቸው። የፀጉርዎ ከርዳዳነት ካልዎት የገጽ ውበት ጋር ተደምሮ ስለረዳኝ ነው በዚህ አይደነቁ። ያልኩሆት ቦታ የደረስን መሰለኝ ብለው የታሠሩበትን ቀበቶ ፈቱ። ስፍራውን በማወቃቸው ጆኒ አሁንም ደነቀው። የታክሲ ሂሳቡንም ሳያዩ አስበው የገንዘቡንም ኖት ለይተው ከፈሉት። ድንቅ ነው ብሎ አመስግኖ ከመኪናው ደግፎ አወጣቸው።

ለሊቱ አልቆ ሰማዩ ፈግጎ ነግቷል። እውሯ ተሳፋሪ ወይዘሮ የማይጠገብ ፈገግታቸውን በጠዋት ከወጣችው ጨረር ጋር አብረው እየፈነጠቁ ጆኒን ተሰናበቱ። «ልቦና ከሚነሳ ጭለማ እንኳን ገላገለህ። መልካም የብርሃን ቀን ይሁንልህ ደህና ሁን» ብለው በተናገሩት አሽሙር እሳቸውም መልሰው እየሳቁ ጆኒን አሳቁት።

«ለእርሶም የዘላለም ብርሃን የዓይን ጮራ ይስጥዎት» ብሎ መመኘቱ እንደስድብ ስለቆጠረው ትቶ «ደህና ሁኑ እሜቴ መልካም ቀን፣ በቸር ይግጠመን» ብሎ ተሰናበታቸው።

የባዝል አዳራሽ እንደተለመደው በሲጋራ ጪስ ተሞልቷል። የለሊት ሹፌሮች ሥራቸውን ጨርሰው የእለቱን ሂሳብ ያሰላስላሉ። የቀን ፈረቃ ሠራተኞች አንድ በአንድ እየመጡ ተጠረቃቅመዋል። ማዶ ሮዚና እንድርያስ ሂሳባቸውን ጨርሰው እርስ በእርሳቸው ይወያያሉ።

እግቢው ውስጥ በእድሜያቸው ጠና ያሉ ሁለት ጀርመናዊ ሴቶች ቆመዋል። የቀን ቀን ፈረቃ የታክሲ ሹፌሮች ናቸው። እነዚህን አሮጊቶች ሮዚ ጥሉባት አትወዳቸውም። እነሱም ሲያይዋት ምንቅር ምንቅር ስለምትልባቸው እንብዛም አይወዷትም። እንዳጋጣሚ ሆኖ ሮዚ የባዝልን አዳራሽ ለቃ ስትወጣ፣ እነሱ ከደጅ ተከታትለው ሲገቡ በራፉ ላይ እርስ በእርሳቸው ተጋጩ። ሁሉም ይቅርታ አልተጠያየቁም። እንዳውም ሮዚ ቆጣ ብላ «የማንም ጨምዳዳ አሮጊት ሁሉ አይታችሁ አትገቡም» ብላቸው ሄደች።



እነሱም በሁኔታዋ ተገርመው፡-

«እንዳንቺ ካለ ጥቁር እንግዳ፣

ይሻላል፣ ምን ጊዜም የነጭ ጨምዳዳ» ብለው በስድብ ግጥም ወረፏት።

ጆኒ ባዝል የደረሰው አርፍዶ ነበር። አዳራሽ ውስጥ ብዙ ሰዎች አልነበሩም። ፋጡማም ብትሆን አልጠበቀችውም። ፍቅረኛዋ ጆኒ በእለቱ ቤቷ እንዲያድር ስለቀጠረችው ቁርስ ለማዘጋጀት ቀደም ብላ እቤቷ ገብታለች። የለሊቱ ሥራ ጆኒን ቢያደካክመውም የፋጡማን ቀጠሮ በመጠበቅ በሰዓቱ እቤቷ ደረሰ። በእርግጥ ለቤቱ እንግዳ አልነበረም።

ፋጡማ የውስጥ ገላዋን የሚያሳይ ስስ ፒጃማ ለብሳለች። ተንጠልጣይ ጉትቻዎቿን አውልቃ በምትኩ ትናንሽ የወርቅ እንቡጦች አድርጋለች። የምትወደውን ልዩ የፓሪስ ሽቶ ሰውነቷን ደባብሳ ተቀባብታለች።

ጆኒ በሩ ተከፍቶ ሲገባ ክፍሉ ደስ የሚል ሽታ አወደው። ዓይኖቹ የፋጡማን ብሩህ ገፅታ አልፈው ያጉጠጎጡ ጡቶቿ ላይ አረፉ። እርስ በእርሳቸው ተቃቅፈው ተሳሳሙ።

ጆኒ በሥራ የደከመ አካሉ በርትቶ የውስጥ ስሜቱ ጐረመሰ። ልብሶቹን በቅጽበት አውልቆ እመታጠቢያ ፋጡማን ይዞ ገባ። የሞቀው ሻውር እንደ ዝናብ በላያቸው ላይ ወረደ። ተቃቅፈው እየተሻሹ ደግመው ደጋግመው ተሳሳሙ። የስሜት አውታራቸው ተጋግሎ፣ ጆኒ ፋጡማን እንደ ሕፃን ልጅ ታቅፎ እመኝታ ቤት ገባ። ደረቷ ላይ ተኝቶ ጡቶቿን እየሳመ አንገቷን አልፎ የግራ ጆሮዋን በከንፈሮቹ ይዞ መጠመጠው። የሆነ ነገር በአፉ ሽር ብሎ ገብቶ በማንቁርቱ ተቀረቀረ። ደጋግሞ እየሳለ ካልጋው ዘሎ መታጠቢያ ቤት ገባ። በስሜት ኃይል ተገፍትሮ ሳይታወቀው የዋጠውን የፋጡማን የወርቅ ጉትቻ ለማውጣት ታግሎ አቃተው።

ፋጡማ የታመመ መስሏት ደንግጣ መታጠቢያው ክፍል ገብታ ደረቱን ያዘችው። ጆኒ ሁኔታውን ለፋጡማ እየሳመ ሲነግራት ከት ብላ ስቃ «መልካም ምግብ» ብላ የግራ ጆሮዋን ጨብጣ ቀረች።

• • •

ፋጡማና ጆኒ ከእንቅልፋቸው የነቁት እረፋዱ ላይ ነበር። የሁለቱም ሰውነት ደካክሟል። ፋጡማ ጠዋት ያልተበላውን የቁርስ ዝግጅት አሙቃ፣ ሌላም ጨማምራ ለጆኒ አልጋው ላይ አቀረበችለት። ጥቂት አብረው ጉራርሰው መአዱ ተነስቶ ቀዝቃዛ ኦራንጅ ተጉነጩ።

ጆኒ ወደግራ ዞሮ ትራሱን ተደግፎ በሆዱ ተኛ። ሁኔታው ፋጡማ ስለገባት ቆጣ ቆጣ ብላ ጉትቻዋ በመዋጡ አኩርፋ ካሣ እንዲሆንላት ፈልጋ። «ዛሬ የአንተ ተራ ነው በደንብ እሸኝ» ብላ በትእዛዝ ጆኒን ገላምጣ፣ በሆዱ ተኝታ፣ ጀርባዋን ሰጠችው። ሁለቱም ሁሉን ጨርሰው የፍቅር ወሬ መወያየት ጀመሩ።

ጆኒ የትላንት ወይም የነገ ፍቅር እንደሌለ ነገራት። ፋጡማ በአባባሉ ተገርማ «ታዲያ ፍቅር ያለው መቼ ነው?» አለች።

«ፍቅር ፍቅር ያለው ዛሬ ነው በአሁኑ ደቂቃ ካንቺ ጋራ።» ብሎ አስረዳት።

«እውነት ጆንዬ ታፈቅረኛለህ?»

«መጠርጠሩሳ በደንብ ነዋ!»

«በምኔ ነው የምታፈቅረኝ?»

«በሁለመናሽ አንቺነትሽን ወድጄ አፍቅሬሻለሁ።»

«አትዋሸኝ አንተ የምትወደው ያቺን ነገር ብቻ ነው።»

«ምን?»

«ያቺን ነገር!»

በርግጥ ፋጡዬ ወሲብ የፍቅር መሠረት ነው። ግን አንቺን ያፈቀርኩሽ በሱ ብቻ አይደለም። እንዳልኩሽ በሁለመናሽ በቁንጅናሽ በጠባይሽ ወዘተ ጭምር ነው። ደግሞ በወሲብ ብቻ የተመሠረተ ፍቅር አይዘልቅም፣ ቢዘልቅም መጨረሻው አደገኛ ስለሚሆን እፈረዋለሁ።

«ያስደስታል እንጂ ምኑ ያስፈራል። እኔ ደግሞ ወላሂ ሴክስ የሌለበት ፍቅር አይጥመኝም። ዜግነት፣ ሃይማኖት፣ መልክ ጠባይ ገንዘብ ፍቅር ሁሉም ተጠረቃቅመው ሴክስን አያክሉም ለእኔ ሴክስ ዋና ወሳኝ ጉዳይ ነው» ብላ የሀገሯን የቁርክ ተረት ገጠመችለት።

«የመቁጠሪያ ጠጠር (ዶቃ)

ቢበዛም ቢያንስም

ማሠሪያው ክር ነው ሁሉን የሚይዝ» የሚል ነበር።



ጆኒ የፋጡማን አባባል ሰምቶ የእድሜ መግፋቱን ከአለበት የስኳር በሽታ ጋር ተደምሮ ባለችው ጉዳይ ላይ ለከርሞ ብርታት እንደማይኖረው ሰግቶ ፈራ። ምን ጊዜም ፍቅር ከወሲብ እንደሚበልጥ ለፋጡማ ነግሮ ማሳመን እንደማይቻል አውቆ ተሸፋፍኖ ተኛ።

ፋጡማ ሽፍንፍኑን ገልጣ ከበፊቱ ለየት ያለ ጥያቄ አቀረበችለት። ስላለፉት ፍቅረኞቹና የተለያዩበትን አብይ ምክንያት እንዲያጫውታት ነበር። ፋጡማ ጥሎባት ከሁሉም ነገር እንዲህ ያለውን ነገር መስማት ትወዳለች። ከአሁን በፊት ጨቅጭቃው አንድ ሁለቱን ነግሯታል። ግን ጆኒ አንዲት ያገሩን ልጅ ወዶ አብረው አንድ ቤት ሦስት ዓመታት ኖረው መለያየታቸውን ነግሯት የታሪኩን ዝርዝር በደንብ ስላላጫወታት ምናልባት መልሰው ይገናኙ ይሆን? በሚል ስጋት ወይም በሌላ ሁኔታ ነገሩን ለማወቅ ጓጉታ ወተወተችው። ጆኒ ፋጡማን አፍቅሮ ጭቅጭቋን አይወድም። አንዳንዴ ብቸኝነቱን ይመርጣል። ያፈቀረ ደግሞ የመረጠውን ማድረግ አይችልም። ፍቅር ወጥመድ ነው። ፍቅር ላፍቃሪው የፈለገውን ማድረግ መስጠት መሰዋት ነውና ፋጡማ የጠየቀችውን በአጭር ባጭሩ ዘርዝሮ አጫወታት።

«አዎ ፋጡማ ባለፈው ጊዜ እንደገለጽኩልሽ ልጅቷ ስሟ እልፍነሽ ሣህሉ ትባላለች ኢትዮጵያዊት ቆንጆዬ ልጅ ናት።» ፋጡማ ብስጭትጭት ብላ «ቁንጅናዋን ትተህ ይልቅ ታሪኩን ንገረኝ ብላ ሲጋራዋን ለኮሰች።

«የተዋወቅኋት እዚህ ብሬመን ሳይሆን ሐምበርግ ከተማ ነበር። ከሀገሯ ከመጣች ገና ሰባት ወሮች ሆኗታል። የፖለቲካ ጥገኝነት ጠይቃ የምትኖረው እታናሽ እህቷ ቤት ነበር። እንዳጋጣሚ የሆነ በዓል ሆኖ ተጋብዤ ሄድኩ። ተዋወቅን። ተግባባን። አድራሻ ተለዋውጠን ተለያየን። በሆነ ቀን ብሬመን ጋብዣት መጣች። በደንብ አስተናግጄ አድራ በማግሥቱ ሸኘኋት። ፋጡማ ሲጋራዋን ቶሎ ቶሎ ማግ ማግ አድርጋ ጭሱን ወደላይ አቡና «ማስተናገድ ማለት ምንድነው በአንድ ቀን ትውውቅ ሴክስ አደረጋችሁ?» አለችው።

«እንግዲህ ምን ብዬ ልንገርሽ በዛን ሰዓት የምኖረው ብቻዬን ነበር ያገሬ ቆንጆ ልጅ እቤቴ አድራ እንዳው ሳልዳራ እንቅልፍ የሚወስደኝ ይመስልሻል? ጥሩ ማስተናገድ የምልሽ እሱንም ጭምር ነውና እወቂው» ብሎ አፈጠጠባት። ፋጡማ ቅናቷን ሲጃራዋን እመተርኮሻው ላይ አጥፍታ በመደፍጠጥ ተወጣችው።

«ግን ያንንም ያደረግነው በደንብ አላዳመጥሽኝም እንጂ በእለቱ ሳይሆን በጣም ዘግይቶ ነው። በቴሌፎን ተጨዋውተን ደብዳቤ ተጻጽፈን ይበልጥ ከተግባባን በኋላ ነው እዚህ የመጣችው። ብቻ ታሪኩን አሳጥሬ ልንገርሽ። እሷም እየተመላለሰች እኔም እየተመላለስኩ ግንኙነታችን ጠንክሮ ተዋደድን። በመጨረሻ ሐንበርግን ትታ እኔ ቤት ገባች። አብረን በፍቅር ሦስት ዓመት ኖርን። የመጀመሪያ ልጇንም ከሀገር ቤት ሁሉን ጨርሼ አስመጣሁላት። ቤቱ ከሁለት ሦስት በመሆናችን ደርቶ ሞቀ። ልጆች ቢኖሩኝም ከእልፍነሽ ተጨማሪ ልጅ እንዲኖረኝ ተመኘሁ።

በሆን ወቅት ከሀገር ቤት የመጣችውን ሴት ልጇን ለእህቷ ወስዳ ለማሳየት ተያይዘው ሁለቱም ወደ ሐንበርግ ሄዱ። እዛ ሰንብተው አንድ ሁለት ወር ቆዩ። ልጅቷም እዛ ት/ቤት ስለተገኘላት አብራ ከአክስቷ ጋር መኖሩን መረጠች። እልፍነሽ ተመልሳ መጣች። ግን ልጅ ማዶ እናት እዚህ በመሆናቸው ሁለታችንም ሐንበርግ እንድንኖር ሀሳብ ቀርቦ እኔ ሳልስማማ ቀረሁ። እሷ ግን የልጇን ምክንያት አድርጋ ኑሮዋ እዚህም እዛም ሆነ። በዚህም ምክንያት ይሁን በሌላ ፍቅራችን እየበረደ ሄዶ ቀዘቀዘ። በዚህ ሁኔታ እንዳለን ይገርምሻል ፋጡማ እልፍነሽ አረገዘች። የተመኘሁት በመድረሱ ደስ ብሎኝ ሳምኳት። ልዩ ልዩ ስጦታም ገዝቼ ሰጠኋት። የቀዘቀዘው ፍቅራችን በእርግዝናዋ ምክንያት መልሶ ሞቀ። እዚህም ሆነ ሐምበርግ አንድ ሰፊ ቤት ተከራይተን አብረን ለመኖር ወሰንን። ግን የሴጣን ነገር ሆኖ ሁለቱም ቦታዎች የኪራይ ቤት አጣን።

ፋጡማ ንግግሩን አቋርጣ «እባክህን አልተስማማንም በል እንጂ እንዴት የኪራይ ቤት ይታጣል?» አለችው ተጠራጥራ።

«የተመኘሁትን ልጅ ከኔ አርግዛ እንዴት አንስማማም ብለሽ ትገምቻለሽ?» ብቻ ምክንያቱ ይሄው ሆኖ አብረን መኖር አልቻልንም። ሲውል ሲያድር ሆዷ እየገፋ መጥቶ የመውለጃዋ ጊዜ ተቃረበ። እዚህ መመላለሱን ትታ ግንኙነታችን በስልክ ብቻ ሆኖ ዓይኖቿን ማየት ጓጉቼ ስናፍቃት ሰነበትኩ።

የሆነ ቀን የእርጉዝ ልብስና የሕፃናት አሻንጉሊት ይዤ ሐንበርግ የምትኖርበት እህቷ ቤት ሄድኩኝ። አልነበረችም። የሆነ ምክንያት ተነግሮኝ ተመልሼ መጣሁ። ከትንሽ ቀናት በኋላ ሆስፒታል መግባቷን ሰማሁ። ሄጄ ጠየቅኋት ገና አልተገላገለችም።

በሦስተኛው ቀን በጠዋት ቤቴ ስልክ ተደወለ። አነሳሁት እሷ ነበረች። ድምጿን ስሰማ ደስ አለኝ። ስቅስቅ እያለች ታለቅሳለች። «ምን



ነካሽ» ብዬ ደንግጬ ጮኩባት። «ምን ተፈጠረ ለቅሶው ምንድነው?» ብዬ እኔም እንደሷ መናገር አቅቶኝ ተንተባተብኩ። በኋላ ብዙ ተንፍሳ ማቃሰቷን አቁማ «መውለዷን ደህና ተገላግያለሁ» ስትለኝ ደስ ብሎኝ ጭንቀቴ በረደ። በኋላ «ይቅርታ ጆንዬ ተሳስቼ ጥፋት አድርጌአለሁ» አለችኝ። «የምን ጥፋት አልገባኝም!» ብዬ ጮኩባት። «ልጁ ያንተ አይደለም የአንድ ጀርመናዊ ሰው ነው። የኔን መልክ እንኳን አልያዘም አባቱን ቁርጥ ነጭ ነው» ብላ አረዳችኝ።

ስልኩን በጆሮዋ ላይ ዘግቼ የምሆነውን አጣሁ። ያዙኝ ልቀቁኝ ብዬ ከስሜቶቼ ጋር ታግየ አበድኩ። በቅናት ተንገርግቤ ነደድኩ። ሁለቱን ለመግደል ወስኜ ጨከንኩ።

ፋጡማ ንግግሩን አቋርጣ «ውይ ያላህ ሥራ ይገርማል ከአሁን በፊት አንተ እሰው ትዳር ውስጥ ገብተህ የሰው ሚስት አባልገህና አስረግዘህ አሁን ደግሞ ብድሩን አገኘህ። ይሄ ታምር ነው» ብላ መጨረሻውን ለማወቅ ጓጓች።

ጆኒ ከመኝታው ሳይወድ ተነስቶ ወገቡን ቀና አድርጎ ቁጭ አለ።

«ያኔ የሆንኩትና የደረሰብኝ አይጣል ነው» ለምን አስታወሺኝብሎ ፋጡማ ላይ ጮኸባት።

ፋጡማ፣ «ይቅርታህን ተወው፤ ደግሞ በቀደም ስትናገር፣ ‹እኛ ኢትዮጵያውያን በሀገር እንጂ በሴት አንቀናም› ብለህ አልነበረም እንዴ? ታዲያ ምን ነካህ ጆኒ?»


«አላውቅም፤ ቅናት ይሁን ሌላ በሽታ ብቻ እንደ እብድ ወፈፍ አድርጎኝ የምይዝ የምጨብጠውን አጣሁ። በደመነፍስ ስልኩን ዘግቼ ሁለቱንም፣ እልፍነሽንም ሕፃኑንም፣ ልበቀል ወስኜ ትንሽ ስለታም ቢለዋ እቅፍ አበባ ውስጥ ደብቄ ወደ ሆስፒታል ለመሄድ መኪናዬ ውስጥ ገባሁ።»

«እሷንስ ይሁን ሕፃኑ ደግሞ ምን አደረገ?›

«ፋጡማ፣ ቅናት! ቅናት የሚሉት በሽታ ለክፎኝ ነው ሁለቱን እንዳጠፋቸው ያደረገኝ!»

«ይሄ በሽታ አይደለም፤ እብደት ነው» እንዳለች የፋጡማ በር ተንኳኩቶ የጀመሩት ወሬ ተቋረጠ።

# ክፍል አሥራ ሁለት



የተፈጥሮ ሕግ ጊዜውን ጠብቆ ተከሰተ። የበልግ ወቅት (Herbest) ሥፍራውን ለክረምት (Winter) ለቀቀ። መልካቸው ከአረንጓዴነት ተለውጦ የበጨጩ ዛፍና ተክሎች ቅጠላቸው ሙልጭ ብሎ እረገፈ። አየሩ ቀዝቅዞ በረደ። ሰማዩ ደምኖ አለቀሰ። የበረዶ ቅልቅል ዝናብ በአውሮፓ ተርከፈከፈ። ሜዳውና የቤቶች ጣራ በነጭ የበረዶ አጉበር መሸፈን ጀመሩ።

የሕዝቡ አለባበስ ከወትሮ የተለየ ሆነ። ከውስጥ ካኒቴራ፣ ቡታንቲና ሌላ የውስጥ እረኸርም ስስ ሱሪ፣ ሸሚዝ ወፍራም ሹራብ፣ የሚሞቅ ጃኬት ወይም ኮት በላዩ ላይ ካፖርት ተጨመሩ። የእጅ ጓንቲ ተደርጐ ወፍራም ጫማ ተጫምቶ አንገትን ፎጣ በሚያክል እስካርፍ ጠምጥሞ መታየት ሆኗል።

ለወትሮ ፍጥነታቸውን ሳይገቱ ቸኩለው ከወዲያ ወዲህ የሚሽከረከሩት ታክሲና ሌላም ተሽከርካሪዎች ሉጋሙ ወደኋላ እንደተሳበ ፈረስ አቆብቁበው በቀስታ ተጓዙ።

እለቱ የወሩ መጀመሪያ በመሆኑ ደምቋል። ሠራተኛው ወር ሙሉ የደከመበትን ደሞዝ ያለገደብ የሚያባክንበት ምሽት በመሆኑ የመጠጥ ቤቶችና የቤተኛ አዳሪ መናኸሪያዎች የፈንጠዝያ አውድማ ሆነዋል። ያገባው ቆንጆ ሚስቱን እቤቱ አስቀምጦ፣ ያላገባው ለፍላጐቱ ማርኪያ



ገንዘቡን ጨብጦ ወደከተማው የምሽቱ መፈናጠዣ ሄዶ ይቀብጣል። የወረት ፍላጐቱ ስሜቱን እየኮረኮረ በማሞቅ የወረት ደስታ ይሰጠዋል።

የብሬመን ትንሽ ከተማ የምሽቷ ወቅት በዚህ ቀን እንደሌሎቹ ትልልቅ ከተሞች ትሞቃለች። ትደምቃለች። በአሥረሽ ምችው አሸሸ ገዳሜ ትዋባለች። የሕዝቡ ትርምስ፣ ሁካታና ጩኸት ምሽቱን የቀን የደራ ገበያ ያስመስለዋል። ሰካራም በርከቶ ያዙኝ ልቀቁኝ ይላል። አልኮል ደሙን አሙቆ አይምሮውን ስለነሳው በሆነ ባልሆነ ምክንያት ፈጥሮ ይደባደባል ይፈናከታል። አንዳንዱም የዋህ ጅል ብጤ ሰካራም እረብጣ ገንዘቡን እየመዘዘ የሚያውቅ የማያውቀውን ከዳር እስከ ዳር እየጋበዘ ጉራውን ይነፋል። የሳቅ የለቅሶ የሪታና የኡኡታ ጩኸት በየቦታው አልፎ አልፎ ይሰማል።

ፖሊሶች በሥራ ተወጥረው ይሯሯጣሉ። አንዱን አሥረው ሌላውን ለቀው የተጣላውን ገላግለው የሰረቀውን አሳደው ይይዛሉ። የትራፊክ ፖሊሶች ሰክረው የሚነዱትን ሹፌሮች እየመረመሩ መንጃ ፈቃድ ይነጥቃሉ። የአንቡላንስ መኪናዎች በጠብ የቆሰለውን፣ ቁንጣን ወጥሮት ከመጠን በላይ ጠጥቶ ሲወላገድ ወድቆ የተከሰከሰውን ምስኪን አግበስብሰው ይወስዳሉ። የመኪናቸው ጡሩንባ እሪታና ዋይታ እያባረቀ ይጮሃል። የተኙ ሕፃናቶችን አባርቆ ያስደነግጣል።

ጊዜው ክረምት ቢሆንም ምሽቱ ይሞቃል። የበረዶ ንስናሴና የመንገዱ እርጥበት የታክሲ ሹፌሮችን ፍጥነት እንደወትሮ ሊገታ አልቻለም። በምሽቱ ጥሩ ገበያ አግኝተው ቦርሳቸው የሚወጠረው በዚሁ የወር መጀመሪያ እለት በመሆኑ ይጣደፋሉ።

በማግሥቱ ሥራ ቢኖርም እስከ ለሊቱ አጋማሽ ጥቂትም አለፍ ብሎ ያለማቋረጥ ይጠጣል ይበላል ተደንሶ ይፈነጠዛል። ምሽቱ አልቆ የሚነጋ አይመስልም። ለነገ ብሎ ነገር ጨርሶ አይታሰብም። «ዓለም አላፊ ጠፊ ናት በሕይወት ሳሉ መደሰት ዛሬ ነው» እየተባለ እንደ ሕፃን ልጅ ቦርቆ እንደሠርገኛ ጨፍሮ ይመሻል።

ጆኒ ያለፈውን የለሊት የታክሲ ሥራ ጨርሶ እቤቱ የገባው ብቻውን ነበር። የፋጡማ ለስላሳ ገላ አቅፎ፣ የሴትነት ወዟን ተቃብቶ ከእሷ ጋር ማደሩን ፈጽሞ አልጠላውም። የሷን እንጃ እንጂ እሱ እሷን በጣም ይወዳታል። ይጨነቅላታል። ግን ከሁሉ በልጦ ሰሞኑን ልቡን ወትውቶ አይምሮውን ያስጨነቀው አንድ ነገር አለ። አዎ ድርሰቱ ነው።

የተዋጣለት ደራሲ ባይሆንም እንደ ነገሩ የሮዚን የፊልም ታሪክ (Dreh-buch) ጽፎ አዘጋጅቷል። ግን ገና አልጨረሰውም። በመሐከሉ የፋጡማ ፍቅር ገብቶ አጨናግፎታል። ሰሞኑን እርግፍ አርጐ የተወውን ጽሑፍ ለመቀጠል ዛሬ ቆርጦ ተነስቷል።

ጆኒ ምክንያቱ ባልታወቀ ምክንያት ብዙ ጊዜ የሆነ ነገር ጀምር መጨረስ አይሆንለትም። ምስጢሩ ምን ይሆን? ክፉ ዓይነ ጥላ አለበት። ሥራውን ደክሞ እንዳገባደደ ሳይፈጽመው የሆነ እንከን ያጋጥመዋል። ደግሞ ደጋግሞ ቢሞክርም ድካሙ ውጤት አግኝቶ ዓላማው ግቡን አይመታም። ይሄም ሁኔታ ለጊዜው ያናደው እንጂ ፈጽሞ ተስፋ አይቆርጥም። በዚሁ ምክንያት ሳያልቅ የሰነበተውን ድርሰት መልሶ አፈጠጠበት።

ጆኒ በበጋም ሆነ በክረምት በማናቸውም የወር መጀመሪያ እለት የታክሲ ሥራ መሥራት አይወድም። ብዙ ገንዘብ እንደሚያገኝበት ልቡ ቢያውቅም ከገንዘብ ይልቅ ሰላምና ጤንነቱን ማግኘት ይመርጣል። ሁካታና ግርግር፣ ቀልብ የሚገፍ ጩኸት መቅለብለብና ጥድፊያ የሰካራም ጠብና ግልምጫ በሚያዳልጥ መንገድ ታክሲ ይዞ ሩጫ ይጠላል። በኪኒን የተያዘ የስኳር በሽታ ስላለበት እንዲህ ያለው ሁኔታ ሕመሙን የሚያባብስበት እየመሰለው ልቡ ጠርጥሮ ይፈራል።

ጆኒ በዚሁ ምክንያትና የሮዚም ድርሰት ተጨምሮ በእለቱ አይሠራም። እረፍዱ ላይ ተነስቶ ያቀደውን ዓላማ ለመፈጸም ቆርጦ ወስኗል። ነጭ ወረቀት ዘርግቶ ቀለም ያረገዘ ብዕር ጨብጦ አንገቱን አቀርቅሮ ድርሰቱን ይጽፋል። እንደ ቸኮለ ሀሳብ አልመጣለት ብሎ አምጦ ይታገላል። የጻፈውን መልሶ እያነበበ ሳይጥመው ደልዞ ሲጥመው አልፎ፣ ቅደም ተከተሉን ለዋውጦ ያስተካክላል። ሲደክመውና አይምሮው ሲጨነቅ ሙዚቃ ከፍቶ ይዝናናል።

«ጡቷ ያልጋተውን ላም ወተት እንዲወጣ ብሎ ማለብ ዘበት ነው» ብሎ ጥቂት እረፍት አድርጐ ቀስ በቀስ ሀሳብ ሲጠረቃቀምለት ተመልሶ ወደድርሰቱ ይሄዳል።

ምን ጊዜም ቢሆን ተሰጥኦና በቂ ችሎታ የሌለው ደራሲ የሥራው ፍሬ ድካም እንጂ ውጤት ያለው የኪነት ጥበብ እንዳልሆነ ልቡ እያወቀ ተስፋ ሳይቆርጥ ተጨንቆ ይጽፋል። ጊዜው ሮጦ መምሸቱ ጨርሶ አልታወቀውም። ድንገት ስልኩ ተደውሎ ባነነ። ጥልቅ ከሆነ የጽሑፍ



ባሕር ውስጥ መንጭቆ ያወጣውን ስልክ ተቆጥቶ አረገመው። በቅጽበት ደግሞ ልቡ ፋጡማን አስታውሶ በደስታ ስሜት አነሳው።

«ዮሐንስ ነኝ።»

«ሰላም ጆኒ ሥንታየሁ ነኝ።»

«ኦ ዶክተር እንደምነህ? ምነው ድምፅህ ጠፋ?»

«ሥራ በዝቶብኝ ነው ይቅርታ።»

«አውቃለሁ ከሥራህ ሌላ ፕሬዚዳንትነቱ ተጨምሮ ፋታ አይሰጥም። ከማዶ የደወለለት ዶክተር ሥንታየሁ የሚባል ኢትዮጵያዊ ወዳጁ ነበር። በከብት ሕክምና ተመርቆ ጀርመን ውስጥ የሆነ ከተማ ውስጥ እየኖረ ይሠራል።

ዶክተር ስንታየሁ በዚሁ በሚኖርበት ከተማ የኢትዮጵያኖች መገናኛ መሐበር ዋና ሊቀመንበር ነው። አንድ በቅርቡ ከኢትዮጵያ መጥቶ ስደተኝነት ጠይቆ ከባለቤቱ ጋር እዛው ከተማ ይኖራል። ከሀገሩ የተሰደደበትን ምክንያት አሟልቶ ቢጽፍም የጀርመን መንግሥት ጉዳዩን አይቶ ተቀባይነት አልሰጠውም። ከሀገር እንዲወጣ ደብዳቤ ደርሶት ይግባኝ ብሎ በጠበቃ ተከራክሮ አቃተው። እሱና የሕግ ባለቤቱ በፖሊስ ተይዘው ታሠሩ። ከትንሽ ጊዜ በኋላ ሚስቱ ተፈትታ እሱ እዛው ቀረ። አምስት ወር ታሥሮ ማቀቀ። በመጨረሻ ኑሮ አንገፍግፎት እስር ቤት እንዳለ እራሱን በራሱ ሰቅሎ ተገኘ። ሞቱ ለባለቤቱና ጀርመን ለሚገኙት ኢትዮጵያውያን ስደተኞች ሁሉ መራራ ሀዘን ፈጠረ። በእዚህ ዓይነት አይሁን እንጂ የስደት ኑሮ የመረራቸው ብዙ ኢትዮጵያኖች አልፎ አልፎ በየከተማው እራሳቸውን በየጊዜው እያጠፉ ሞተዋል። የባእድ ሀገር ኑሮ ያንገፈገፋቸው ብዙ ሰዎች አሉ።

ዶክተር ስንታየሁ ለጆኒ ስልክ የደወለው በሟቹ ቀብር ሥነሥርዓት ላይ እሱና ሌሎችም ኢትዮጵያኖች የሚችሉ ከሆነ እሥፍራው እንዲገኙ ነበር። የጀርመን መንግሥትም ሟቹን ያላግባብ አሥሮ ለዚህ ስላበቃው ኢትዮጵያውያን ስደተኞች ከፍተኛ ዲሞንስትሬሽን ቦን ከተማ እንደሚያደርጉ የዝግጅቱን ፕሮግራም አንድ ባንድ ለጆኒ ገልጦ ሁለቱም ተሰነባብተው ስልኩ ተዘጋ።

ጆኒ ድርሰቱን መጻፍ አቁሞ በነገሩ አዝኖ ተከዘ። ሁኔታውን ሌሎችም ኢትዮጵያኖች እንዲያውቁት በየቦታው ስልክ ደውሎ አስታወቀ።

ሮዚና ፋጡማ ክላውዝና እንድርያስ ሙራትና ሌሎችም የምሽቱ የታክሲ ሹፌሮች በእለቱ ገበያ በዝቶ እየተጣደፉ ከወዲያ ወዲህ ይሯሯጣሉ።

የዛሬው የሴንተራል ፉንክ ተናጋሪ ኡቮ ነው። ልዩ ልዩ የታክሲ መቆሚያ ስፍራዎችን እየጠራ በሩን ማለት የታክሲ አገልግሎት ሥራውን ለታክሲ ሹፌሮች እያደለ ይለፈልፋል። የሮላንድ የታክሲ ደንበኞች የስልክ ጥሪ በላይ በላዩ ተደራርቦ ይንቃጨላል። በአንድ ሰዓት ውስጥ ከሁለት መቶ የሚበልጡ ጥሪዎች ደርሰውታል። እለቱ ሐሙስ ቢሆንም ገበያው እንደ ዓርብና ቅዳሜ በርክቷል።

ከድር የሮላንድ የሴንተራል የሥራ ባልደረባ በእለቱ እረፍት ወስዶ በምሽት ብቻውን ይንቀዋለላል። እሱን የተካው ጀርመናዊ ሚካኤል ይባላል እንደሱ ቀልጣፋ ባይሆንም ድምጹ ይጣፍጣል። ከድር ከሙራት ጋር ቀጠሮ አድርገው አልተገናኙም። ሁለቱም የሮዚ ጠላቶች ናቸው። በሷ ላይ ተገናኝተው ሊዶልቱባት ያሰቡትን እቅድ አለ።

ሮዚ ከነዚህ ተንኮለኛ ሰዎች ብትጣላም የጠበቀና የመረረ ቂም የላትም። ሲውል ሲያድር እንዳውም ነገሩን ችላ ብላ እረስታቸዋለች። እነሱ ግን አልዘነጓትም። እርስ በእርሳቸው ተመካክረው ሌላም ሰው ጨምረው የሆነ አደጋ ሊፈጥሩባት የተንኮል ወጥመድ መረባቸውን ሊዘረጉባት አቅደዋል። እንዳውም ሙራት ሽጉጥ ገዝቶ በጉያው መያዝ ጀምሯል። ሮዚንና ክላውዝ የነሱ ተባባሪ የሆነውን ሌላም ሹፌር አብሮ በያዘው ሽጉጥ ለማዳበን ባይቆርጥም አስቧል። የሮዚ ፍቅር በቅናት ተለውጦ በሽቋል። ለዚሁም ሽጉጥ ብቻ ሳይሆን በተለይ ሮዚን ድምፅ በሌለው መሣሪያ ተጠግቶ ጠቅ አርጎ ወንጀሉ ሳየታወቅበት ለመጉዳት የኤድስ በሽተኛ ደም የተሞላበት መርፌም ጨምሮ ይዟል።

ሮዚ እንዳጋጣሚ ጥሩ የታክሲ አገልግሎት በር ደረሷት ሆላንድ ደርሶ መልስ ከሆነ ተሳፋሪ ጋር በብዙ ገንዘብ ተኮናተረች። ሂሳቧን በቅድሚያ ተረክባ የምትሄድበትን ቦታ ለሴንተራል አስታውቃ ከብሬመን ወጥታ ተፈተለከች።

ክላውዝ በዚህ ምሽት ሮዚ ከተማውን ለቃ መሄዷን በፉንክ ሰምቶ በመስጋት አዘነ። ፋጡማ ግን ክላውዝን ብቻውን ለማግኘት ጥሩ አጋጣሚ ስለሆነላት ደስ አላት።



የደራው የምሽቱ የታክሲ ገበያ ወደ እኩለ ለሊቱ ገደማ እየቀዘቀዘ ሄደ። ጥቂት የታክሲ ሹፌሮች እረፍት አድርገው በየምግብ ቤቱ ታጎሩ። ፋጡማ ክላውዝን ፍለጋ ከቦታ ቦታ መኪናዋን ይዛ ተሯሯጠች። በመጨረሻ የሆነ ቦታ አግኝታው ቤቷ የተዘጋጀ ምግብ ስላለ አብረው ሄደው እንዲበሉ ጋበዘችው። ክላውዝ አፍሮ ተግደረደረ። ከአሁን በፊት ሁለቱ እንዲገናኙ በስልክ ጥሪ ወትውታው አሻፈረኝ ብሏታል። ቢሆንም ተስፋ አልቆረጠችም። የሮዚም እርቆ መሄድ ጥሩ አጋጣሚ ስለሆነ ደግማ ደጋግማ በመለመን እሺ አሰኘችው። ሁለቱም ታክሲያቸውን ይዘው ፋጡማ ቤት ደረሱ። እቤት ገብተው ተፋጠጡ። በርግጥ የተዘጋጀ ምግብ አልነበረም። ፋጡማ ኮቷንና ሸሚዟን አውልቃ በካኔቴራ ብቻ ታየች። ክላውዝ የፈረጠሙ ጡቶቿን አይቶ ቋመጠ።

ፋጡማ ኪችን ገብታ እንቁላል ጠባብሳ አቀረበች። አብረው ተጎራርሰው በሉ። ሻይም ተፈልቶ ቀረበ። የፋጡማ ዓይኖች ተስለምልመው ክላውዝ ላይ ወደቁ። ፍላጎቷ ቢገባውም አቅፎ ለመሳም አልደፈረም። ሲጃራውን አውጥቶ ጋበዛት። ሁለቱም አጨሱ። ፋጡማ የሆነ ነገር ትዝ ብሏት ፍንጥር ብላ ጓዳ ገብታ ምናምን ይዛ መጣች። ሀሺሽ ነበር። አብረን እናጭስ ብላ ክላውዝን ጋበዘችው። የሲጋራውን ጥቅል ሰብራ ከአሽሹ ጋር ደባልቃ በሌላ ወረቀት እየጠቀለለች ክላውዝ በነገሩ ተገርሞ እንቢ አላት። እሷ ግን የጠቀለለችውን በሳት ለኩሳ ደጋግማ ማገችው። ሰውነቷ ተቅበጠበጠ። ዓይኖቿ ይበልጥ ፈጠጡ። ከጆኒ ደብቃ ሁሌ የምታደርገው ስለሆነ ሰውነቷ መርዙን ለምዶታል። ሙዚቃ ከፍታ ብቻዋን ደነሰች። ጠረጴዛውን እንደመወልወል አድርጋ አውቃም ይሁን ሳታውቅ የክላውዝን የሻይ ብርጭቆ ገፋ በማድረግ ጭኑ ሱሪ ላይ ደፋችው። ክላውዝ ደንግጦ ተነሳ። ፋጡማ ፎጣ አምጥታ ጭኑን እየዳበሰች ያንንም ጉዳይ እየነካካች ሻይ የፈሰሰበትን ቦታ ጠራረገችው። ክላውዝ ስሜቱን መቆጣጠር አቅቶት አቅፎ ሳማት። ሁለቱም ተያይዘው ወደመኝታ ክፍል ገቡ።

ጆኒ በዚህ ለሊት ደከመኝ ብሎ ሳይታክት የሮዚን ታሪክ ጠረጴዛ አቅፎ፣ አንገቱን አቀርቅሮ ይጽፋል።

ሙራትና ከድር በቀጠሮ ሰዓት ባይሆንም በዚሁ ምሽት ተገናኝተው በሮዚ ላይ ሰሞኑን ሊፈጽሙባት ያሰቡትን ተንኮል ተመካክረው ጨርሰዋል።

እንድርያስ የመኪና ግጭት ደርሶበታል። ጥፋቱ ግን የእሱ አልነበረም። የያዘው መንገድ ከግራም ከቀኝም ለሚመጣ ተሽከርካሪ ቅድሚያ የሚያሰጥ "Vorfahrt" ምልክት ያለው ነበር። ሳያስበው ከቀኝ በኩል ብቅ ብሎ የታክሲውን ቀኝ ጐን ገጭቶ ያጐበጠውን ሹፌር ተቆጥቶ ይጮሃል «ዓይን የለህም የትራፊክ ምልክቱን አታይም ቅድሚያው የኔ ነው» እያለ እየሰደበ ይጮኽበታል። ደግነቱ በግጭቱ የተጐዳ ሰው አልነበረም። ጥፋተኛው ሹፌር በግጭቱ ተደናግጦ ፈዟል። ምሽት ቢሆንም ያሉት እግረኛ መንገደኞች በአደጋው ስፍራ ተሰብስበው ሁኔታውን ይመለከታሉ። ከሴንተራል ጥሪ የደረሳቸው የትራፊክ ፖሊሶች እስፍራው ደርሰው ምርመራ ይዘዋል። የሁለቱንም የመንጃ ፍቃድና የመኪናው ባለንብረትነት ተቀብለው በፉንክ ከትራፊክ ጽሕፈት ቤት እያመሳከሩ ያጣራሉ። ግጭቱ ፎተግራፍ ተነሳ። አጥፊው ሹፌር በዋዛ አልተለቀቀም ሰክሮ እንደሆን ለማረጋገጥ ፖሊሶቹ የያዙትን መመርመሪያ ትንፋሹን እንዲሰጥ አቀረቡለት። የተባለው ታዞ አደረገ። ሹፌሩ ባይሰክርም ጠጥቷል። ጀርመን ውስጥ ጠጥቶ መንዳት ፈጽሞ ክልክል ነው። ደም ውስጥ ከ0.8 ፕሮሚል አልኮል የበለጠ ሰው የመንጃ ፍቃዱ ለተወሰነ ጊዜ ተንጥቆ ሌላም የገንዘብ ቅጣት ይከፍላል። ፖሊሶቹ እንድሪያስን አሰናብተው ጥፋት ያጠፋውን ሹፌር ይዘው ወደጣቢያ ሄዱ።

ፋጡማና ክላውዝ ያደረጉትን አድርገው ለሊቱ ሳይነጋ ሮዚም ከሆላንድ ሳትመለስ በየሥፍራቸው ተሰማርተዋል።

ማግሥቱ የሥራ ቀን በመሆኑ ገበያው ቀዝቅዟል። ሰዓቱ እየገሠገሠ ሄዶ ወደመንጋቱ ተቃርቧል። አንዳንድ የታክሲ ሹፌሮች በጊዜ ሥራ ጨርሰው ወደየቤታቸው ገብተዋል። ያቺ ለተወሰነ ጊዜ ጭቃ የነበረችው የብሬመን ከተማ አሁን የመነኩሴዎች መኖሪያ ፀጥ ያለች ገዳም መስላለች።

ሮዚ ባለችበት አካባቢ በረዶ ባይጥልም ዝናብ ይዘንባል። ሰፊው አገር አቋራጭ የመኪና አስፋልት አውራ ጐዳና (Autobahn) ግን በትራፊክ ብዛት አልተወጠረም። ሮዚ ከሆላንድ ተመልሳ ብሬመን ለመድረስ የቀራት ጥቂት ኪሎሜትሮች ነበሩ። በዝናቡ ምክንያት ፍጥነቷ እንደወትሮ አልነበረም። የሆነ ቦታ እንዳለች ድንገት የመኪናዋ የመስታወት መጥረጊያ (Schelbenwesche) ተበላሽቶ ቆመ። ሮዚ



ደንግጣ መኪናዋን ወደዳር አቆመችው። የማስጠንቀቂያ መብራቷን ለኩሳ የመኪናዋን የሞተር ክዳን ከፍታ ውስጡን ተመለከተች። ተሳፋሪው ሰው ስለቴክኒክ የሚያውቀው ባይኖርም ከመኪናው ወጥቶ አጠገቧ ቆሟል። ዝናብ ስለመታው ተመልሶ መኪና ውስጥ ገባ። ሮዚ ከሞተሩ በስተቀኝ ትንሽ ሳጥን ተመለከተች። ደስ ብሏት ከፈተችው አዎ እውስጡ ያለው የመኪናዋ ዚሽሩንግ (ኮንታቶሪ) ነበሩ አንዱ ተቃጥሏል። ለተጠባባቂ የተቀመጠውን ነቅላ የተበላሸውን ጥላ አያያዘችው። የመኪናዋ የመስታወት መጥረጊያ ተንቀሳቅሶ መሥራት ጀመረ። ቆሞ የመሰላት ልቧ ድው ድው እያለ ጤና ተሰማት። ልብሷ በዝናብ እረጥቧል። ሮጣ መኪና ውስጥ ገብታ የቀራቸውን መንገድ ተያያዘችው። የመኪናዋን ማርሽ ከሦስተኛ አራተኛ ከአራተኛ አምስተኛ ለዋውጣ ሽው! ብላ ተፈተለከች።

የመኪናው የመስታወት መጥረጊያ እልህ እንደያዘው ፍጥነቱን ጨምሮ ከወዲህ ወዲያ ተወዛወዘ። ጥቂት እንደተጓዙ ዝናቡ አባርቶ ሰማዩ ወገገ። በረዥም ጉዞና በድንጋጤ የጨፈገገው የሮዚም ፊት እንደ ንጋቱ ፈገግታ ተከናነበ። ተሳፋሪው የውስጥ ጭንቀት ስላለበት ጭብጥ ብሎ ተኮማትሮ ተቀምጧል። በዚህ ሁኔታ የሆላንድን ግዛት አልፈው ሲነጋጋ ጀርመን የክልል ኬላ (ቦርድ) ደረሱ። የጠረፍ የፍተሻ ቃፊሮች ትንሽ ተመለካክተው እንዲያልፉ ለቀቋቸው።

ተሳፋሪው ደስ ብሎት ቦረቀ። ሮዚን «እድለኛ ሹፌር ነሽ» ብሎ ከልቡ አመሰገናት። ከሆላንድ በርካሽ ዋጋ ገዝቶ መኪናው ወንበር ሥር የደበቀው እፅ ኮከይን ሳይፈተሽ አልፈው ብሬመን ደረሱ። ሮዚ ለምን እንደሄደ ምን ይዞ እንደ መጣ ጨርሶ አታውቅም። ብቻ በሰላም ሄዳ በሰላም በመመለሷ ፈጣሪዋን አመስግና ሰውየውን የተባለው ሥፍራ አደረሰችው። ተሳፋሪው በሰጣት 800 DM ላይ ሌላ ጉርሻ 2 መቶ ማርክ አከለላት። ሹፌርነቷንም ድፍረቷንም ቁንጅናዋ ሳይቀር አድንቆ አወደሳት። ሆላንድ የሄደበትንም ምክንያት ሚስጢሩን ሳይደብቅ አጫወታት። ሮዚ በጉርሻው ብትደሰትም ሚስጢሩን ሰምታ ክው አለች። ግንባሯን አማተበች። ሰውየው ንግግሩንና አድናቆቱን ለእሷ እየገለጠ ዛሬ አብረው ያደረጉትን ሌላ ቀን ብቻዋን እንድታደርግለት ተማጥኖ በዚህም ብዙ ገንዘብ እንደምታገኝ ደፍሮ ነገራት።

ሮዚ «ጉመን በጤና የምሠራው ሥራ ይበቃኛል ከእሳቱ ወደረመጡ» ብላ እንቢ ብላው ሁለቱም በዚሁ ተለያዩ። አዎ ሮዚ ገና ጀርመን እንደ ገባች የመጀመሪያ ወዳጁ የሲሪላንካ ተወላጅ (Dealer) ነበር። ምስጢሩን ጨርሶ አታውቅም። ግን በላስቲክ የታጨቀ ገንዘብ ይዞ ይመጣል። እንደብሩ ብዛት ተካፍላ አልተጠቀመችበትም። እሱም ያሸሸውን ወደ ሀገሩ አሸሾ የሆነ ቀን ጥሎበት በፖሊሶች እጅ ከፍንጅ ተይዞ እሥር ቤት ገባ። እሷም ተመርምራ ነፃ ወጣች። ታዲያ ከዚያ ወዲያ ሮዚ እንዲህ ያለውን ሥራ መሥራት ቀርቶ የሚሠሩትንም ጠላቻቸው። «ለገንዘብ ብሎ እየባነኑ ነፍስን ሽጦ በሥጋት መኖር» ባይበላ እዛ ጥንቅር ብሎ ይቅር። እንዲህ ያለውን እኔ ልጅቷ አላደርገውም ብላ ለራሷ ምላ ተገዘተች።

ሮዚ ሥራ ጨርሳ ባዝል ስትደርስ ፆ ዘወትር በሹፌሮች ተሞልቶ በሲጋራ ጭስ ታፍኖ የነበረው ሰፈ አዳራሽ የጠራ አየር ውጦ ጭር ብሎ ጠበቃት። የሮላንድ የለሊት የፈረቃ ሹፌሮች ለቀኖቹ መኪናቸውን አስረክበው በየቤታቸው ገብተዋል። የሚወዳት ክላውዝ እንኳን እሷን አልጠበቃትም። የእለት ሂሳቧን ሳታደርግ ፈጥና እቤቱ ደውላ አጣችው። ስልኩ እየጠራ ባለማንሳቱ ነደዳት። «የት አድሮ የሆን?» ብላ ልቧ ተጠራጠረ። የቅናት ስሜት ወረራት። በግል መኪናዋ ቤቱ ለመሄድ ፈልጋ ይሉኝታ ያዛት። የለሊቱ ሥራ ሰውነቷን ቢያደካክማትም ቅናቷ ብርታት ሰጣት። ከልብ ትወደዋለች። ከእሷም ሌላ ማንንም ሴት እንደማይጠጋ ታምነዋለች። «ደክሞት ተኝቶ ይሆናል» ብላ እራሷን በራሷ አጽናንታ ቤቷ ገባች።

በእርግጥ ክላውዝ እቤቱ አልነበረም። ሥራ በጊዜ ጨርሶ ከፋጡማ ጋር ተያይዘው በድጋሚ ሄደዋል። ያደረገውን አድርጎ ቤቱ የገባው እረፋዱ ላይ ነበረ። እሱም የሮዚን ከሆላንድ በሰላም መመለስ ለማወቅና የሱንም ታማኝነት ለማረጋገጥ አስቦ ስልክ ደወለላት። ብዙ ጊዜ ጠርቶ የሚያነሳው አልነበረም። ሮዚ ደክሟት ለጥ ብላ ተኝታለች። ክላውዝ ልቡ ተጠራጥሮ ሰጋ። ፍቅር አይሉት ቅናት ብቻ ልቡ ተረብሾ ተጨነቀ። ሮዚ በቀላሉ የማትደፈር መሆኗን ገምቶ፣ ለእሱ ያላትን ታማኝነትና ፍቅር አመዛዝኖ ተረጋጋ። ግን በፋጡማ በመሸነፉ የሞራል ወቀሳ ተሰምቶት ባደረገው ተፀፅቶ እንቅልፍ እንቢ አለው። ፋጡማ ግን በአድራጎቷ ተደስታለች። ያላንዳች እፍረት ምሥጢሯንም ለመሸፋፈን ፈልጋ ለጀኒ ስልክ ደውላ የለሊቱን የሥራ ብዛት ገልጣ ለእሱም ያላትን ታማኝነትና ፍቅር ዋሽታ አጫወተችው። ሕይወት የሚስጢር ኑሮ እውነት የጉደላት አንዱ ሌላውን እራሱን ጨምሮ የሚሸነጋግልባት ከንቱ ዓለም። ሰላቢ።





# ክፍል አሥራ ሦስት

ወቅቱ ክረምት ቢሆንም አይበርድም። አልፎ አልፎ በአንዳንድ አካባቢ ይዘንባል። ማልደው የተሠማሩት የከተማው ጽዳት ሠራተኞች መኪናቸውን ይዘው መንገዱን እየፈተጉ ያጸዳሉ። በለሊት ተርከፍክፎ ያደረውን በረዶ እረግቶ እንዳያሟልጭ የሚረጩውን ኬሚካል በዋና ዋና ሰፈ ጎዳናዎች ላይ አልፎ አልፎ ይበትናሉ።

ወደ ት/ቤት የሚሄዱ ሕፃናቶች ቦርሳቸውን በጀርባቸው አንግተው ፊታቸውን በእስካርፍ ሸፋፍነው አንድ ላይ ሆነው ይጓዛሉ። የከተማው የሕዝብ የትራንስፖርት ተሽከርካሪዎች ሥራቸውን ጀምረዋል። ትንሽ ትልቁ አሮጊት ወጣቱ የማይታክተውን የኑሮ ግዴታ ለመወጣት ማልዶ ተነስቶ ከወዲያ ወዲህ ይባዝናል።

ወደ ሥራ የሚሄደው ሥራ፣ ወደ ንግድ የሚሄደው ገና መደብሩ ሳይከፈት ቀድሞ ተኮልኩሏል። የታመመ ሐኪም ቤት ባለጉዳይ ፍርድ ቤት በአጠቃላይ በልዩ ልዩ ዓላማዎች ሕዝቡ ተሰማርቶ ይታያል። የጀርመን ሕዝብ በጣም ታታሪ ሥራ ወዳድና ብልህ ነው። ሥንፍና አሉባልታና ውሸት ጨርሶ አይወድም።

ብዙ አውቶብሶች በሕዝብ ተሞልተው ቢታዩም ሰው እርስ በእርሱ ተቀራርቦ አያወራም። ችግሩን ይሁን ደስታውን ለሌላው ነግሮ አብሮ አይወያይም። የእግዜር ሰላምታ እንኳን የሚለዋወጠው በጣም ጥቂት ነው። አብዛኛውን ጋዜጣውን እፊቱ ለጉሞ አንዳች ሳይተነፍስ በዝምታ መጓዝ በጀርመን የተለመደ ባሕል ነው። ታዲያ ይህ ባሕላዊ ልማድ እንዲህ ሆኖ እያለ ታክሲ ውስጥ ሲገቡ ደፍረው የቆጥ የባጡን ለምን እንደሚለፈልፉ ጀኒ ሁሌ ይገርመዋል። ስካር ይሆን?

ይህ የዝምታ አጉል ልማድ በትራንስፖርት መስጫዎች ብቻ ሳይሆን በሌላም ቦታ የተከሰተ ነው።

የሠራተኞች ጽፈት ቤት ወይም የግል ዶክተር ሐኪም ቤት ብዙ ሰው ተሰብስቦ ተራ ሲጠብቅ እርስ በእርሱ ተቀራርቦ አይወያይም። አዳራሹ በሕዝብ ተሞልቶ ዝምታ የሰፈነበት ፍጹም ፀጥታ የዋጠው ምድረ በዳ ይመስላል። ትንሽ እንኳን ደፍረው ይህን አጉል ባሕል ጥሰው የሚነጋገሩ ቢኖሩ የውጪ ሀገር ሰዎች ናቸው።

በተለይ አፍሪቃውያኖች ሲገናኙ ሰላምታና ጭውውታቸው አይጣል ነው። ታዲያ ይህ ልማዳቸው ባይከፋም አጠገብ ላጠገብ አብረው ሆነው ልክ እንደ ደንቆሮ በመጮህ ስለሚነጋገሩ ነዋሪው ሕዝብ ይጠላቸዋል።

ሰዓቱ እረፍዶ፤ ማለዳው አልፎ፤ ቀትሩ ቀንነቱን ማስታወቅ ጀመረ። የብሬመን ትንሽ ከተማ በሕዝብ ተሞልታ ደመቀች። ልዩ ልዩ የንግድ መደብሮች ተከፍተው ሕዝቡ መገበያየት ቀጥሎ እቃ እያማረጡ ያን ወስዶ ያን ጥሎ በሥርዓት ይተረማመሳል።

የቀን የታክሲ ሹፌሮች መኪናቸውን ይዘው ከወዲያ ወዲህ ይቅለበለባሉ። ሌሎችም የሕዝብ ትራንስፖርት መስጫ ተሽከርካሪዎች በየፌርማታው ቶሎ ቶሎ በመምጣት ተኮልኩለዋል። ሕዝቡ ለመሳፈር አይገፈታተርም የሚወጡት ወጥተው ሲያልቁ በዝግታ ይሳፈራል።

በቅርቡ ፈተናውን አልፎ በሮላንድ ታክሲ ድርጅት ውስጥ የሚሠራው ኢትዮጵያዊ ደርቤ ፀጋው ታክሲውን ይዞ ተሳፋሪ ለማግኘት ይጣደፋል። ሥራውን በጣም ወዶታል። እንዳጋጣሚም ይሁን በራሱ ጥረት በእለት በእለቱ የሚያገባው ገቢ ከነባር የቀን ሹፌሮች በጣም የተሻለ ነው። ከሴንተራል ብዙ ጊዜ የሚሰጠውን የታክሲ አገልግሎት በሮች እየተቀበለ ከወዲያ ወዲህ ይከንፋል። አንዳንዴም ከብሬመን ውጪ እቃ ይዞ እንዲሄድ እየታዘዘ ሳይዘገይ ፈጥኖ ደርሶ ይመጣል።

ደርቤን በዚህ ቀልጣፋ አገልግሎቱ ሌሎች የቀን ታክሲ ሹፌሮች ቀንተው ቢጠሉትም የድርጅቱ ኃላፊ ባለንብረት አቶ ሀሮልድ ይወዱታል።

ደርቤ ባለትዳር ነው። ሚስቱ ኢትዮጵያዊት የሆነች ቆንጆ ልጅ ናት። ፍቅራቸው የሞቀ ቤታቸው የደራ ነው። የቀኑ ሥራ ከለሊቱ ፈረቃ የተሻለ ቢሆንም ይቺን ቆንጂዬ ነፍሰ ጡር ሚስቱን በለሊት ለብቻዋ ትቶ



ከነ ጆኒና ሮዚ ጋር ሆኖ መሥራቱን ጨርሶ አልወደደውም። በገቢም በኩል ከእነሱ ይበልጥ እንጂ አያንስም። ለፉክክር ሳይሆን ለቤቱ ፍቅር ያደላል።

ደርቤ የዋዛ ሰው አይደለም። ለሥራው የሚጠቅሙትን ሰዎች ያውቃል። በተለይ ሴንተራል የቀን ፈረቃ የሚሠሩትን የፉንክ ተናጋሪዎች ለመወዳጀት ብዙ ጊዜ አልፈጀበትም። ብስኩትና ኬክ ሌላም ፍራፍሬ እየገዛ አልፎ አልፎ ሴንተራል ቢሮ ሄዶ ያበረክታል። በየመጠጥ ቤቶችም የሚከፋፈለውን የምንዛሬ ገንዘቦችን በኖት ለውጦ ይይዛል። ለድርጅቱ ጥሩ ስም ይጥራል። ሥራ የሚጀምረውም ከሁሉም ሹፌሮች በፊት ነው። በመሐከሉ እንኳን እንደሌሎቹ እረፍት አያደርግም። ሙያውን ሲጀምርም ሆነ ሲጨርስ ታክሲውን እንደ ነገሩ ሳይሆን በደንብ አድርጎ አጥቦና እንደመስተዋት ይወለውላል። የወረት ካልሆነ ይህ ትጋቱ በድርጅት ውስጥ ጥሩ ስምና ምስጋና የሚያሰጠው ሆኗል።

ደርቤ የእለት ቀልጣፋ አገልግሎቱን አከናውኖ እረፋዱ ላይ ቦርሳው ጠርቀምቀም ብሏል። ሆዱ ጉድሎ ቢርበውም ለከርስ ተብሎ የሚጠፋው ጊዜ ይቆጨዋል። በዚህም መኪናውን ኢድል ቫይስ (Edlweiss) የታክሲዎች ማቆሚያ ስፍራ አሰልፎ ተራውን ይጠብቃል። ሚስቱ እንዳስለመዳት ለእራት የሚሆነውን ልዩ ልዩ ምግቦች በደንብ አዘጋጅታለች።

ቆንጂት የደርቤ ባለቤት ናት። በቅርቡ ከሀገር ቤት ስለመጣች የጀርመንን ኑሮ ገና አለመደችውም። እቃው ያማረ ቤቱ የተሟላ ቢሆንም ትፈራለች። ባሏ ከሌለ ብቸኝነት ይሰማታል። ቋንቋው ባይገባትም ሬዲዮኑንም ቲቪውንም ከፍታ ሲንጫጫ መስማት ያዝናናታል። ያረገዘ ሆዷን እየዳበሰች በቶሎ ወልዳ ከልጇ ጋር የምትጫወትበትን ቀን ትናፍቃለች። ቤቱን አፅድታ ምግብ አዘጋጅታ ብትጨርስም ጊዜው ዓመት መስሎ ይረዝምባታል። የምታደርገው ሲቸግራት የለበሰችውን የእርጉዝ ልብስ አውልቃ ሌላ ትለብሳለች። ደርቤ በቅርቡ ብዙ ልብሶችና የወርቅ ጌጣ ጌጦች ገዝቶላታል። ታዲያ ቆንጂት ሥራ ስትፈታ አንዱን አውልቃ ሌላውን ትለብሳለች። መስታወት እየተመለከተች ብቻዋን ትስቃለች ትንሽ ተክዛ በሁኔታው ትገረማለች። «ልብስና ጌጥ ቢለዋወጥ ሌላ ተመልካች ከሌለው ምን ዋጋ አለው» ብላ መልሳ ትተክዛለች።

ቆንጂት አንዳንዴ ሀሳቧ መንጥቶ እርቆ ሀገር ቤት ይደርሳል። ኢትዮጵያ ያሉትን ጓደኞቿን ድሃ ጐረቤቶቿን አስታውሳ «አሁን ይሄን ያማረ ልብሶች ለብሼ የወርቅ ጌጣ ጌጦቼን አድርጌ ቢያዩኝ እንዴት ይገረሙ» ትላለች። «እኔስ ከነሱ በልጬ በማህላቸው ሳልፍ አይጣል የሚሰማኝ ደስታ» ብላ በስሜት ተኩራራች።

በእርግጥ ለሴት ልጅ አንዱ ደስታዋ ሌላው የለበሰችውንና ያደረገችውን ጌጣ ጌጥ አይቶ አድናቆቱን ሲገልጽ ነው። ታዲያ ቆንጂት ከባሏ ከደርቤ በስተቀር ሌላ የኔ የምትለው ሰው ባጠገቧ ባለመኖሩ ታዝናለች። የባሏ መምጫ ባይደርስም ቤቱ ስለሰለቻት አላፊ አግዳሚውን ሰው ለማየት ወደመስኮቱ ተጠግታ የደጁን ሁኔታ በትካዜ ፊዛ ተመለከተች።



ደርቤ ታክሲውን ይዞ ተራውን ጠብቆ የሁለተኛውን የታክሲ ቦታ ረድፍ ይዟል። የመጀመሪያው የታክሲ ሹፌር የሮላንድ ድርጅት ተቀጣሪ የሥራ ባልደረባው ነው። ዜግነቱ የውጪ ነው። በሥራው የቆየ ቢሆንም እንደ ደርቤ ንቁና ቀልጣፋ አይደለም።

ከሴንተራል ለዚሁ ሰው የታክሲ አገልግሎት በር ደረሰው። የሆነ እቃ ገዝቶ ለደንበኛ ማድረስ ነበር ትእዛዙ።

አንድ የታክሲ ደንበኛ አሻንጉሊት ተገዝቶ እቤቱ እንዲመጣለት ስለጠየቀ ገዝተህ እቤቱ ውሰድለት! የሚል ትእዛዝ ነበር ከደርቤ ፊት ያለው የታክሲ ሹፌር የደረሰው በር። የታክሲ አገልግሎት ሥራ

አልገባኝም። ምን ዓይነት አሻንጉሊት ትልቅ ትንሽ ለስንት ዓመት ሕፃን የሚሆን ነው? አሻንጉሊቱ።

ለሕፃን የሚሆን አይደለም የላስቲክ አሻንጉሊት ነው

ምንድነው የላስቲክ አሻንጉሊት ብሎ ነገር?

አሻንጉሊቱ ለወሲብ ሥራ የሚሆን ለትልልቅ ሰዎች መዳሪያ የሚያገለግል ነው ከአካባቢው ከሴክስ ሱቅ መግዛት ትችላለህ።



አ አሁን የተባለው ገባኝ ግን በዚህ ጉዳይ ብዙ እውቅ ስለሌለኝ ትእዛዙን ለሌላ ሹፌር እባክህ ስጥልኝ።

ማነው ፍቃደኛ ይህን ትዕዛዝ የሚፈጽም! ሲባል።

ደርቤ ተቀላጥፎ በአወንታ መልስ ሰጠ።

«እኔ እታዘዛለሁ። ምን ዓይነት አሻንጉሊት? ወፍራም ቀጭን ጥቁር ወይስ ነጭ ገላ? ወርቃማ ወይስ ቀይ ፀጉር ያላት? ዋጋውስ እስከስንት የሚፈጅ?» ብሎ ጠየቀ።

የሆነው ይሁን አንተን ደስ ያለህን ግዛ ብቻ ዋጋው ከመቶ ማርክ እንዳይበልጥ።

እሺ አደርጋለሁ። ግን ፍላጐት ባልከው አልስማማም። ለኔ ጣም ያለው አሻንጉሊት ሳይሆን ሰብአዊ ሰው ነው።

የምትለው ይገባኛል ጠያቂው ሰው ምናልባት የኤድስን በሽታ ፈርቶ የሆናል። ጭቅጭቁን ትተህ ደንበኛው ስለቸኮለ የተባለውን አድርስለት። ደርቤ ቦታውን ጠይቆ የተባለውን አሻንጉሊት ለተባለው ሰው ገዝቶ አደረሰለት።

እለቱ በዚህ ዓይነት ውሎ ቀኑ መሸ። የቀን የፈረቃ የታክሲ ሹፌሮች ሥራቸውን ጨርሰው መኪናቸውን ይዘው ባዝል ተኮለኮሉ።



ሮዚ ቁእንቅልፏ የነቃችው በግድ ነበር። አጠገቧ ምልታ ያስቀመጠችውን ሰዓት እንኳን በደንብ አልሰማችውም። በደመነፍሷ ተገላብጣ ጩኸቱን ሳታስበው አጥፍታ ተመልሳ ተኝታ ነበር። አሁን የቀሰቀሳት የስልኳ ጩኸት ነው። ስልኩ አጠገቧ ስለሌለ የግድ ን

ተንጠራርታ ተነስታ ሮጣ አነሳችው። የደወለላት ወዳጇ ክላውዝ ነበረ። ታማኝነቱንና ፍቅሩን ለማረጋገጥ ከትላንት ጀምሮ ስልክ መደወሉንና እሷን ማጣቱን ነገራት። ሁለቱም የማይጠገብ የፍቅር ውይይታቸውን በረዥሙ ተወያይተው ስልኮቻቸውን ዘጉት። በእለቱ ክላውዝ ስለማይሠራ ሮዚ ትንሽ ቅር አላት። እሷም እንደሱ እረፍት ወስዳ አብሮ መሆኑን ልቧ ተመኘ። ግን የማይቻል ነው በእለቱ መሥራት አለባት። የሮላድ የታክሲ ድርጅት ድንገተኛ ሕመም ካልሆነ ለሥራ ተመዝግቦ በሆነ ባልሆነ ምክንያት መቅረት ያስወቅሳል። በዚህ ላይ ለድርጅቱ ያላትን ጥሩ ዝናና ተወዳጅነት የምታጣ ስለመሰላት በቶሎ ተጣጥባ ፈጥና ወደ ሥራዋ ሄደች። ደርቤንም ባዝል አግኝታው በአጭር ጊዜ ውስጥ ያተረፈውን ዝና አድንቃ ነገረችው። ደርቤ የታክሲ ሥራውን ከጀመረ ሰንብቶ ብዙ ጊዜ ሮዚ በሩቅ አይታ ሰላም እንኳን ሳትለው እንዳላየ ሆና በማለፏ ልቡ ቅር ብሎት ተጨንቆ ነበር። አሁን ግን ተጠግታ በአጭር ጊዜ ያተረፈውን ዝና ስትገልጽለት ደስ ብሎት ተኩራራ። በርግጥ ሮዚ ይህን ያደረገችው አብሮ ለመኖር ያላት ዲፕሎማሲ እንጂ እሱን ወዳው ወይም ትጋቱን አድንቃ አልነበረም። በርግጥ ደርቤም ቢሆን ይህን የታክሲ ሙያ ከመጀመሩ በፊት፣ አስቀይሟታል። የሆነ ምሽት የሆነ ቡና ቤት ታክሲ አስጠርቶ እንዳጋጣሚ እሷ ትመጣለች በሞቅታ ስሜት ሰላም ሳይላት አመናጭቆ አባሯታል። ታዲያ ሮዚ «የወጋ ቢረሳ የተወጋ አይረሳም» እንደሚባለው ሆኖባት በዛ መጥፎ አድራጐቱ አሁንም ቂም ይዛበታለች። ፊቷ ግን ፈገግ ብሎ «መልካም ምሽት ይሁንልህ» ብላ ተሰናበተችው።

ጀኒም በእለቱ ሥራ ገብቷል። ታክሲውን ፈርፌልድ አቁሞ ተራውን ይጠብቃል። የሆነ ደብዳቤ በእጁ ይዞ ያነባል። በነገሩ ባይቆጭም በጻፈለት ሰው ድክመት ከልቡ አዝኗል።

ሮዚ መኪናዋን እያሽከረከረች ድንጋይ በር ቀበሌ ፈርፌልድ ደረሰች። ከሩቅ ጀኒን አይታ ደስ አላት። ታክሲዋን ከእሱ ቀጥላ በማስለፍ አቁማ ዘላ ጀኒ መኪና ውስጥ ገብታ ቂጥ አለች። እንደ ወትሮ የሞቀ ሰላምታ አልተሰጣጡም። ሮዚ ግራ ገብቷት።



«ምን ሆንክ ጀኒ ምን አበሳጨህ?»

«አልተበሳጨሁም ግን ነገሩ አሳፍሮና አሳዝኖኝ ነው»

«የምን ነገር አልገባኝም»

«የዘመመ የስድብ ደብዳቤ ነዋ»

«ማነው ዘመመ? ምንድነው ደብዳቤ የምትለው?»

ኢትዮጵያዊ አሁን ሀገር ቀይሮ ፍራንክፈርት ሄዷል።

«አ! አወቅሁት ዘመመ ዘውዱን ነው የምትለኝ እሱንስ እንኳን የብሬመን አድባር ከዚህ ነቀለችው። ነግሬህ አይደል የኔን ታሪክ አበላሽቶ ብዙ ችግር የፈጠረብኝ ሰው ነው።»

«አውቀሽዋል ያባቱንም ስም አልረሳሽውም።»

«እሱን እስከምሞት ድረስ የማረሳው ጠላቴ ነው ግን ያልገባኝ ከአንተ ጋር በምን ተገናኛችሁ?»

«ባለፈው ወር ይሄው ሰው ቦን በሚታተመው በተስፋ መጽሔት ላይ የሆነ ነገር ጽፎ በሀገር ፍቅር ስሜት ተቆርቁሬ እርማትና ገንቢ ሂስ በማድረጌ ተቆጥቶ ነው»

«አንተ ደግሞ ሰው ተገኘ ብለህ ሙትት ብለሃል። ጉረኛ ሰው ውዳሴን እንጂ ምን ጊዜም ሀቅን አይቀበልም ጅብ በማያውቁት ሀገር ቁርበት አንጥፉልኝ ይላል አንተ እሱን እያወቅኸው ችላ ማለት ነበረብህ።»

ሁለቱም መኪናቸውን ወደ ፊት አጠጋግተው ከቆሙ በኋላ ተመልሰው ውይይታቸውን ቀጠሉ።

«ችላ ማለት ነበረብህ?» ይህማ አይሆንም ሮዚ። ቆማጣን ቆማጣ ካላሉት...ይባል የለ ስህተትን በእንጭጩ ማረም ነው ካለዛ ተስፋፍቶ ብዙ ሰው ይጐዳል»

«እሱስ እውነት ሂስን ከማያውቅ ደደብ ሰው መከራከሩ ማለቴ ነው ለመሆኑ ምንድነው የጻፈልህ?»

«ምን ይጽፍልኛል ስድብ ነዋ ድሮስ ከዝንብ መቼ ማር ይገኛል?»

«ያልገባኝ መልሱን በግልጽ በዛው መጽሔት ላይ ከማውጣት ተቆጥቦ ለምን በግል አድራሻህ እንደጻፈልህ ነው?»



ጫማው የወለቀበት ሰካራም

«እኔንም ያሳዘነኝ ይሄው ነው እንጂ ፋይዳ ለሌለው ስድቡ አልቆጨኝም። ነገሩ ድንቁርናና የወለደው እልህ ነው። ጠብ ያለሽ በዳቦ እንደሚባለው አይነት።»

ሮዚ «በአድራሻው ለጻፈልህ ስድብ ምላሹን ጻፍለት።»

«መቼ አድራሻው በግልጽ ይታወቃል ብለሽ ነው። እንደ አውሬ ተሸሽጐ ነው የሚኖረው። በስልክ መጽሐፍ ላይ እንኳ ስሙ እንዳይወጣ በስውር እንዲያዝ አድርጓል።»

«ይህ ሰው እንዲህ ካደረገ የሚያደርገው ወይም ያደረገው ክፉ ሥራ ቢኖር ነው እንጂ ሰላም በሰፈነበት ዲሞክራሲ ባለበት ሀገር ተቀምጦ መሸሸግ አልነበረበትም።»

«ትክክል ነሽ ሮዚ! የበግ ለምድ የለበሰ ተኩላ ወይም ቀንድ የሌለው ሰይጣን ይሆናል። ማን ያውቃል» ብሎ ጆኒ እንደመለሰላት ከፉንክ በር ደርሶት ሄደ።

ጊዜው እየመሸ ሄዶ እኩለሌሊት ተጠጋ። የታክሲ ሥራ ቢደራም ባለፈው ቀን ጆኒ በደንብ ስላልተኛ ደካክሟል። ለፋጡማ ሥራ ስትጨርስ እቤት እንድትመጣ ነግሮ ታክሲውን ይዞ ወደባዝል ሲገሠግሥ የሆነ ተሣፋሪ ድንገት አስቁሞት ይዞት ሄደ። የተባለው ቦታ አድርሶት ሰውየው የታክሲውን ገንዘብ አልከፍልም ብሎ ተጨቃጨቁ። ጆኒ «እንዴት ገንዘብ ሳይኖርህ ታክሲ ላይ ትወጣለህ?» «ሰክሬአለሁ አላውቅም» ሲለው ጆኒ በንዴት የሰውየውን ቀኝ እጅ ጠምዝዞ ሲይዘው መሬት ወድቆ ዘጭ አለ። ጆኒ ገንዘብ ለማግኘት ኪሱን ቢፈትሽ ምንም ነገር አጣ። እፉ ሸተተው። ወደ ታች ጐንበስ ብሎ ለወደፊቱ መቀጣጫ እንዲሆን በዘዴ ጫማዎቹን አስወልቆ ተቀብሎ ወዲያ ማዶ አሻግሮ ወረወረው። ሰካራሙ እሪ ብሎ ጮኸ በባዶ እግሩ መረማመድ አቅቶት እየተርበተበተ ወድቆ ሲነሳ እዛው ትቶት ታክሲውን ባዝል አድርሶ ሥራውን ያለወትሮ በጊዜ ጨርሶ ቤቱ ገባ።

አሁንም የምሽቱ የታክሲ ገበያ የደራ ነው። ግን ሮዚ ሰውነቷ ቀፏታል። ሆዷ ባር ባር እያለ ተጨነቀች። ክላውዝ በአለቱ ባለመሥራቱ



ጆኒም ቢሆን ያለወትሮው ገና በጊዜ ሥራ ማቆሙ ይሁን በሌላ እንደ ወትሮ ደስ የሚል ስሜት የላትም። ሲጋራ ደጋግማ ማጨሷ አፏን አመረረው እንጂ መጥፎ ስሜቷን ተከላክሎ ስላልፈወሰላት ግማሹን አጭሳ ወዲያ አሽቀንጥራ ጣለችው።

ሮዚ ሰሞኑን ሀገር ቤት እናቷ ጋ ስልክ ባለመደወሏ ስጋቷ ከእሷ አልፎ ኢትዮጵያ ኮበለለ። «እማዬ ምን ነክቷት ይሆን? አባዬ እንኳን አያመውም። ውይ ቅድስ ገብርኤልዩ ብቻ ክፉ አታሰማኝ ከእሷ ከማዩ በፊት እኔን አስቀድመኝ አበስኩ ገበርኩ» ብላ ግንባሯን አማተበች። ዓይኖቿ እንባ አዘሉ። «ምን ነክቶኝ ነው ሆዴ እንደዚህ የባባው? አሁን ደግሞ እንዳልደውል አያመችም በለሊት ማስደንገጥ ነው። ቆይ ሥራ ስጨርስ» ብላ ሰዓቷን ተመለከተች። እኩለሌሊት ቢያልፍም እስከሚነጋ ያላት አጭር ጊዜ ዓመት መስሎ ታያት። ሲጋራዋን ለኩሳ መኪናዋን ወደፊት አስጠጋች። ያለችው ሽታየንቶር ፌርፌልድ ነበር። ይሄኛውን በር ሠርታ ከፋጡማ ጋር እራት ለመብላት በፉንክ ኪስሜት ምግብ ቤት ለመገናኘት ተቀጣጥረዋል። እስካሁን ምንም ባትበላም አራባትም። ግን ቀጠሮ ያደረገችው ለምግቡ ሳይሆን እረፍቱ ከሰው ጋር ማውራቱ የውስጥ ጭንቀቷን የሚቀንስላት ስለመሰላት ብቻ ነው። የሦስተኛ እረድፍ ቦታ ባትይዝ ተሳፋሪ መጠበቁ ፉንክ ማዳመጡ ሰልችቷት ነበር። ሰዓቷን ደግማ ተመለከተችው እንዳሰበችው ገፍቶ አልሄደላትም። የእጇ ሰዓት የተበላሸ መስሏት መኪና ውስጥ ካለው ሰዓት ጋር አስተያየችው። ያው ናቸው ጥቅ! ጥቅ! እያሉ የምሽቱን ጊዜ አስተካክለው ወለም ዘለም ሳይሉ ያመለክታሉ። ልቧ ግን እንደ ሰዓቶቹ አልሆነም። ቸኩሎ ድው! ድው! ይላል። ምክንያት የሌለው ድለቃ ገረማት።

ሮዚ «የፈሩት ይደርሳል የጠሉት የወርሳል» የሚባለው ሆኖባት ሞገሥ የሚባለው አንድ የሰከረ ኢትዮጵያዊ ስደተኛ እየተንገዳገደ መጥቶ አጠገቧ በቀኝ በኩል ቆመ። ሰላምታ ተለዋውጠው ጆኒን የት እንደሚያገኘው ጠየቃት።

«ጆኒ ሥራ ጨርሶ ቤቱ ሄዷል። ለምን ነበር?» አለችው።

«ገንዘብ ቸግሮኝ እንዲያበድረኝ ነበር»

«ከአሁን በፊት የስጠህን መልሰህለታል?»

«በሁለታችን ጉዳይ አንቺን ምን አገባሽ? ይልቅ ውትወታውን ትተሽ አንቺ ካለሽ አበድሪኝ ነገ እከፍልሻለሁ ጥቂት ገንዘብ ነው።»

«ይቅርታ ሞገሥ እኔ የለኝም ተወኝ ሥራዬን ልሥራበት።» «የምን የለኝም ነው ሴት ተቀን እየሠራሽ ለኔ ለወንድምሽ ያልሆነ ለማን ሊሆን ነው?»

«አንተስ ከመለመን ለምን እንደኔ አትሠራም?»

«እንዳንቺ የፈረንጅ አሽከር መሆን ይቅርብኝ ወላጆቼን ባታውቂያቸው ነው እንዳንቺ ያሉትን...»

«ምን? ምን ልትል ነው ጨርሰው ጨምላቃ ሰካራም እጅ እግር እያለህ ወላጆቹ ቅብጥርሶ ከማለት አትሠራም እዛ ከለማኞች ጋር ቸርነት ከመሰለፍ? ስነፍ ለማኝ!»

«እኔ ለማኝ አይደለሁም ለማኝ አንቺ ነሽ እንዳንቺ ሴት ብሆን ኖሮ ፎቅ ቤት እሠራ ነበር ሴትነቱን አላወቅሽበትም»

«ደደብ ሽርሙጥና ባንተ ቤት ክብር ነው ሰካራም ሀገር አሰዳቢ ሂድ ከዚህ» ብላ እንደ ሐጐስ በጥፊ ሳይመታት መስታወቷን ጥርቅም አርጋ ዘግታ ሞተሯን አስነስታ ከቦታው ተፈተለከች።

ሞገሥ ባለበት ሆኖ እየዛተ! ሲፎክር የሆነ ታክሲ ነጂ ከመኪና ውስጥ ወጥቶ «እዚህ አትጩህ!» ብሎ በቁጣ ከሥፍራው እንዲርቅ አደረገው።

ሮዚ ከቦታው እርቃ ከሄደች በኋላ «ለካስ ሰውነቴን የቀፈፈው ለዚህ ነው» ብላ ከአደረባት ሥጋት በጥቂቱ ተዝናናች። ያቺ እናትዬ «ሰውን ሰው መውደዱ መች ይከፋ ነበር ያቃጥል ያንገበግብ አለው እንጂ ነገር» ያለችው ትዝ ብሏት በሀገሯ ልጆች ተቆጨች። «ትግሬው ቢሉት አማራ ሁሉም አበሻ አንድ ናቸው ከዛ አጋሜ ተገላገልኩ ስለ የዚህ ደግሞ መጨመር ሰው ሠርቶ ቢሻሻል የማይወዱ እኔስ ለነሱ ብዬ የት ልግባ? ሀገሩን ለቅቄ ብመጣ እዚህም እየተከታተሉ አላስቀምጥ አላሠራ ወይ ጣጣ ይሄ የስደት ኑሮ ስንቱን አሳየኝ» ብላ በኑሮዋ ተማራ ተንገሸገሸች። ሰውነቷ በረድ ብሎ ሲረጋጋ መኪናዋን የሆነ ጥግ ቦታ አቁማ እራቷን ለመብላት ኪስሜት ምግብ ቤት ዘው ብላ ገባች። ፋጡማ ቀደም ብላ



ለራሷ ምግብ አዛ ብቻዋን ስትበላ አገኘቻት። ሰላምታ ተለዋውጠው ተፋፈሩ። ሮዚ ምግብ ሳይሆን የሆነ ኬክ ብጤ አዛ ፋጡማ ፊት ለፊት ተቀመጠች። ፋጡማ እንደ ወትሮ ሆና አልታየቻትም። ቀና ብላ የሮዚን ገጽታ ማየት ተሳናት። ምግቡ አልቆ አይኖቿ ባዶ ሰሀን ላይ ተተከሉ። ወሬያቸው ስለዛሬው ገበያ ሳይሆን ስለትላንቱ ምሽት ነበር። ይህን የጀመረችው ሮዚ ስለነበረች የዛሬን ትታ ያለፈውን የትላንቱን በማውራቷ ከክላውዝ ጋር ያደረገችውን ጉድ ያወቀችባት ይመስል ልቧ ፈርቶ አፏ መናገር ተሳነው። ዓይኖቿም እሷን መመልከት ጨርሶ አቃተው መቁነጥነጥ አበዛች። ሲጃራዋን ለኩሳ እየማገች የትላንቱን ወሬ ወደዛሬ ለመለወጥ እየጣረች አፏ ተንተባተበ። ሮዚ ፋጡማ ሀሽሽ እንደምታጨስ ስለምታውቅ ያ ነገር ጕሉባት ይሆናል ብላ በየዋህነት ሁኔታዋን ገምታ አዘነች። ብዙም ቁም ነገር ሳየጨዋወቱ ሂሳባቸውን ከፍለው ከምግብ ቤቱ ወጡ።

ጆኒ እቤት እንደገባ በቶሎ አልተኛም። ሰውነቱ ቢደክምም እንቅልፍ እንቢ ስላለው የሮዚን ድርሰት ያነባል። ድንገት የቤቱ ስልክ ተደውሎ በድንጋጤ ቃና «ዮሐንስ ... ነኝ አሎ» አለ።

«በላቸው ነኝ ቀሰቀስኩህ እንዴ? ምነው ትንፋሽህ ተቆራረጠ?»

«አ! ኢንጂነር በላቸው እንደምነህ ፈጽሞ አልቀሰቀስከኝም ገና ከሥራ መግባቴ ነው»

«ኢንጂነሩን ትተህ በላቸው በለኝ ሁሌ ስነግርህ አትሰማኝም» አለው መአረጉን በትምህርት ትጋቱ ቢያገኘውም አባባሉን ወዶ በይሉኝታ ይዞት ተግደርድሮ።

«በል እንዳልክ ኢንጂነሩን ከጠላህ ልጅ በላቸው እልሃለሁ»

«ልጅ» የሚለውንም አስወግደው ጡረታ የወጣ ሹመት አልፈልግም። ይልቅ አሁን የደወልኩልህ ነገ እቤቴ መጥተህ እራት እንድትበላ ነው።

«ምን ተገኘ እራት የሚያስጋብዝ?»

«እናት»

«የምን እናት አልገባኝም»

«ወላጅ እናቴ ከኢትዮጵያ ትላንት መጥታለች። እንድንቃመስ ብላ እንጀራ ብጤ አምጥታለችና ለዛችም ለሮዚ ነግረሃት አብራችሁ ብትመጡ ደስ ይለኛል»

«እንኳን ደስ ያለህ ወንድሜ ምነው ትላንት ብትነግረኝ። እኔም ሆንኩ ሮዚ ሄደን እንቀበላቸው ነበር።»

«ሥራ ማስፈታት አልፈለግሁም እሷም ግር ግር አትወድም።» «በል ደግ ስለግብዣው ከልብ አመሰግናለሁ ለሮዚም ነግሬ አብረን እንመጣለን» ብሎ ስልኩን ዘጋው። ጆኒ በዚህ ወቅት ዶክተር ስንታየሁ የነገረውን መርዶ ነግሮ ደስታውን ሊያደፈርስበት አልፈለገም።

አዎ ለጆኒ ስልኩን የደወለለት ለረዥም ጊዜ ብሬመን ውስጥ የሚኖር ኢትዮጵያዊ ወዳጁ ኢንጂነር በላቸው አራምዴ ይባላል። ባለትዳር የሁለት ልጆች አባት ነው። ለረዥም ዓመታት አውሮፓ ውስጥ ቢቆይም የሀገሩን ቋንቋ ባህልና ታሪክ ያልዘነጋ ለኢትዮጵያ ነፃነትና አንድነት ከውጪ ሆኖ በግልና በድርጅት ውስጥ ሆኖ የሚታገል ብርቱ ዜጋ ነው። ለጠላው ሰው ወደ ኋላ የማይመለስ ቀንድ የሌለው ሰይጣን ነው።

ከአሁን ቀደም ጆኒ ከዚሁ ሰውዬ ጋራ በመመካከር ብሬመን ውስጥ የኢትዮጵያኖች መገናኛ መሐበር መሥርተው ነበር። ግን በልዩ ልዩ ምክንያት መሐበሩ ጽናት ሳያገኝ ፈረሰ። አሁን ጆኒ የጀመረውን የሮዚ ድርሰት ከጨረሰ ሁለተኛ ዓላማው ይህን የፈረሰ ማህበር ከሱና እሱን ከመሳሰሉ የበሰሉ ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያኖች ጋር ሆኖ በመመካከር መልሶ ማቋቋም ነው። ሁኔታው ካመቻቸ በዚሁ የራት ግብዣ ይህን አብይ ጉዳይ አንስቶ ለመወያየት ጥሩ አጋጣሚ ስለሆነለት ጸስ ብሎት ፊቱ ፈገገ።

አዎ በልዩ ልዩ ጊዜ ከውድ ሀገራቸው ተሰደው የኮበለሉ እድሚያቸውና ጾታቸው የተለያየ ብዙ ኢትዮጵያኖች በዚቹው ጆኒ ባለባት በብሬመን ከተማ ይኖራሉ። የቻሉት ሲማሩ ያልቻሉት ደግሞ የፈረንጅ ሰሀን አጥበው ዲቃላ አሳድገው ኑሮአቸውን በስደት ይገፋሉ። ያልቻሉትም የውጪ ሀገር ኑሮ ያንገፈገፋቸው ሆድ የባሳቸው ጥቂት ብኩኖች በመጠጥና በሌላም መጥፎ ልማዶች ተለክፈው አልፎ አልፎ ሕይወታቸውን በገዛ እራሳቸው ያጠፋሉ። እዚህም ደረጃ ያልደረሱት



የተጨበጠ ዓላማ፣ ብሩህ ተስፋ በማጣት ከሰው እርቀው እራሳቸውን ደብቀው በአእምሮ ሕመም ይሰቃያሉ።

በተለይ በባእድ ሀገር የተወለዱት ሕፃናት ወላጆቻቸው ጥረት ስለማያደርጉላቸው የሀገራቸውን ቋንቋ ባህልና ታሪክ ጨርሶ የማያውቁ ሞልተዋል።

ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ ኢትዮጵያ የውጪው ዓለም የሚያውቃት ታሪክና ባህሏን ሳይሆን ድህነቷን ብቻ ነው። በዚህም ተደቅለው የተወለዱት ሕፃናት በሀገራቸው ስለሚያፍሩባት «ኢትዮጵያዊ ነኝ» ከማለት ጀርመናዊነትን ይመርጣሉ። ከባህል ምግብ እንጀራ ይልቅ የፈረንጆቹን ቺዝ በርገርና ቢግሜክ ይወዳሉ። የሀገራቸውን ቋንቋ ጨርሶ የማይናገሩም አሉ። መልካቸው ክልስ ስማቸው ሳይቀር የባእድ ሆኖ የመጡበትን የማያውቁ የኢትዮጵያዊነት ጠረን የጐደላቸው የወደፊት ግሥጋሴ መድረሻቸው ምን ይሆን? መነሻውን ያላወቀ መድረሻውን ለይቶ ለማወቅ በጣም ይከብዳል።

ጆኒ የሮዚን ድርሰት ማንበብ አቁሞ ይህንና ይህንን የመሳሰሉ ሀሳቦች ተደጋግመው እየመጡበት መንፈሱ ተጨነቀ። በርግጥ ችግሩን ቀደም ብሎ ያውቀዋል። እሱም እንደ ሌሎቹ ጥቂር ስደተኛ በባእድ ሀገር እየተሰደበ የሚደርስበትንም በደል በመቻቻል ለረዥም ጊዜ ኖሯል። አሁን ግን ሁሉን ለምዶት ከእራሱ ይልቅ የሚያስበው ለሌላው ኢትዮጵያውያን ስደተኞች በተለይ ጀርመን ለተወለዱ ሕፃናቶች ነበር። «ነገ ሀገር አለን» ብለው በኢትዮጵያዊነታቸው እንዲኮሩ ከአሁኑ መለዮአቸውን መገንባት ቋንቋ ባህልና ታሪካቸውን ማስተማር እጅግ አስፈላጊ መሆኑን በማተኮር አጥብቆ አሰበ።

አዎ፣ ለዚህ ችግር ወሳኝ መፍትሄ ባይሆንም በመጠኑ የሚረዳው በብሬመን የኢትዮጵያ የስደተኞች መገናኛ መሐበር ማቋቋም እጅግ አስፈላጊ መሆኑን አስቦ በዓላማው ጸና። ጆኒ የሮዚን ታሪክ እንደጨረሰ ለዚህ አብይ ተግባር የሚያደርገውን ተኝቶ ሲያውጠነጥን አንቅልፍ ይዞት ሄደ።

ሮዚ ከምግብ ቤት ወጥታ መኪናዋን ካቆመችበት ደባቃ ሥፍራ አስነስታ ሄደች። ከከተማው ክልል ሳትወጣ ጥቂት ኪሎሜትሮች እንደነዳች በግራ በኩል የሆነ ነገር ተንገጫግጮ አስደነገጣት። ፍሬን ይዛ

ለማቆም ስትሞክር የፊት ጐማው ከአራቱ ብሎኖች ተፈትልኮ ከመኪናው እርቆ ብቻውን ተንከባሏል። ታክሲዋ በግራ በኩል አዘንብላ በመሽከርከር ከሆነ ግንብ ጋር ልትም ብላ ተጋጨች። መሪው መሐል ተጠቅሎ የተቀመጠው የአየር ፊኛ (Air bag) በቅጽበት ተፈትልኮ ወጥቶ ሮዚን አቅፎ በመያዝ ከጉዳት ሰወራት። በዚህ አደጋ ከውጪም የተጐዳ ሰው አልነበረም። ግን ግጭቱን ያዩና የሰሙ የአካባቢው ነዋሪዎች ቶሎ በመድረስ የመጀመሪያ እርዳታ በማድረግ ሮዚን ከመኪና ውስጥ በዘዴ ደግፈው ብርድልብስ አንጥፈው አስተኟት። ወዲያው ፖሊስና አንቡላንስ ደርሰው ሮዚን ይዘው ሆስፒታል ወሰዷት።

መኪናዋ በፖሊሶች ተከባ የግጭቱ ሁኔታ በፎተግራፍ ተነሳ። የመኪናዋ አግድሞሽ መቆም ሌላ ትራፊኮችን እንዳያውክ በሌላ መኪና ስትጫን በቀኝ በኩል ያለው የኋላ ጐማ ድንገት ወድቆ እመሬት ዘጭ አለ። በሁኔታው ፖሊሶቹ ተገርመው የቀሩትን ጐማዎች ቢመለከቱ ሁሉም ብሎናቸው ላልቷል። ይህ የሆነ ሰው በሮዚ ላይ አደጋ ለመጣል የተደረገ ትልቅ ሤራና ተንኮል መሆኑን ጠርጥረው ወንጀለኛውን ለማወቅ መኪናዋን ለምርመራ ወደትራፊክ ጽ/ቤት ገራዥ እንዲሄድ አደረጉ።

ፋጡማ ሥራ ጨርሳ እጀኒ ቤት ሲነጋጋ ደረሰች። አገር አማን ነው ብሎ ከእንቅልፉ ተነስቶ እቅፍ አድርጐ ሳማት። የሮዚን የለሊት አደጋ አጫወተችው። በድንጋጤ ልብሱን እንኳን ሳይለውጥ ፋጡማን እቤት ትቶ በግል መኪናው ሆስፒታል ደረሰ። ሮዚ ቤቷ መሄዷ ተነገረው። ፈጥኖ መኖሪያ ቤቷ ደረሰ። ክላውዝም ሰምቶ አጠገቧ ሆኖ አቅፎ ይዟታል። ጉዳት ባይደርስባትም ዓይኖቿ እንባ አቅርረዋል። ጀኒ ሆዱ ባብቶ በነገሩ አዘነ። ቤቱ ጭር ብሎ በዝምታ ተዋጠ። ሮዚ ስቅስቅ ብላ አለቀሰች። ክላውዝ የምን ለቅሶ ነው ብሎ ተቆጣ። በዛ ወቅት ስለአደጋው ሁኔታ መነጋገር ፈጽሞ አልተቻለም። «ዛሬ ሲቀፈኝ ነው ከቤት የወጣሁት ምነው እግሬን በሰበረው» ብላ ሮዚ ተማረረች። ጀኒ ከጉዳት በመትረፏ እያባበለ አጽናናት። ክላውዝ ሰውነቷን አያሻሸ አበረታታት። በዚህ ሁኔታ አብረው ሦስቱም እዛ ቆዩ። ሮዚ ደክሟት ለመተኛት ስታሸልብ ጀኒ ሁለቱን ተሰናብቶ የሮዚን ጉንጭ በወንድምነት ፍቅር አብሶና ስሞ ጥሏቸው እያዘነ ወደቤቱ ተመለሰ። ክላውዝ የሮዚ ትንፋሽ ስለተቋረጠበት ደንግጦ ተርበተበተ።



ፋጡማ ጀኒ እስከሚመለስ ቁጭ ብላ አልጠበቀችውም። ልብሷን አወላልቃ አልጋ ውስጥ ገብታለች። እሱም አወላልቆ ተዳበላት። እንደ ወትሮ ተቃቅፈው አንሶላ አልተጋፈፉም። የፋጡማን እንጃ እንጂ ጀኒ በሮዚ ሁኔታ አዝኖ ስሜቱ አልተፍታታም። ቢደክመውም እንቅልፍ የሚባል በዓይኑ አልዞር ብሎ አስቸገረው። የአደጋ ሁኔታውን ባያውቀውም ይህ ተንኮል ምናልባት የሙራትና የከድር ሳየሆን አይቀርም ብሎ ልቡ ጠረጠረ። «ግን ይሄን የሚያሠራ ሮዚ ምን በደል በደለቻቸው? የለም እንዲሁ ተራ አደጋ ይሆናል» በማለት አሰቦ «እንኳን የእሷን ክፉ አላሳየኝ» ብሎ ተጽናና። ለመተኛት ዓይኖቹ ተከድነው ሲያሸልቡ የፋጡማ ኩርፊያ አባነነው። እርርር እሽ! እርርር እሽ እርርር እሽ ፊቱን ወደሷ ዞሮ አፏን ስሞ አቅፎ እንደያዛት እሱም እንደሷ ማኩረፍ ጀመረ ኩርርር አሽሽሽ ኩርርር እሽሽሽ።

እረፋዱ ላይ ፋጡማና ጀኒ ከእንቅልፋቸው ነቅተው፣ ሮዚ ቤት ስልክ ደውለው የሚያነሳው ጠፋ። ቡና እየጠጡ እዛው መኝታ ላይ ተጋድመው እርስ በርሳቸው ይወያያሉ።

ባለፈው ጊዜ ጀኒ ለፋጡማ ጨርሶ ያላወራላትን የድሮ ፍቅረኛውን ታሪክ ፋጡማ ጠይቃው ቡናውን ፉት እያለ በጀርባው ተንጋሎ ይህንኑ ታሪክ ቀጠለላት።

«ያው እንደልኩሽ እልፍነሽ ለጀርመናዊ ሰው ልጅ መውለዷን በስልክ እንደሰማሁ ክፉኛ ተበሳጨሁ። የቅናት ዛር መላ አካላቴን ወረረኝ። ያለችበትን ሆስፒታል ስለማውቀው በቶሎ ሄጄ እሷንም ሕፃኑንም በቢላ አርጄ በመግደል ወሰንኩ።» ፋጡማ ንግግሩን አቋርጣ «ቢስሚላሂ» ብላ ዓይኖቿን ጨፍና ተንገፈገፈች። ጀኒ ንግግሩን ቀጠለ።

«የሚያማምሩ ቀይ የጽጌረዳ አበባዎች ገዝቼ የሥጋ መቁረጫ የሰላ ቢላዎ እውስጡ ሸጉጬና ደብቄ መኪናዬ ውስጥ ገባሁ። ሰውነቴ በቅናት ወበቅ ግሎ ነደደ። ፋጡማ ንግግሩን አቋርጣ «እኔ እኮ ጀኒ እንደዚህ የምትቀና አይመስለኝም። ለካስ ደካማ ነህ» ብላ ለራሷ ጥንቃቄ ለመውሰድ ጀኒን በመፍራት ስሜቷ ተርበተበተ። ጀኒ «ይሄ ድክመት ሳይሆን ወንድነት ነው። ብቻ በአጠቃላይ በፍቅረኛዬ መነጠቅ ከዛም አልፎ ከሌላ መውለድ አበሳጨኝ መኪናየ ውስጥ ገብቼ በግድ አስነስቼ በአጭር ጊዜ ውስጥ ከከተማው ወጥቼ ትልቁ አውራ ጐዳና አውቶባህን ውስጥ ገባሁ። ፍጥነቴ እየጨመረ ሄዶ ከነፍኩ። ቅናቴ ሳይበርድ ያቀድኩትን በቶሎ ለመፈጸም ቸኮልኩ። በሁለቱ ደም ታጥቤ ቅናቴን ለማርካት ተስገበገበኩ ጐመጀሁ።


መኪናዬ ብትፈጥንም አጭሩ መንገድ ረዘመብኝ። የቤንዚን መስጫውን ፔዳል እስከመጨረሻ ድረስ እረገጥኩት። ትራፊክ ባይበዛም ዓይኖቼ ተጭበርብረው የቅርቡን ትተው የሩቁን እያሳዩኝ ተደነጋገርኩ። ሰውነቴ ግሎ አላበኝ። ትንፋሼ ተቆርረጠ። እጆቼ ተንቀጠቀጡ። ጆሮዎቼ ከፍተኛ የግጭት ጩኸት ሰምተው ደነቆሩ። ከዛ የሆንኩትን ጨርሶ አላውቅም።

በሦስተኛው ቀን ከእንቅልፌ ኮማ ስንቃ ያለሁት ሆስፒታል መሆኑን አወቅሁት። ግራ እጄና ቀኝ እግሬ በፋሻ ተጠግነዋል። ሕመሙ ስላልተሰማኝ ሁኔታው ሕልም መሰለኝ። የክፍሉን አስታማሚ ነርስ ጠይቄ የመኪና አደጋ ደርሶብኝ በአንቡላንስ ሆስፒታል መምጣቴን የደረሰብኝም ጉዳት መጠነኛ መሆኑን አንገቴን እየዳሰሰች አባብላ አጫወተችኝ።» ፋጡማ አንገት የመዳሰሱ ወሬ አልጥም ብሏት ሲጋራዋን ለኮሰች። ጆኒ ንግግሩን ቀጥሎ እኔም የነርሷን የለሰለሰ እጆች እያሻሸሁ በደረሰብኝ አደጋ ተጽናናሁ። ፋጡማ የለኮሰችውን ሲጃራ ሳታጨሰው በንዴት መተርኮሻው ላይ ደፈጠጠችው። ከነርሷ ጋር ጆኒ አዲስ ፍቅር የጀመረ መስሏት እሷም መልሳ ቀናች።

ጆኒ የፋጡማ ሁኔታ አልተሰማውም። ንግግሩን ቀጥሎ እኔም ቅናቴ ይብረድ እንጂ ለእልፍኝሽ ያለኝ ቂም አልተለወጠም ሲውል ሲያድር አጠቃላይ ሀሳቤ እሷን ትቶ የተጐዳ አካሌን ሕመሜን ወደምትዳብሰው አስታማሚ ቆንጆዬ ነርስ አዘነበለ። ፋጡማ ጆኒን በትዝብት ዓይን አይታው። በንዴት በቅናት ስሜት ጠላችው። ታሪኩን ጨርሳ ሳታዳምጥ ከተጋደመችበት ተፈናጥራ በመነሳት ማድቤት (ኪችን) ገባች። ምግብ ለማዘጋጀት ይሁን ለሌላ የተሳለውን ቢላ አውጥታ በቅናት ስሜት እየተጫነች መልሳ መላልሳ ሞረደችው። ጆኒ የፋጡማ ድንገተኛ የቅናት ስሜት ጨርሶ አልታወቀውም። ያለፈውን የፍቅር ትዝታ አስታውሶ ዓይኖቹ የክፍሉ ኮርኒስ ባዶ ጣራ ላይ ተሰክተው እንዳፈጠጡ ስሜቱ ቀዝቅዞ ሰውነቱ በርዶ አንቀላፍቶ ተኝቷል።



# ክፍል አሥራ አራት



ሰማዩ የሀዘን ከል የለበሰ መስሏል። አልፎ አልፎ የተቆጣጠሩ ደመናዎች የዝናብ እንባቸውን ለማፍሰስ ተዘጋጅተው በንፋስ ጥፊ ከወዲያ ወዲህ ይንገዋለላሉ።

ቦታው እዚሁ ጀርመን ውስጥ ከሆነች አንዲት ከተማ የሆነ ቤተክርስቲያን አካባቢ ነው። ግቢው የመቃብር ሥፍራ በመሆኑ የሙታን ከተማ መስሎ እንዲታይ በልዩ ልዩ ሀውልቶች አጊጧል። የንፋሱ ሽውሽውታ፣ የወፎቹ ጭውጭውታ አልፎ የሰው ልጆች ለቅሶና ዋይታ ከሩቅ ተሰማ።

በመጠኑ ተምሶ አፉን የከፈተው የመቃብር ከርስ ላንቃውን ዘርግቶ ጥርሶቹን አግጦ ያዛጋል። የወዳጅና ያፍቃሪ የመረረ ለቅሶ፣ የእድምተኞች የሀዘን እንጉርጉሮና ሙሾ፣ የቄስ ፍትሃትና ዝማሬ፣ የቤተክርስቲያኑ ቃጭልና ደውል አንድ ላይ በመሆን ምድረ ግቢውን አስተጋባው።

ሞት የሕይወት ግማሽ አካል ጥቁሩ ክፍል ነው። ሕይወትና ሞት በአንድ ሳንቲም ላይ እንዳሉ ፊትና ጀርባ የማይነጣጠሉ መንትያ አካል ናቸው። በመሠረቱ መኖርን የፈለገ መሞትን መፍራት የለበትም። ግን ሞትን የማይፈራ ማን ደፋር ሰው አለ? ጤነኛ በሽተኛ ሀብታም ደሃ ወዘተ. ሁሉም በዚች ዓለም ላይ ለመኖር ይፍጨረጨራል። ካላበደ ሕይወቱን እንደዋዛ መስጠት አይወድም ታጓጓዋለች። ግን መራራ ሁኔታ ገጥሞት ኑሮን ማሸነፍ ያልቻለ ደካማ ሰው አልፎ አልፎ ሕይወቱን በገዛ እጁ ሲጥ አድርጐ ሲያጠፋ ይገኛል።

በእለቱ አንድ የኢትዮጵያ ዜግነት ያለው ስደተኛ ሰው አርፏል። የባህር ማዶ ነጭ አፈር የሚጫንበት አስከሬን በመቃብሩ ከርስ ታጥቦና ተገንዞ፣ ምስጥ በማይበላው ሳጥን ውስጥ ገብቶና ታሽጎ፣ የኢትዮጵያ ባንዲራ ለብሶ ቀርቧል። ፍቅረኛ ሚስቱ ዘመድና አዝማድ፣ ወዳጅና ጓደኛ ኢትዮጵያውያን ሌሎችም የሀዘኑ ተካፋይና ጋዜጠኞች የሚስጢር ፖሊሶች ሳይቀሩ በስፍራው ተገኝተዋል።

ሴቶቹ ከል የተነከረ ነጠላቸውን አደግድገዋል። ወንዶቹ ኮሌታው ወደ ላይ የታጠፈ ጥቁር ልብሶች ለብሰዋል። ሁሉም በሀዘን ተውጠው ዓይኖቻቸው እንባ አቆርዝዘዋል። አልፎ አልፎ ከማዶ አንዳንድ ሴቶች ሀዘናቸው በርትቶ ለቅሷቸውን መቆጣጠር እየተሳናቸው ጮክ ብለው እየተንሰቀሰቁ ያለቅሳሉ። በተለይ አንዷ ደረቷን በፈረንጅ አደባባይ ሳታፍር እየደለቀች ያዙኝ ልቀቁኝ ትላለች። የመረረ ሀዘን አድሮባት «አብሬ ካልተቀበርኩ» ብላ መሬት ወድቃ ተንከባለለች። ሁኔታውን ያየ እድምተኛ ልቡ በሀዘን ተነክቶ ዓይኖቹ የማይገታ እንባ አፈሰሱ። በአካባቢው ለቅሶና ዋይታ በርክቶ ስፍራው በእንባ ጎርፍ ታጠበ።

በባደን ቩርትንበርግ (Baden Würtenberg) ግዛት የኢትዮጵያ የመገናኛ መሐበር ፕሬዚዳንት ዶክተር ስንታየሁ የሟቹን የሕይወት ታሪክ በአጭሩ ተናግረው ለዚሁም የቀብር ሥነ ሥርዓት ከልዩ ልዩ ሥፍራ የመጡትን እንግዶች አመስግነው ንግግራቸውን ጨረሱ።

ልብሰ ተክኖ የለበሱት የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ቀሲስ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል እየጠቃቀሱ ሞት የማይቀር እዳ መሆኑን ለእድምተኛው ሀዘንተኛ ቀባሪ ዘርዝረው አስረዱ። ለሙታኑም የፍትሃት ጸሎት አድርገው በተለይ ለሟቹ የቅርብ ዘመዶች ቸሩ እግዚአብሔር ብርታቱንና ጽናቱን እንዲሰጣቸው ተመኙ። ጭብጥ አፈር ከመቃብሩ ከንፈር ዘግነው የኢትዮጵያ ባንድራ የተሸፈነው የሙት ሳጥን ወደ ከርሰ መቃብር የማንሳ በገመድ ግራና ቀኝ ተይዞ በቀስታ ወደታች ሲወርድ እርጭታው የሕሊና የስንብት ጸሎት አድርገው መቃብሩን በያዙት መስቀል ግራና ቀኝ አሳልመው ጨረሱ።

በእለቱ የተቀበረው የሀገሩ የመንግሥት አስተዳደር አንገፍግፎት ሁለት ያደጉ ልጆቹን ለዘመድ አዝማድ ኢትዮጵያ ጥሎ የሕግ ባለቤቱን ይዞ ጀርመን የኮበለለው ስደተኛ ሰው አቶ በድሉ ጥላሁን ይባላል።

ይህ ሰው ጀርመን ከገባ ቅርብ ጊዜ ቢሆንም የፖለቲካ ጥገኝነት ጠይቆ ቩትንበርግ በምትባለው ትንሽ ከተማ ከባለቤቱ ጋር ይኖራል። ጉዳዩ በዳኞች ታይቶ በደንብ ሳይጣራ ጀርመን ሀገርን ለቆ እንዲወጣ ተፈረደበት። የተሰጠው ፍርድ አላግባብ በመሆኑ ይግባኝ ብሎ በጠበቃ



ተከራከረ። አልሆነለትም። እንዳውም ከነባለቤቱ ለ6 ወር እንዲታሠር ተፈረደበት። ባለቤቱ በቅድሚያ ተፈታች። እሱ እዛው ቀረ። ከአምስት ወር በኋላ ሊፈታ አንድ ወር ሲቀረው እዚያው እሥር ቤት እንዳለ ተሰቅሎ ሕይወቱ አለፈች። ሞቱ በገዛ እጁ ይሁን በሌላ ሰው በፖሊስ ተጣርቶ የቀረበ እውነት አልተገኘም ብቻ እራሱን በራሱ እንደ ገደለ ተደርጎ አስከሬኑ ለውድ ባለቤቱና ዘመዶቹ ተሰጠ።

ይህ ጉዳይ ጀርመን የሚገኙትን ብዙ ኢትዮጵያኖችን ቀርቶ ሌላ ዜጎችንም ጭምር አሳዝኖ አስቆጣ። በቦንና በሌላም የጀርመን ታላላቅ ከተማዎች ትልቅ ሰላማዊ ሰልፍ (ዴሞኒስትሬሽን) ተደረገ። የሟቹን የፖለቲካ ጉዳይ በደንብ ያላጣሩ ዳኞች ተወገዙ። የተባበሩት መንግሥታት የሰባዊ ጠባቂ ድርጅት ጉዳዩን እንዲያውቀው ተደረገ። የአምነስቲም ኢንተርናሽናል ይሄን በተመለከተ ብዙ ሪፖርት ጻፉ። የሁሉም ጥረትና ልፋት፣ ለቅሶና ዋይታ ምናልባት ለመጪው እንጂ የዚህን ምስኪን የሟች ነፍስ ሊመልሰው አልቻለም። መራራ ሀዘን ነገሮችን የመለወጥ ኃይል ቢኖረው ኖሮ ስንቱ የሞተ በተመለሰ ነበር። ግን ሀዘን ተደርቦ የሚጎዳው አዛኙን ፍጡር ነው።

የቀብሩ ስነ ሥርዓት ግን እጅግ ብዙ ሰው በተገኘበት በታላቅ ሁኔታ ተከብሮ ውሏል። በቅርብ የሚያውቁት ወዳጅና ጓደኞቹ ሟቹ ያደረገውን የፖለቲካ ትግል ለሀገሩ ያለውን ፍቅር በመዘርዘር አሰምተዋል። በተለይ አቶ ተፈራ ፍቃዱ የተባለው ወዳጁ በሟቹ ስደተኛ ገጸባሕሪ የጻፈውን ግጠም አነበበ።

«ፍርድ የጎደለብሽ
ሞት የረከሰብሽ
አንቺ ዓለም ምድሪ፣
ውጣ ውረድ ብዬ
ሳይገኝ ፍርዱ ሳይወጣ እውነቱ፣
ዛሬ ተረትቼ ገባሁ ከመሬቱ፣
ሞትን እሸሽ ብዬ
ከሀገሬ ኮብልዬ
ቤቴን ዘጋግቼ ልጆቼንም ጥዬ
ለካስ እጓዝ ነበር ሞትን ተከትዬ።


JN STILLER TRAUER

የአገሬ አፈር ይብላኝ ያገሬ መሬት
አስከሬን ቢጠግብ ማታና ጠዋት
በሀገሬ ስቀበር በመረሬ አፈሩ
ሠርግም ለቅሶም ቢሆን ያምራል የሰው ልጅ በሀገሩ።
ዘመድ አዝማዶቹ ምን ያንጫጫችኋል
ከመከራ ስደት የኔ ሞት ይሻላል።
እንደኔ በአደጋ በስደት ያላችሁ
በጋራ ውይይት መፍትሄ ብላችሁ
በሀገራችሁ ኑሩ እውነት ልንገራችሁ።
ከሀገሩ የወጣ ሀገሩ እስኪመለስ
ቢጭኑት አህያ ቢለጉሙት ፈረስ
እውነትም ተብሏል እመሰክራለሁ
ከየት ሽንጐ ቆሜ ከማ እሟገታለሁ
በደሌን ስቃዬን ለአምላክ እነግራለሁ
ፍርድ አያጓድልም ከእሱ እጠብቃለሁ»
ብሎ በዛ የተሰበሰበውን ቀባሪ መልሶ አስለቀሰው።

በዚህ የቀብር ስነ ሥርዓት ሮዚና ጆኒ ኢንጂኔር በላቸውና ደርቤ ፀጋው ከብሬመን መጥተው ከስፍራው ተገኝተዋል። በቀደም የሙሽራ ልብስ የለበሰችው ሮዚ ዛሬ ጥቁር በጥቁር ለብሳ በሀዘን ተጨብጣለች። ሚቹን ባታውቀውም በሁኔታው ተቆጥታ በማዘን ተንሰቅስቃ አልቅሳለች። ጆኒም እንደ እሷ ልቡ በሀዘን ተነክቶ፣ የስደት ኑሮ ምሬቱን እያስታወሰ፣ የሀገሩን ጥቁር አፈር እየተመኘ አልቅሶ አንብቷል። እሱና ደርቤ ፀጋው ሮዚን ግራና ቀኝ ደግፈው ቆመዋል።

ከማዶ ባሻገር ኢንጂኔር በላቸው አቶ ዘመመ ዘውዱን እንዳይወድቅ ደግፎ ይዞታል። አቶ ዘመመ ለራሱ ይሁን ለሚቹ ሀዘኑ ባልታወቀ ስሜት እየተብረከረከ ምርር ብሎ ያለቅሳል። እንባው ግን ጥልቅ ሀዘን በማይታይበት ፊቱ ላይ በመውረዱ ያስቀይማል።

ከመሐል የሚቹ ባለቤት በከፍተኛ መራራ ሀዘን ተውጣ እየነፈረቀች ያዙኝ ልቀቁኝ ትላለች። የሙሾ እንጉርጉሮ እያሰማች «አብሬ



ካልተቀበርኩ» ብላ ደረቷን እየደለቀች ትጮሃለች። አካባቢው የሀዘን እምታና ዋይታ ዋጠው። የጠቆረው ሰማይ የነጐድጓድ ድምፅ አሰምቶ የበኩሉን የዝናብ እንባ ወደ መሬት አንጠባጠበ። በስፍራው የተሰበሰበው ሁሉ የሚቹ የቀብር ስነ ሥርዓት እስከሚፈጸም ድረስ እዛው በእንባውና በዝናቡ እርጥበት ቆሞ በመጨረሻ ቄሱ ጸሎተ ቡራኬ አድርገው ሕዝቡን አሰናበቱት።

ጊዜው እየገሠገሠ ሄዶ የሚቹ ቀብር ሳምንት አለፈ። የኢንጂኔር በላቸው አራምዴ ግብዣ በዚሁ ሀዘን ምክንያት አልተፈጸመም። ብሬመን የተደራጀ ማሕበር ባይኖርም ከሀገር ቤት እንግዳ ሲመጣ «እንኳን ደህና መጡ» ለማለት የችሎታን ስጦታ ይዞ መገናኘት የተለመደ ባህል ሆኖ ቆይቷል። በዚሁም ምክንያት የኢንጂነሩ ወላጅ እናት ስለመጡ ሮዚና ጆኒ ደርቤና ደመቀ ሌሎችም በርከት ያሉ ኢትዮጵያኖች በበላቸው ቤት ተሰብስበዋል።

የመጡት እንግዳ ምንም ቢያረጁ ስለሀገር ቤት አስተዳደር ጭቆናና የኢኮኖሚ ውድቀት፣ የጐሳና የዘር ልዩነት የኤርትራን ድፍረት ሳይቀር በደንብ ያውቃሉ። አንደበታቸው እንደ አካላቸው አልደከመም። የሚያውቁትን አካፍለው ለተደረገላቸውም መስተንግዶና ስጦታ አመስግነው ወደመኝታ ክፍላቸው ገቡ።

በእለቱ የነበሩት ኢትዮጵያውያን ስለሀገር ጉዳይ አንስተው እርስ በእርሳቸው ተወያዩ። ከዛም አልፎ በጀርመን ውስጥ በስደት ኑሮ የሚገጥማቸውን ችግር አብረው አወጉ።

ጆኒ ባለፈው ጊዜ የወጠነውን ሀሳብ በዚሁ አጋጣሚ ዘርዝሮ አጫወታቸው። በተለይ ውጪ የሚወለዱት ሕፃናት የሀገራቸውን መሠረታዊ ታሪክ ባህልና ቋንቋ መማር እንደሚገባቸው አሳሰበ። በስደትና በልዩ ልዩ ምክንያት ከኢትዮጵያ የሚመጡትንና እዚህም ያሉትን ለመርዳት የእርስ በርስ ግንኙነት እጅግ ጠቃሚ መሆኑን አስረድቶ ብሬመን ውስጥ አንድ ማሕበር ማቋቋም እንደሚያስፈልግ ነገራቸው። ሁሉም የቀረበውን ሀሳብ ደግፈው በወር አንድ ጊዜ እንዲገናኙ ተወሰነ።

ውሎ አድሮ የተለያየ ብዙ ስብሰባዎች በልዩ ልዩ ቦታዎች አደረጉ። ለመሐበሩ መመሥረት የዲሞክራሲያዊ ውይይት አስፈላጊ መሆኑን አምነው የማሕበሩም ሊቀመንበር ኢንጂነር በላቸው፣ ዋና ፀሐፊ ጆኒ

ሆነው ተመረጡ። ይህም መሐበር በብሬመን የሚገኙ «የኢትዮጵያውያን ስደተኞች መገናኛ ማሕበር» በሚል ስያሜ ተቋቋመ። በመጨረሻም ማሕበሩ በጀርመን መንግሥት በሕግ የተፈቀደ መሆኑ ተረጋግጦ ሥራውን ጀመረ።

ጊዜው ወደፊት እየሮጠ ሄዶ የገና በዓል ደረሰ። በነሐሴ ወር (ዲሰንበር) አውሮፓ የጨፈገገ ክረምት ነው። ሌት ተቀን በረዶ እንደጥጥ ከሰማይ እየበነነ ይረግፋል። መሬቱ በበረዶ ክምር ይሞላል። በዚህ ወቅት ብርድና ቁሩ አይጣል ነው።

ሮዚ ባለፈው ጊዜ የመኪና አደጋ ደርሶባት እንብዛም ባትጐዳም ለታክሲ ሥራ ያላት ፍላጐት እያደር ቀዘቀዘ። በሳምንት ሰባት ቀን መሥራቷ ቀርቶ ሦስት ቀን ማረፍ ጀመረች። ከፍተኛ ትምህርቷንም ለመቀጠል ወሰነች። ዩኒቨርስቲ ሊያስገባት የሚያስችለውን ልዩ ልዩ ማስረጃዎች አቅርባ የሕግ ትምህርት ለመማር አመለከተች። ፍላጐቷ ተቀባይነት አግኝቶ ፈነጠዘች። የመጀመሪያው ሴምስተር በሚቀጥለው አዲስ ዓመት በሕዳር ወር መሐከል አጋማሽ መሆኑ ተነገራት።

ሮዚ መጪውን የገና በዓል እዚሁ ቆይታ የዓመት እረፍቷን ወደ አሜሪካ ሄዳ ታላቅ እህቷን ለመጠየቅና የተባለውንም ሀገር ለመጐብኘት ወሰነች። ክላውዝ ለሮዚ ያለው ስሜት እየቀዘቀዘ ቢሄድም ያላቸው ወዳጅነትና መተሳሰብ እስካሁን አልተቋረጠም።

ፋጡማ ለጆኒ ያላት ፍቅር ግን እያደር ላልቶ ግንኙነታቸው እንደ በፊቱ አልሆነም። ጆኒ የድርሰቱ ሥራ ውጥረት ስለመሰለው ፋጡማን ጨርሶ በሌላ አልጠረጠረም። ይህ የዋህነቱ ብዙ ጊዜ ጐድቶታል «ሁለት ሰዎች ከተፋቀሩ መተማመን እንጂ መጠራጠር ኩነኔ ነው» ብሎ ያምናል። የሴቶች ዋሾ ለስላሳ አንደበት፣ ለቅሶና መቅለስለስ የተጠራጠረ መንፈሱ እንዲፀና የጨከነ ልቡ እንዲፈታ ያደርጉታል። ከአለፈው ስህተት መማር ስለማይችል በዚህ ጉዳይ ሁል ጊዜ ይጠቃል።

የፋጡማና የክላውዝ ግንኙነት በድብቅም ቢሆን አልተቋረጠም። የእልህ የወሲብ ሥራቸው እያደር መቀራረብንና መላመድን አትርፎ መዋደድን መሠረተ። የሰሞኑም የሮዚ ዘወትር አለመሥራት ለግንኙነታቸው ጥሩ አጋጣሚ ሆኖ ወሲባቸውን ጠገቡት። በሚሥጥር የሚያደርጉት መሽኮራረም ሳያስቡት ለሌላው በግልጽ መታየት ጀመረ። የሰዎች አሉባልታ የታክሲ ሹፌሮች ሀሜት አነፈሰ።



ጆኒ በድርሰቱ ላይ የመሐበሩ ጉዳይ ተጨምሮ ለፋጡማ ያለውን ፍቅር በመጠኑ ቀንሶበታል። ቢሆንም የታክሲውን ሥራ ሲሠራ በእረፍት ጊዜ እራት ከእሷ ጋር ለመቋደስ ፈልጐ ስለሚያጣት የቅናት ወላፈን ከቦታል።

ፋጡማ የጆኒን ደካማ ጐን ከነገራት ያለፈ የፍቅረኞቹ ታሪክ ታውቃለች። ለስላሳ አንደበቷ የውሸት እንባዋ ቅናቱን አባሮ ልቡን አራርቶ ይይዘዋል። ፍቅርን በዘዴ ካላስጨረሱ በቅናት የሚመጣውን ጦስ ፋጡማ ጠንቅቃ ታውቃለች። ይህም ባይሆን በሆዷ የያዘችው ቅሪት ማለት አርግዝናዋ ከእሱ ይሁን ከክላውዝ በአንድ ቀን ከሁለት ወንዶች ጋር ተኝታ ገና የማ መሆኑን አለየችም እስከዛው ጆኒን በዘዴ መለማመጥ ግድ ሆኖባታል።

ገና (Christmas) በአውሮፓ እጅግ አድርጐ የሚከበር ታላቅ በዓል ነው። ወላጆች ከልጆቻቸው፣ ፍቅረኞች ከወዳጆቻቸው፣ ጓደኛ ከጓደኛ ዘመድ ከዘመድ ተገናኝተው የሚገባበዙበት ስጦታ የሚለዋወጡበት ተወዳጅና ተናፋቂ የክርስቶስ ልደት መታሰቢያ እለት ነው።

በዚህ ታላቅ በዓል ብዙ የንግድ መደብሮች እጅግ ብዙ ገቢ ያካብታሉ። የታክሲዎችም ገበያ በዚሁ ወቅት ይደራል። ከተማዋ በልዩ ልዩ ቀለማት ማብራቶች አምራ ታሸበርቃለች። ለዚሁ በዓል መታሰቢያ የሚሆኑ የጥድ ዛፎች (ክርስቲማስ ትሪ) ተቆርጠው በየቦታው የሸጣሉ። በየመንገዱና በየመደብሩ የልደት መዝሙሮችና ዘፈኖች ጐልተው ይሰማሉ። በተለይ ሕፃናቶች በዚህ ወቅት ደስታቸው ወሰን የለውም። በየመንገዱና ብየቤቱ ይቦርቃሉ የሚሰጣቸውን የገና ስጦታ እያለሙ በዓሉን በናፍቆት ይጠብቃሉ።

የፋጡማ ሃይማኖት ለዚህ ታላቅ በዓል ባይጨነቅም ጆኒን ለማስደሰት ብላ የገና ምሽቱን ከእሱ ጋር መኖሪያ ቤቱ ለማሳለፍ ቃል ገብታለች። ስጦታም ገዝታ አሰናድታለች። ጆኒም በዓሉን ከእሷ ጋር ሆኖ ለማሳለፍ ደስ ብሎት ቤቱን በሚያምር ትልቅ የገና ዛፍ አሽቆጥቁጦታል። ለእሷም የሚሰጣትን ስጦታ አዘጋጅቷል።

ሮዚና ክላውዝም በዚሁ በዓል አብረው ለመሆን ወስነው የሮዚ ቤት ከመቼውም ይበልጥ በገና ዛፍና በሌላም አዳዲስ የቤት እቃዎች አሸብርቋል።

አዲሱ የታክሲ ሹፌር ደርቤ ፀጋው የሚያፈቅራት ባለቤቱ ቆንጂት ነፍሰ ጡር ሆና መውለጃዋ ስለደረሰ ሆስፒታል አስገብቶ ያስታምማል። እጁን እያሻሸ ከንፈሯን እየሳመ አበረታቶ ደስታውን ይገልጻል። ለዚሁ በዓል የሚሆን ልዩ ገፀበረከት ገዝቶላታል። እሷ ለእሱ ያላት ስጦታ ግን ምን ጊዜም የማይጠገበውን የአብራካቸውን ፍሬ ነበር።

ያ ዓመቱን ሙሉ ሲናፈቅ የነበረው ታላቅ በዓል ደርሶ ዛሬ የቤተክርስቲያን ደውሎች በየቦታው ተደወሉ። ሕዝቡ በየቤቱ ተከቶ ከተማዋ ጭር አለች። ተራርቆ የሰነበተው ቤተሰብ በዚሁ ምሽት ተቀራርቦ ተጠጋጋ። ድግሱን በልቶ ስጦታ ተለዋወጠ።

ጆኒ ለፋጡማ የሰጣት የወርቅ የጆሮ ጉትቻ ነበር። ባለፈው ጊዜ አንገቷን በስሜት ተውጦ ሲስም አንድን ጉትቻዋን ውጦባት ነበር። ለእሱ ምትክ እንዲሆናት አስቦ ያደረገው ነው። ፋጡማም እንደሱ አስባ ባለፈው ጊዜ ልብስ ስትተኩስ ያቃጠለችውን ሸሚዝ ትዝ ብሏት ያመጣችለት ስጦታ የሀር ነጭ ሸሚዝ ነበር።

ሮዚና ክላውዝ የተሰጣጡት ስጦታ ጌጣ ጌጥ ሳይሆን የተለየ ነበር። ክላውዝ ሮዚ ለዓመት እረፍቷ ወደአሜሪካ ለመሄድ መወሰኗን ስለሚያውቅ ያመጣላት ስጦታ ለዚሁ ጉዞ የደርሶ መልስ ትኬት ነበር። ሮዚ በስጦታው ተደስታ ሳመችው። ለእሱም ያዘጋጀችለትን የውስጥ ለውስጥ መዋኛ ሙሉ ልብስ ከነመነጽሩ ሰጠችው።

ደርቤና ቆንጂት በዚሁ ታላቅ ምሽት ሆስፒታል ነበሩ። ቆንጂት ምጡ ሳየበረታባት የመጀመሪያ ልጇን በሰላም ተገላገለች። ደርቤ በደስታ ቦርቆ ለበዓሉም ለናትነቷም መታሰቢያ እንዲሆን የአልማዝ ፈርጥ ያለበትን ትልቅ የወርቅ ሐብል አንገቷ ላይ አጠለቀላት። ቆንጂት ሕፃኑን አንስታ ለባሏ ሰጠችው። ደርቤ ስጦታውን ሴት ልጁን በደስታ ተቀብሎ ሳመላት። ስሟንም ለበዓሉ መታሰቢያ እንዲሆን ክርስቲና ብሎ ሰየማት።

በየበዓላቱ ወዳጅ ለወዳጅ ዘመድ ለዘመድ፣ ጓደኛ ለጓደኛ፣ የተገናኘው ተገናኝቶ ያልተገናኘው በስልክ ጥሪ «እንኳን አደረሰህ (ሽ)» መባባል በአውሮፓ የተለመደ ባህል ነው።

ጆኒ የደርቤ ባለቤት በደህና መገላገሏን በመስማቱና ለበዓሉም መልካም ምኞት ለመግለጥ ስልክ ደወለለት።



«መልካም ገና ባለቤትህ ተገላገለች አሉ እንኳን ደስ ያለህ!»

«አዎ በአምላክህ ለአንተም መልካም ገና»

«ምን ተገላገለች?»

«ሴት ነዋ!»

ምኞቱ በመሳካቱ ተኩራርቶ ወንድ ልጅ ከሌላ ወዳጁ ስለነበረው አሁን ከሚወዳት ሚስቱ ሴት ልጅ በማግኘቱ በደስታ ስሜት እየፎከረ።

«ታዲያ እስከዚህ ምን ያስፎክራል ደርቤ?»

«ልጅ ማስወለድ ጭቃ ጠፍጥፎ አሻንጉሊት፣ ወይም ብረታ ብረት ገጣጥሞ ሮኬት መሥራት መሰለህ? የማታውቀው ብዙ ጥበብ አለው» አለ አነጋገሩ የቀልድ ይሁን የምር ቅጡ ባልታወቀ ስሜት።




«ልጅ ለማስወለድ ምን ዘዴ ያስፈልጋል። ያው ግፋ ቢል ወሲብ ነው» አለ ጆኒ ንግግሩን ከሳቁ ጋር ደባልቆ ውይይታቸው የቀልድ መሆኑን ፈር እያስያዘ።

«አዎ! እሱም ቢሆን ጥበብ ያስፈልገዋል። ዝም ብሎ ማድረግ ብቻ አይደም ሰልህ ብዙ ዘዴና ብልሃት አለው።»

«ምን ዓይነት ጥበብ ደግሞ መቼም አንተ የማታውቀው የለም። ቀልድም ቢሆን ጆኒ በአነጋገሩ ተገርሞ።»

አዎ ጥበቡ የፈለገውን ጾታ እንዲገኝ የማድረግ ዘዴ ነው። ለዚህ ነው የፈለጉትን ሴት ልጅ ያገኘሁት።

«እንዲህ ያለ አዲስ ልማድ አይገባኝም ብቻ እንኳን ደስ ያለህ» ብሎ ስልኩን ዘጋው።

ሮዚም እንደ ጆኒ «እንኳን አደረሰህ» ለማለት ስልክ ደወለችለት። ለገናም የደረሳትን ስጦታዎች የክላውዝን ደብቃ የሌሎችን ገልጣ አጫወተችው።

ሮዚ «ሃሎ ጆኒ እንኳን አደረሰህ መልካም ገና።»

«አንቺንም እንኳን አደረሰሽ። በዓሉን እንዴት አከበርሽ?»

«በደስታ።»

«ብቻሽን?»

«አ! እንግዲህ እንደ ፖሊስ አትጠይቀኝ ብቻዬንም ሆነ ከሰው ጋር በዓሉን በጥሩ ሁኔታ አሳልፌአለሁ። አንተስ?»

«እኔ ያሳለፍኩት ከፋጡምዬ ጋር ሆኜ ነው።»

«ምን ስጦታ ተሰጣጣችሁ?»

«ወርቅና ሸሚዝ። አንቺስ?»

«አዲስ የሙዚቃ የአማርኛ ዘፈን ካሴት ከአሥመራ ተልኮልኛል።»

«አትቀልጂ እባክሽ! ከአሥመራ ደግሞ ምን ወዳጅ አለሽ?»

«ኤርትራውያን እኮ ከኢትዮጵያ ቢለዩም ሁሉም ጠላታችን አይደሉም።»

«እሱንማ አውቃለሁ። አብረን ኖረን ተዋልደን የለ። ለመሆኑ የማን ዘፈን ነው የተላከልሽ? የበረከት?»

«አይደለም። የሐመልማል አባተ አማርኛ ዘፈን ነው።»

«እነዚህ ኤርትራውያን እኛንና ቋንቋችንን እየጠሉ ዘፈናችንን ወደው ማዳመጣቸው ምን ይባላል?»

«ድንበራቸው ተለየ እንጂ ፍቅራቸው አሁንም አለ።»

«አይ የእነሱ ፍቅር በአፍንጫዬ ይውጣ።»

«ለምን?»

«እኔ የሕዝብን ታሪክ አንድነትና ነፃነት የማይደግፍ ዜጋ ምን ጊዜም ወዳጄ አይሆንም።»

«እባክህ ጀኒ ለጊዜው ነው እንጂ ተመልሰው ይመጣሉ።»

«አሁንስ ቢሆን መቼ ከኛ ጫንቃ ወረዱ! ነፃነት አሉ ነፃነት ሰጠናቸው ግን አሁንም የሙጥኝ ብለውናል።»

«እሱስ ወደው ሳይሆን ለጥቅማቸው ብለው ነው። ያላመረቱትን ቡና በስማቸው ኤክስፖርት ያደርጉ የለ።»

«ምን እሱ ብቻ የክልል ድንበራችንን ጥሰው የለማ መሬታችንን የኛ ነው በማለት ለጦርነት ተዘጋጅተዋል በግር ግር ምናልባት የሥልጣን



ኮርቻቸውን ለማደላደል ይሆናል እንጂ የወዳጅ ጠበኛ የሚያደርጋቸው ምንድነው?»

«እውነት ሊዋጉ? አትለኝም።»

«ነው እንጂ በተጠንቀቅ ላይ ነው ያሉት።»

«እንደገና መልሶ የእርስ በርስ ጦርነት ጅልነት ነው።»

«አዎ ከጅልነትም ጅልነት ታዲያ ይሄ እንዳይሆን የኢትዮጵያ ልኡካን የተደጋገመ የሰላም ጥሪ ለሻብያ መሪዎች አድርገው አልተቀበሉም።»

«ለምን?»

«ጦርነቱን ፈልገው ነዋ!»

«ምን ተማምነው? ቢቀርባቸው ይሻላል። የእሳት እራት ከመሆን አርፎ መቀመጥ ይበጃል።»

«እውነትሽን ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ ታጋሽ ነው። ትዕግስቱ ካለፈ ግን ቁጡው እንደ ተነካ ንብ ወሮ ተናዳፊ ነው። እንኳን ኤርትራ ጣሊያንን በአድዋ ድል ያደረገ ጀግና ነው።»

«ንቀት ነው እንጂ ታሪኩንስ ያውቁታል።»

«እባክሽ ሮዚ በበዓል ቀን ፖለቲካ አታናግሪኝ። ሁኔታቸው እኔንም አናዶ ገብተህ ተዋጋ የሚል ስሜት አሳድሮብኛል።»

«እኔም እከተልሃለሁ ጀኒ አብረን አንግባ ለምዬ ኢትዮጵያ ለውድ ሀገሬ እምትላታለሁ።»

«እኔም። ሮዚ ግን ዘፈኑን የላከልሽ ሰው ማነው?»

«አሁን ስም መጥራቱ ምን ያደርግልሃል! ካሴቱን ወስደህ አዳምጠው።»

«መልካም የኔ እህት ጊዜ ካለሽ ነይ። ለበዓሉ ያዘጋጀሁትን ድግሥ አብረን እንቋደሳለን።

«በደስታ እመጣለሁ።»

በመጨረሻ «መልካም በዓል ለሁላችን» ተባብለው ስልኩን ዘጉት።»

ጀኒ በዚሁ ታላቅ በዓል ሳቢያ የሦስት ቀን እረፍት ወስዷል። የጀመረውን ድርሰት ለመጨረስ ቆርጦ ተነስቷል። የመጽሐፉ ጅምር እንዳማረ ሁሉ መደምደሚያውም የተዋበ እንዲሆን ከልቡ ይጥራል።

ከቤቱ ሳይወጣ ከሚወዳት ወዳጁ ከፋጡማ ሳይገናኝ አንገቱን ደፍቶ፣ አዕምሮውን ጨምቆ የሮዚን ታሪክ ልብ ወለድ መጽሐፍ የመጨረሻውን ክፍል መደምደሚያ ጽፎ ጨረሰ። በስድስት ወራት ውስጥ አቀርባለሁ ብሎ የፎከረው ድርሰቱ ዓመት ሙሉ ፈጅቶ አለቀ። የበኩር ልጅ ባይሆንም ሁለተኛ የድርሰት ሥራውን ወልዶ ተገላገለ።

የመጀመሪያ ሥራው ትርጉም አዘል የተዋናይ መስተዋት ይባላል። ይሄኛው ሁለተኛ ልብ ወለድ ድርሰቱ ነው። ደራሲ ባይሆንም ጀርመን ውስጥ በስደት ኑሮ ሲኖር በእለታዊ ገጠሞች ላይ የተመሠረተ አንድ ክፍል ሲሆን ሁለተኛውን «ጥቁር እንግዳ በአውሮፓ» በሚል አርእስት ሌላ ድርሰት ለመጻፍ አቅዷል። በእርግጥ ይሄ የሮዚ ታሪክ የጻፈው ለንባብ ሳይሆን ለፊልም ሥራ (Drehbuch) እንዲሆን አስቦ ነው። በዚህም ድርሰቱ አንባብያን አያረካም ብሎ ይጠራጠራል። ብቻ ሥራውን ጨርሶ ዓላማውን በከፊል ስለፈጸመ ደስ ብሎት ፈነጠዘ። ታሪኩ ተጽፎ ይለቅ እንጂ እንደገና ተነቦ በደንብ ታርሞና ተስተካክሎ ገና አልተጻፈም። ለዚህም እረዳትና ልዩ አማካሪ የግድ አስፈላጊ ሆኖ ታየው።

በእርግጥ ጆኒ በሥነ ጽሑፍ ትምህርት በዶክትሬት ድግሪ ከታወቀ ዩኒቨርስቲ የተመረቀ አበልጁ የሆነ ጥሩ ወዳጅ አለው። ዶክተር ሲራክ ይባላል። የሚኖረው አውሮፓ ፖላንድ ዋና ከተማ ዋርሶ ውስጥ ነው። ጆኒ ለዚሁ ምሁር ሁኔታውን በስልክ አናግሮ በመስማማቱ ድርሰቱን ለግርድፍ እርማት ዋርሶ ከተማ ላከው።

የጆኒ ድርሰት እረቂቅ ለዶክተር ሲራክ ተልኮ በመጠኑ ታርሞ መጣ። የታሪኩ አወቃቀር የተጫዋቾቹ አመራረጥ የሥነ ባሕሪ አወራረስና ዲያሎግ የተዋጣለት ነበር። ግን በውስጡ የሀገራችንን አንባብያን የሚያስቀይም ከባህላችን ወግና ልማዶችን ያልተዛመዱ በርከት ያሉ የብልግና ቃላቶች የወሲብ አድራጐቶች አሉበት። ስለዚህ እነዚህ ነገሮች እንዲወገዱ ወይም በምሥጢር እንዲጻፉ ምክር ተሰጠው።

ጆኒ ይህንን አድራጐት እስካሁን ብዙ ታዋቂ ደራሲያን የተጠቀሙበት በመሆኑ ትንሽ ለየት ያለ የስነ ጽሑፍ የእፍረታዊ ባህል አብዮት መጻፍ አስፈላጊ በመሆኑና እንዲህም ያለ አጻጻፍ በአውሮፓ በመለመዱ የጓደኛውን ምክር በሙሉ አልተቀበለውም።

«የትኛውም ኅብረተሰብ ከቆየ ልማዱና ባሕሉ ቀስ በቀስ ሊላቀቅ የሚችለው በዚሁ ዓይነት የተጻፉ የደፋር ደራሲያን የባህል ዓብዮት ውጤት



ሥራ ነው። በመጽሐፍ አይሁን እንጂ በጋዜጣ ደረጃ (ማዶና ኢሮቲክ) ሕዝቡን ከሚስጢር ልማድና ባህሉ ገላግለውታል።» ብሎ ጽሑፉን እንደገና አስተካክሎ ነቀፋ የሆኑትን ቃላቶች በከፊል ቀንሶ ከዓመት እረፍቱ በኋላ በኮምፒዩተር ጽሑፍ በደንብ አስተካክሎ ለመጻፍ ወሰነ።

በርግጥ ይህ በሮዚ ታሪክ ላይ የተመሠረተው ልብ ወለድ መጽሐፍ የመጀመሪያው ክፍል ይሆናል።

ጆኒ ይሄን የጻፈው ለፊልም ሥራ እንዲሆን ታዞ ነው። ምናልባት – የታሪኩ ባለቤት ሮዚ ከዚህ መንደርደሪያ ሀሳብ ተነስታ፣ ወይም ሌላ አቋም ወስዳ በትእዛዝ ሳይሆን በስሜት የተሞላ የስነ ጽሑፍ ድርሰት እንደምታቀርብ በእርግጥ ተስፋ ያደርጋል።

ጊዜው እየሮጠ ሄዶ ከነፈ። የገና በዓል አልፎ የዘመን መለወጫ ታላቅ በዓል ደረሰ። የለሊቱ የታክሲዎች ሥራ ተጀምሮ ሮዚም ሆኑ ክላውዝ ፋጡማም ሆነች ጆኒ ሌሎችም ጭምር በእለቱ ሁሉም ሥራ ገብተዋል።

የሮዚ የመጀመሪያ በሯ ማለት የታክሲ አገልግሎት ሥራዋ ከሆነ መደብር ነበር። መደብሩ የፀሐይ ሳሎን ነው። (Sonnen Stadium) ፈረንጆች ነጭ ቆዳቸው በኤሌትሪክ ብርሃን ሙቀት የሚጠይሙበት ሱቅ ነው። ያስጠራቻት የድርጅቱ ባለቤት ቢያንካ ትባላለች። ከሮዚ ጋር በደንብ ይተዋወቃሉ። እንዳውም የሮዚ ቁንጅናና ጠይም ቆዳ ማርኳት ትወዳታለች። ለድርጅቷም የድጋፍ ማስታወቂያ እንድትሆን አስባ በብዙ ገንዘብ ልትቀጥራት ፈልጋ ሮዚ አልተስማማችም። ያም ሆኖ ቢያንካ ታክሲ ሲያስፈልጋት ሮዚን በፉንክ እያስጠራች የሁለቱ ግንኙነት እስካሁን አልተቋረጠም።

ሮዚ መኪናዋን አቁማ ቢያንካ ገብታ ተቀመጠች። ሁለቱም የሞቀ ሰላምታ ተለዋውጠው ጉዞ ጀመሩ። ሮዚ ቢያንካን «የመደብርሽ ሥጋ እንዴት ነው» ብላ ጠየቀቻት።

«ወይ ይገርምሻል ሮዚ ገበያ በሽበሽ ነው ፋታ አሳጥቶኛል ግን ምን ያደርጋል ገንዘብ ሞልቶ ጓደኛ የለኝም።»

«ዋናው ገንዘብ ነው በሌላው አትጨነቂ። ይልቅ ልጠይቅሽ ያሰብኩት ነገር አለ ለምንድነው ፈረንጆች ሊጠቁሩ የሚፈልጉት?»

«እንዳንቺ ቆንጆ ለመሆን አምሯቸው ነው እኔማ ዘወትር እየተቀቀልኩ እንቢ አለኝ ምነው ስወለድ ያንቺን ቆዳ በሰጠኝ።»

«እባክሽ አትቀልጂ። ይሄ ቢሆን ኖሮ መቼ ኒገር ሻንቅላ እያሉ ይሳደቡ ነበር።»

«አ! እባክሽን ብላክ ኢዝ ቢዩቲፉል የሚሉም እንዳሉ አለመዘንጋት ነው።»

«አይ ቢያንካ እንደሱ የምንለው እኛ ጥቁሮች እንጂ ፈረንጆች አይደሉም።»

«አትሳሳች እኔም እላለሁ በተለይ ያንቺን ቀለምና ውበት አደንቃለሁ ከልቤም እወድሻለሁ» ብላ ወደሮዚ ጠጋ ብላ ልትስማት ሞከረች።

ሮዚ ቢያንካን ሳትስማት በቀኝ እጇ ገፍተር አድርጋ «ውበቴን ማድነቅ መብትሽ ነው። ግን አትንኪኝ እንዳው ልጠይቅሽና እንዴት ሴት ሆነሽ ሴትን ትወጃለሽ?»

«አ! ሮዚ እኔ ጨርሶ ወንድ አልወድም። ሊዝቢያን ነኝ። ለዚህ ነው የወደድኩሽ ሮዝዬ።» ብላ ስትጠጋት ሮዚ መኪናዋን ዳር አሲዛ አቁማ ሂሳቧን ሳትቀበል ገፍትራ አስወጣቻት።

«ውይ እኛ ታክሲ ነጂዎች ያለብን አበሳ» ብላ እድሏን አማረረች። «የሰካራም ጠባይ፣ የጉረኛ ተረብ የትምክተኛ ምፀት የዘረኛ ንቀት እረ ስንቱን ችለነዋል። ይህ አልበቃ ብሎ የዚች የሊዝቢያን ድፍረት ይገርማል ምኑን ጥሎብናል?» ብላ ተከዘች።

ጆኒ እንዳጋጣሚ ኢትዮጵያዊ መርከበኞችን ብሬመን ከተማ አግኝቶአቸው ወደ አዲሱ ወደብ ወሰዳቸው።

«የዓባይ ወንዝ» የተባለችው የኢትዮጵያ መርከብ በብሬመን ወደብ መሐለቋን ጥላ ባህሩ ዳር ቆማለች። ለአውሮፓ ያመጣችውን ቡና ይሁን ቆዳ፣ ሰሊጥ ይሁን ቦሎቄ አራግፋ ለጥቂት ሰዎች መንደላቀቂያ የሆኑ አሮጌና አዳዲስ መኪናዎችን ሌላም ቁሳቁሶችን አግበስብሳ ጭናለች።

መርከበኞቹ ጆኒን እራት ጋብዘውት ተያይዘው አብረው ክፍል (ካቢን) ገቡ። ምግብና መጠጥ ቀርቦ ጆኒ በደንብ ተጋበዘ። ወቅቱ የሥራም ቢሆን ያለበት ቦታ ኢትዮጵያ እንዳለ ቆጥሮ ደስ አለው። ውይይት ተጀምሮ ጆኒ ብዙ ስደተኞች ከኢትዮጵያ በመርከብ ተደብቀው ብሬመን እንደገቡ ነገራቸው።

አንደኛው መርከበኛ የጆኒን አነጋገር አርሞ «ያልካቸው ሰዎች ስደተኞች ሊባሉ አይገባም እናውቃቸዋለን ኑሮ የመረራቸው ወዛደሮች



ናቸው። ስደተኞች ማለት የሀገሩን አስተዳዳር ተቃውመው ለእስራትና ግድያ ሲፈለጉ ያመለጡ የፖለቲካ ሰዎች ማለት ነው» አለ።

«እንዳልከው እርግጥ ነው። ግን ለመሰደድ የግድ የፖለቲካ ንቃት አያስፈልግም። ኑሮ ሲመረው ነፃነቱ ሲገፈፍ ፍትህ አጥቶ ሲበደል አሻፈረኝ ብሎ ካለበት ከኮበለለ ስደተኛ ነው። እናንተስ እንዴት ነው የኢትዮጵያ አስተዳደር ኑሮ አላማረራችሁም?» ብሎ በድፍረት ጠየቀ።

«ቢመርስ ቤተሰብ ጥሎ የት ይኬዳል? ያለችውን ቂጣም ሆነ ቆሎ ተቃምሶ በሀገር መኖሩ ይመረጣል።»

«ችግሩ እኮ የእህል ጉዳይ ብቻ አይደለም። የመብት የነፃነት የፍትህና የዲሞክራሲ መጓደል ጭምር ነው።»

አንዱ «እሱ ያመጣውን እሱ እስኪመልሰው መጠበቅ ነው» ሲል ሌላው «እውጪ ሆኖ ሆድን ሞልቶ የፈረንጅ ሰሀን እያጠቡና ዲቃላ እያሳደጉ ከመኖር ሀገር ቤት ተቀምጦ እየተራቡ መታገሉ ይሻላል» ሊሉወ ፈልጐ ጆኒን ማስቀየም ስለመሰለው ተወው። በዚሁ አይነት ትንሽ ተወያይተው ጆኒ ወደ ሥራው ተመለሰ።



ፋጡማና ክላውዝ ታክሲያቸውን የሆነ ቦታ አቁመው አብረው አንድ መኪና ውስጥ ተቀምጠዋል። እርስ በእርሳቸው ተቃቅፈው ይሳሳማሉ። ሮዚ ድንገት ሁኔታውን ተመልክታ አይኖቿን ማመን አቃታት። እልህ ይዟት ሳታስበው መኪናዋን አጠገባቸው ቀጥ አድርጋ አቆመችው። ከመኪናዋ ዘላ ወርዳ ፋጡማን ካለችበት ከክላውዝ እቅፍ ውስጥ ስባ አወጣቻት። ፋጡማ የሮዚን እጆች ከሰውነቷ በግድ አስለቅቃ በጉልበቷ የሮዚን መንጋጭላ ልትመታ ስትሞክር ሮዚ እግሯን ይዛ ጣለቻት። ፋጡማ ከወደቀችበት ተንከባላ ተነሳች። ሁለቱም ግብ ግብ ተያይዘው በቦክስ ተማቱ በጥፍራቸው ተቧጠጡ። ፋጡማ የሮዚን ፀጉር ጨምድዳ ያዘቻት ሮዚ በጥፍሯ የፋጡማን ፊት ቧጠጠችው። በሁለት እጆቿም

ማንቁርቷን ይዛ አነቀቻት። ፋጡማ ትንፋሽ አጥሯት ተጨነቀች። በቀኝ እግሯ ሮዚን ረግጣና ጠልፋ ጣለቻት ሁለቱም እመሬት ወደቁ። ተንከባለሉ ፋጡማ ከላይ ሮዚ ከታች።

በአካባቢው የነበሩ ታክሲ ነጅዎችና ሌላም ሰዎች ጠቡን ከበው ተመለከቱ። ሙራት ለፋጡማ ለማገዝ አሰፈሰፈ። ጆኒ በድንገት ደርሶ እጠቡ መሐል ገብቶ ገላገላቸው። የፋጡማ ፊት በሮዚ ጥፍሮች ተቧጦ ደም አመንዥኋል። ሮዚ ፀጉሯ ተመነጫጭሮ ዓይኖቿ ቀልተው ፊቷ አመድ መስሏል።

ሁለቱም ቢገላገሉም እሩቅ ለሩቅ ሆነው ያዙኝ ልቀቁኝ እያሉ ይጮሃሉ። በእልህ ተፈራግጠው ይፎክራሉ። ይሰዳደባሉ። ፋጡማ በቱርክም በጀርመንም ቋንቋ እየቀበጣጠረች ትጮሃለች። ጉትቨረን ሲክሪም አፈ! ኒገር ሁረ ትላለች። ሮዚ አራስ ነብር ሆና ያዙኝ ልቀቁኝ ብላ ትጋበዛለች። እሷም በሀገሯ ቋንቋ «ያልታወቀብሽ ልክስክስ ሸርሙጣ» «ቁሌታም ትላም» ብላ በጀርመንኛም «ሽቫይን ብሎደ አልተ ኩወ!» አለቻት። ፖሊስ ተጠርቶ እስካሁን አልመጣም። ሌላ ጣጣ ሳይመጣ ጆኒ ሮዚን ሙራት ፋጡማን ይዘው ከጠቡ ቦታ እርቀው ሄዱ።

ጆኒ ፋጡማን ቢወዳትም በዚህ አድራጎቷ መልሶ ጠላት። አረገዝኩልህ ያለችውንም ተጠራጥሮ በሞኝነቱ አዘነ። በሴት በኩል ያልታደለ ምስኪን መሆኑን አወቀ። ሮዚ ክላውዝ ይህን ወራዳ ሥራ በአደባባይ በማድረጉ ታዝባ ጠላችው። ለእሱ ያላትን እምነትና ፍቅር ከልቧ ተፍቆ ስሜቷ በቅናት አረረ።

ጆኒ ሮዚን አባብሎ ከአጽናናት በኋላ ሁለቱም ሥራቸውን አቋርጠው መኪናቸውን ይዘው ባዝል ደረሱ። ጠቡን በሚመለከት የቋጥ የባጡን አውርተው ሲደክማቸው በግል መኪናቸው ወደየቤታቸው ሄዱ።

ሮዚ ቤት ገብታ የሰላም እንቅልፍ አልተኛችም። አጭሩ ለሊት እረዝሞ አስቸገራት። ክላውዝን ሁለተኛ አለማየት ከልቧ እርም ብላ ቆረጠች። የቅርብ ጓደኛዋ ፋጡማ ይህን አስከፊ ነገር በማድረጓ ጠላቻት። ለሷም ምሥጢሯን ሁሉ ዘርዝራ በማጫወቷ ጸጸታት። የብልጥ ሞኝ መሆኗ ገርሟት «ያልጠረጠረ ተመነጠረ» ብላ የቀዳችውን ኮኛክ በአንድ ትንፋሽ ዥው አድርጋ ጠጥታ ሲጋራዋን ለኮሰች።

ለፍቅር ያላትን እጦት አሰላስላ ተከዘች። «ምን የእርግማን ቋጥ ነኝ» ብላ እድሏን እረገመች። ጀርመን ከመጣች ከሀብታሞችም ሆነ ከሌላም ታላላቅ ሰዎች ተወዳጅታ ብትቆይም ፍቅሯ ሰምሮ ከእሷ ጋር



እስከመጨረሻው አልቆዩም። የሷም ይሁን የእነሱ ጥፋቱ የማን እንደሆነ ጨርሶ አታውቅም። ሀገሯ የሚደረገው ነገር ትዝ ብሏት «ምነው እዚያ ኢትዮጵያ እያለሁ በደብተራ ድግምት የሚደረገውን የመስተፋቅር ክትባት በተከተብኩ» ብላ ተቆጨች። መልሳ «አበስኩ ገበርኩ እንዲህ ያለውስ አጉል አምልኮ አንኳን ቀረብኝ ብላ ግንባሯን አማትባ ኮኛኳን ቀድታ ተጐነጨች። በቅባት የወዛ ፊቷን በመስታወት ተመልክታ ገና ወጣት ነኝ ለፍቅር ምን አስቸኮለኝ» ብላ መልሳ ተጽናናች።

በርግጥ ለክላውዝ የነበራት ፍቅር በአንድ ጀንበር ከልቧ ተፍቆ አልጠፋም። መኝታዋ አጠገብ የተቀመጠው የሱ ፎቶግራፍ እስካሁን አልተነሳም። የቅናት ዛር መልሶ ሰውነቷን ወረረው። ሲጋራዋን አጥፍታ ልትደውልለት ስልኳን ጨብጣ ቁጥሩን አዞረች ገና ሳይጠራ መልሳ ዘጋችው። መቀመጥም መተኛትም አቅቷት ክፍሏ ውስጥ ሆና ከወዲያ ወዲህ ተንቆራጠጠች። ቅናቱም መጠጡም ተደምሮ ሰውነቷን አላበው። ቀዝቃዛ ሻወር ወስዳ ተጠቅላ ተኛች።

ጆኒ የነገሩን ሁኔታ ለማጣራት ለፋጡማ ስልክ ደወለላት። ስልኳ እየጮኸ በቶሎ አላነሳችውም። በዚህ ሰዓት የደወለው እሱ መሆኑን በስሜት አውቃለች። ብቻ የምትለውን ውሸት በማሰላሰል አልቻኮለችም። ጆኒም የጥሪውን መልስ እስከሚያገኝ ታግሶ እሱም ጥያቄውን ከየት እንደሚጀምር ያሰላስላል።

ጥር ጥርርርር ጥር...ፋጡማ ስልኩን አንስታ «ሃሎ ፋጡማ ነኝ» ቀሰቀስኩሽ ይቅርታ ጆኒ ነኝ።

«አውቃለሁ። በሁለታችን ጠብ መሐል ገብተህ እኔ ከላይ ሆኜ ስገጫት ጠብቀህ ገላጋይ መስለህ ያገዝከው ያገርህ ልጅ ስለሆነች ነው? ያንተ ነገር ታዘብኩህ በቃኝ» ብላ በቁጣ ጮኸችበት።

«የምን እገዛ አመጣሽ መሐላችሁ ገብቼ እኩል ነው የገላገልኳችሁ። ጅራፍ ገርፎ ይጮሃል እንደሚባለው ባንቺ ብሶ ቁጣ ያደረግሽው ወራዳ ሥራ አሳፍሮኛል።»

«አ አሳፈረ አላሳፈረህ ወድጄ አድርጌዋለሁ። በለሊት አትጨቅጭቀኝ ልተኛበት። ደግሞ የፈለኩትን ለማድረግ መብት አለኝ። እኔ ልጅቱ በሕግ ያገባኸኝ መሰለህ እንዴ? እዛ የትም ጥለሀት የመጣ ሃውን ሚስትህን ሄደህ ተቆጣ» ብላ ስልኩን በጆሮ ግንዱ ላይ ዘጋችበት።

ጆኒ ተናዶ መልሶ ደወለላት። አላነሳችውም። የሚጠጣ አልኮል ነገር እቤቱ ፈልጐ አጣ። ከወዲያ ወዲህ እየተንጐራደደ ንዴቱን መግታት አቃተው አሁንም መልሶ ደወለላት። ተይዟል። እው! እው! እውውው! የሚለውን ድምጽ መስማት ሰልችቶ ጣለው።

በርግጥ ጆኒ ድርሰቱ አልቆ የደስታውን ወላፈን ገና ሳይሞቅ የፋጡማ ቅናት ሰውነቱን ወረረው። የብቀላ ወጥመዱን ዘርግቶ የሚያደርገውን የተንኮልና የክፋት ሀሳቦችን ጠነሰሰ። ግን አዕምሮ መልሶ እንቢ አለው። እንዲህ ያለው ነገር ተደጋግሞ ስለደረሰበት የአርባ ቀን እድሉን እረገመ። «በሴቶች ላይ ምን ያደረግሁት በደልና ክፋት አለ?» ብሎ እራሱን በራሱ ጠየቀ። ሚስቱን ከነልጆቹ ጥሎ መኮብለሉ፣ የሰው ሚስት ደፍሮ ባይቀማም ሁኔታው አስገድዶት ሬናትን ወድዶ ከትዳሯ ማፈናቀሉ ፀፀተው። ይሄ በማንኛውም ሰው ያለ የኑሮ ክስተት ነው ምናልባት ሌላ እርግማን ቢኖርብኝ ነው» ብሎ ክፋቱን ከልቡ ያለውንም ቅንነትና ደግነት አብሮ እያወዳደረ ደጋግሞ አሰበ።

ጆኒ ሁኔታው አስጨንቆት አንቅልፍ ቢያጣም ሰውነቱ ደክሞ ተዝለፈለፈ። ክፍሉ ጭር ብሎ አስፈራራው። አልፎ አልፎ አጠገቡ ሆና የምታጫውተው ፋጡማ ስለጐደለችበት ሆድ ብሶት ዓይኖቹ እንባ አቀረሩ። የሆነ ክላሲክ ሙዚቃ ከፍቶ እያዳመጠ ተጠቅሎ ተኛ።






# ክፍል አሥራ አምስት

«የሰው ለጅ ሁለት ባሕሪያት ያለው ተዋናይ ነው። ከራሱ በስተቀር ስሜትና አስተሳሰቡን መርምሮ ሊያውቅበት የሚችል ውጫዊ ኃይል ጨርሶ የለም» ይባላል። ይህ ባይሆንማ ኖሮ ስንቶቹ ፍቅረኞች ባልተከዳዱ ነበር።

«ዓለም በጀርባዋ የተሸከመችውን አታውቀውም። አንተም በይሆናል እምነት ደግ ነው ብለህ የተጠጋኸው ሰው አውሬ ሆኖ እንዳይጐዳህ አስቀድመህ ማንነቱን እወቅ» የሚባለውም ለዚህ ነው።

ሮዚ ክላውዝን አፍቅራው ልቡን በማጣቷ፣ ጆኒ ፋጡማን ወዶ በክዳቷ ተናዶ «ሰውን ማመን ቀብሮ ነው» ብሏል። የሁለቱም የልባቸው የትዝታ ጓዳ በቅናት እረመጥ ነዶ ሰንብቷል። ሁለቱም በደረሰባቸው ሁኔታ የሀዘንና የቅናት ማቅ ለብሰው ከርመዋል።

ሮዚ ከእሷ የልቅ ለጆኒ አሰበች። በስተርጅና ለብቻ መኖሩ የሕይወቱን ትንሽ የብርሃን ብልጭታ እንደሚጋርድበት አውቃ የሀገሩ ልጅ የሆነች አንድ የትዳር ጓደኛ ልታስተዋውቀው ወሰነች። ጉዳዩን ከአሁን በፊት ያሰበችበት ቢሆንም በፋጡማ ምክንያት ለጆኒ ልትነግረው አልፈለገችም። ልታስተዋውቀው የፈለገችው የአክስቷን ልጅ እመቤት የምትባለዋን ቆንጅዬ ወጣት ነበር።

አዎ እመቤት ተሾመ የወ/ሮ ቦጋለች ማለት የሮዚ እናት ታናሽ እህት ልጅ ናት። እመቤት ጠባየ ሸጋ፣ ብልህና ባለሙያ ለቤተሰቦቿ ታማኝና አፍቃሪ ባህሏን የጠበቀች ዓይን አፋር የቀይ ዳማ ፀጉረ ዞማ ፈገግታ የተመላባት የደስ ደስ ያላት ቆንጅዬ ወጣት ነች።

ሮዚ ለወላጅ እናቷ ስልክ ደውላ በጉደዩ ተመካከረች። የእመቤትን መስማማት አወቀች። የቤተሰቧን ፍጹም ፍቃደኝነት አረጋግጣ

በመጨረሻ ጉዳዩን ልጆኒ አጫወተችው። «እግዜር ሳይደግስ አይጣላም» ብሎ ባለችው ተስማምቶ እሮዚን አቅፎ ሳማት። የመቤትንም አድራሻ ተቀብሎ በቶሎ ሊጽፍላት ወሰነ። የባእድ ኑሮ ስለመረረው የሀገሩን ልጅ ይዞ ትዳር ቢመሠርት በእርግጥ ኑሮው እንደሚጣፍጥ አውቆ ጐመጀ። በዚህም ለእመቤት የመጀመሪያ መተዋወቂያ፣ የመውደድ ፍላጐት ጮራ የተመላበትን ደብዳቤ ጽፎ ላከላት።

ሮዚ በቅርቡ በደረሰባት ብስጭት የሳምንት እረፍት ወስዳለች። ወደ አሜሪካ ለመሄድ ወስና ዝግጅቱን አጠናቃለች። ግን የአውሮፓ የዘመን መለወጫ በዓል ሲከበር በዋዜማው ማለት ዲሴምበር 31 የታክሲዎች ገበያ እጅግ በጣም ብዙ ነው። ጊዜው ደርሶ ጥቂት ገንዘብ ለመቋጠር ወስናለች። ለዚህም የቀራት ሁለት ቀን ብቻ ነው። ሁለቱ ምሽት እንደ ዓመት ረዝሞ ታያት። ቤቱ ቀዝቅዞ ብቸኝነት ተሰማት፣ ሙዚቃው ተከፍቶ ቢጮኽም ስሜቷን አሙቆ አላዝናናትም።

ጊዜው ከሰዓት በኋላ እሁድ ነበር። ሙዚቃውን አጥፍታ ስልኳን ጨበጠች። መጀመሪያ አሜሪካ ለምትገኘው ታላቅ እህቷ ደውላ የጉዞውን መነሻና መድረሻ ሰዓት ተናግራ ዘጋችው። ሰዓቱ በአሜሪካ የመኝታ ለሊት ቢሆንም እህቷ ከእንቅልፏ በመባንኗ አልተቆጣችም ሮዚም ሁኔታውን አውቃ ይቅርታ አልጠየቀችም።

ኢትዮጵያ የወላጆቿ ቤት ስልክ ተደወለ። ሁለቴ አንደጠራ ወ/ሮ ቦጋለች ያሳደጓት አስናቀች የምትባለዋ ወጣት ስልኩን አንስታ «ሃሎ!» ብላ ስሟን ተናገረች።

ስልኩን የደወለችው ከጀርመን ሮዚ ነበረች። ሁለቱም ለጊዜው በድምፅ አልተዋወቁም። ሮዚ ሌላዋ የቤት ሠራተኛ መስሏት ቆጣ ቆጣ አለች። አስናቀች ለሰለሰች። በኋላ በደንብ ተዋውቀው የናፍቆት ሰላምታ ተለዋወጡ። ሮዚ ከሀገር ቤት ስትወጣ አስናቀች የድሮ ስሟ ተገኘ ትባል ነበር። ያኔ ገና የአምስት ዓመት ሕፃን ነበረች። አሁን 15 ዓመት ሆኗታል። ትንሽ ተጨዋውተው የስልኩ ሂሳብ እንዳይበዛባት እናቷን ወይም አባቷን እንድታቀርብላቸው ብትጠይቅ ሁለቱም እቤት አለመኖራቸው ተነገራት። ምናልባት በቅርቡ የምታገባው ትሩፋት እንዳለች ብትጠይቅም እሷም ከአዲሱ እጮኛዋ ጋር ለሠርግ የሚያስፈልጋቸውን ነገር ለመግዛት ዱባይ ወደተባለ ሀገር መሄዷን ሰምታ፣ አስናቀችን ተሰናብታ ስልኩን ዘጋችው።



ሮዚ የተገኘን ድምፅ በስልክ በመስማቷ ያለፈ ትዝታ ወረራት። ጫማዋን አወላልቃ አፎቴው ላይ ጋደም አለች። ከ10 ዓመት በፊት የተደረገ እውነተኛ ታሪክ በዓይኖቿ መጥተው አንጀበቡባት።

አዎ፣ ወላጅ እናቷ ወ/ሮ ቦጋለች የሆን ቤተክርስቲያን ለማስቀደስ ይሄዳሉ። ሁሉን ጨርሰው ከቤተክርስቲያኑ ሲወጡ በራፉ ላይ አንድ ሰውነቱ የተጐሳቆለ፣ ልብሶቹ የተቦጫጨቀ ሰው እመሬት ትንሽ የከሳች ሕፃን አጋድሞ እያለቀሰ ይለምናል። ሰውየው የሕፃኗ አባት ነበር። ከሩቅ ሀገር በርሃብ ችግር ተሰዶ ከተማ የመጣ መጠጊያ የሌለው ድህነት ያጠቃው ጐስቋላ ምስኪን። ወ/ሮ ቦጋለች በሁኔታው አዝነው የቻሉትን ተዘከሩት። መሬት ተጋድማ የምታለቅሰውንም ሕፃን ወስደው እንዲያሳድጓት ቢጠይቁት ሙሉ ፍቃደኝነቱን በደስታ ገልጦ ልጅን ከመሬት አንስቶ ባባትነት ፍቅሩ ሆዱ እያረገደ አደራ ብሎ ሰጣቸው።

ወ/ሮ ቦጋለች ይችን ሕፃን ታቅፈው መኖሪያ ቤታቸው ደረሱ። «ኡኡቴ ይሄ ደግሞ ከመቼ ወዲህ ያመጡት ደግነት ነው» ብሎ ጐረቤቱ አምቶ ተሳለቀባቸው። ባላቸውና ሌላም ቤተሰቡ «ተስቦ ይዛብን መጣች» ብለው አስፈራሯቸው። ሮዚም ሁኔታው ያሳዝናት እንጂ በእናቷ አድራጐት አልተስማማችም ነበር። የእግዜር ፍቃድ ሆኖ ሕፃኗ ወተቱንም አሬራውንም እየጠጣች በቂ ሕክምና ተደርጐላት እዛው ቤት አደገች። የመጀመሪያ ስሟ ተገኝ አሥራት ነበር። በኋላ አድጋ ትምህርት ስትጀምር አቋሟ ተስተካክሎ ውበቷ ጐልቶ እጅግ ስላማረች አስናቀች አሏት። አሁን የቤቱ ብርቅዬ የሮዚ ምትክ ተወዳጅ በትምህርቷ ንቁህና ብልህ ወጣት ነች።

ሮዚ በዚህ ትዝታ ተውጣ እንቅልፍ አሸልቦ አፎቴው ላይ ተኝታለች። የትዝታዋ ስሜት የሕልም ቅዠት ፈጥሮባት ትወራጫለች። ድንገት የቤቷ በር ተደውሎ ተንኳኳ። ባና ተነሳች ሄዳ በሩን ለመክፈት ግን አልደፈረችም። ጊዜው ቢመሽም ገና አልጨለመም ግን ልቧ ፈርቶ ተጨነቀ። በሯ ደግሞ ተንኳኳ። በደመ ነፍስ ከፎቴው ላይ ፍንጥር ብላ ተነስታ በሩን ከፈተችው። አንድ መልኳ የሚያምር ድንቡሼ ቤት ሕፃን ልጅ አበባ አቅፋ እበራፏ ላይ ቆማለች። ድሮ የምታውቃትን ተገኝ አሥራትን የአሁኑ አስናቀችን መስሏት ብድግ አድርጋ አቅፋ ስትስማት ሮዚ በድንገት ከእንቅልፏ ነቃች። በአጭር ጊዜ ውስጥ ሸልብታ ያየችውን ሕልም አስታውሳ በሁኔታው ተደንጋግራ ዓይኖቿን ባዶ ግርግዳ ላይ አፍጥጣ፣ በትካዜ ስሜት ተውጣ ቁጭ አለች።

ፋጡማ ዑስማን አዲሱ የታክሲ ድርጅት ተመዘገበች እንጂ ገና ሥራ አልጀመረችም። ፊቷ በሮዚ ቡጭራ ስለተጐዳ ሕመሙ እስኪሻላት ከቤቷ አልወጣችም። በነጋታው ክላውዝ መጥቶ በደረሰባት ጉዳት አጽናንቶና ሰውነቷን ደባብሶ አብሯት አምሽቷል። እሱም እንደ ፋጡማ ጉልቶ የሚታይ ቁስል ባይኖርበትም ባደረገው ጥፋት ተጸጽቶ ምራሉ ላሽቋል። ግን የተለየ ምርጫ ስለሌለው ከእሷ ጋር መቆየቱን መርጧል። ፋጡማ ቅሪት ብትሆንም ከእሱ ወይም ከጆኒ መሆኑን ለይታ ስላላወቀች ደፍራ አልነገረችውም።

ሙራትና ከድር በሁለቱ ጠብ ቢደሰቱም ፋጡማ መሥሪያ ቤቱን ለቃ በመውጣቷ አዝነዋል። «እኛ እያለን ለዚች ነጫጭባ ጥቁር ብለሽ እንዴት ሥራሽን ትለቂያለሽ?» ብለው ወቅሰውና አደፋፍረዋት ነበር። ግን የሮላንድ የታክሲ ድርጅት ባለቤት አቶ ሀሮልድ ሮዚን የሚነካባቸው ሰው ጨርሶ ስለማይወዱ «በሳቸው ክፉ ዓይን ከመታየት በነፃነት ተዝናንቼ የምሠራበት ድርጅት ይሻለኛል» ብላ ያደረገችው ውሳኔ ነበር።

ሙራትና ከድር ባለፈው ጊዜ በሮዚ ላይ ያደረጉት ተንኮል በመክሸፉ ተበሳጭተዋል። ወንጀሉ ግን በፖሊስ ተመርምሮ እነሱን ባለመመልከቱ ተደስተዋል። አሁንም ለሮዚ ያላቸው ቂምና ተንኮል ከልባቸው አልተፋቀም። ሮዚ ግን ወንጀሉን እንዲያጣራላት ከአሁን በፊት ለምታውቀው ነጭ ለባሽ ፖሊስ ተገናኝተው ነግራዋለች።

እንድሪያስ አንሶላ ያስለወጠችው ወዳጁ ጥላው ሄዳለች። ሰሞኑን ሥራ አልገባም። እድሉን እያማረረ በየመጠጡ ቤት ማምሸት ጀምሯል። እንደ አጋጣሚ ሆኖ አንዲት ከበርሊን ከተማ የመጣች ቆንጆዩ ተዋውቋል። የዛሬውን ምሽት ከእሷ ጋር ሆኖ እቤቱ በደስታ ይቦርቃል። ምናልባት እሷም እንደሌሎቹ «ይህን ቀይር ያን አምጣ» ማለቷ ይቀራል? ማን ያውቃል?

ጆኒ በእለቱ ሥራ ገብቶ የታክሲ አገልግሎቱን ያጣድፋል። በፉንክ የሚሰጠው በር በርካታ ባለመሆኑ መኪናውን አየር ጣቢያ አካባቢ አቁሞ የታክሲ ተራውን ይጠብቃል። ወቅቱ ክረምት በመሆኑ ዝናብና በረዶ ይጥላል። ሰዓቱ ባይመሽም ጨልሟል። ጆኒ ተራውን ጠብቆ የመጀመሪያውን ቦታ ያዘ። አንድ አጭር ወፍራም ሰው ብዙ ሻንጣዎች ያሉበትን ጋሪ እየገፉ አጠገቡ ደረሱ። ታክሲ ፈላጊ መሆናቸውን አውቆ ሻንጣቸውን ከጋሪው ላይ አንድ ባንድ እያነሳ እመኪና የኋላ ኮፈን ውስጥ



አስገብቶ ጉዞ ጀመሩ። ተሳፋሪው ጀርመናዊ የሆኑ ኢንዶኔዥያ ሀገር ውስጥ ትልቅ ንግድ ያላቸው የናጠጡ ከበርቴ ናቸው። በቅርቡ ሕዝቡ በመንግሥቱ ላይ ባደረገው ሽብር ሰግተው ገንዘብና ጠቃሚ ንብረታቸውን ይዘው መምጣታቸው ነበር። አይሮፕላን ላይ ሆነው ትንሽ ስለወሳሰዱ ለጆኒ ምሥጢራቸውን ሳይደብቁ እያጫወቱት ያሉበት ቦታ ደርሰው ወረዱ። የጫኑትም ትልልቅና ትንንሽ ሻንጣዎች ተረክበው ተሰናበቱ።

ጆኒ የታክሲውን ሂሳብ ከነጉርሻው ተቀብሎ እራቱን ለመብላት ወደመኖሪያ ቤቱ አመራ። ዝናቡ አሁንም ይጥላል። ታክሲውን የሆነ ቦታ አቁሞ እቤቱ ለመግባት የዝናብ ዣንጥላ እመኪናው ኮፈን ውስጥ ፈለገ። የሆነ ትንሽ ጥቁር ሻንጣ ከዣንጥላው ጋር ተጣብቃ አገኘ። የከበርቴው የተረሳ እቃ መሆኑን ልቡ አውቆ እውስጡ ያለውን ለማየት ጓጉቶ ዣንጥላውን ሳይዘረጋ ዘንግቶ ዝናብ እየመታው እቤቱ ገባ።

ጆኒ ያልታሰበ ሲሳይ ገጠመው። ዓይኖቹን ሊያምናቸው አልቻለም። ሰውነቱ በደስታ ድንጋጤ ተርበተበተ። የተራበ አንጀቱ ሳይበላ ጠገበ። በዛች ትንሽ ሻንጣ ውስጥ ያገኘው እጅግ ብዙ ገንዘብ ነበር። የአሜሪካን ዶላር። ምን እንደሚያደርግ ግራ ገባው «ሰው ገንዘብ ሳይኖረው ብዙ ይመኛል ሲያገኝ ደግሞ የሚያደርገው ይጨንቀዋል» ብሎ እራሱን ታዘበ። ለሴንተራል ወይም ለፖሊስ ቢያስረክብ በታማኝነቱ ትልቅ ዝና እንደሚያተርፍ አወቀ። «ግን ዝና ብቻውን ምን ይጠቅማል» ብሎ ያገኘውን ሲሳይ ለማንም ሳይነግር የሆነ ቦታ ደብቆ የለሊቱን ሥራ በተለመደው ሁኔታ በሰዓቱ ጨርሶ ሲነጋ እቤቱ ተመልሶ ገባ።

እንቅልፍ እንቢ ብሎ አስቸገረው። ገንዘቡን ከደበቀበት ለማሸሽ ብዙ ተጨነቀ። ነገሩን ለማረጋገጥ ሁለት ሦስት ለሊት ሠርቶ ሳይታመም የሕመም ፍቃድ ወሰደ። በድብቅ ወደ ሀገሩ የሚወስደውን የአየር ቲኬት ቆርጦ ገንዘቡን ይዞ በሰላም ኢትዮጵያ ገባ።

ውሎ አድሮ በገንዘቡ የሚሠራበትን ፕሮጀክት ለሚመለከተው መሥሪያ ቤት አመልክቶ ሥራው ተፈቀደለት። ፕሮጀክቱ የጐዳና ተዳዳሪ ሕፃናትንና ወጣቶችን ሰብስቦ የሚያስተምርበት አዳሪ የሙያ ማሰልጠኛ ት/ቤት ነበር። ከከተማ ውጪ ሰፊ ቦታ ተሰጥቶት ሥራው በተቋራጭ ኮንትራት ኩባንያ ጨረታ አወዳድሮ ተጀመረ። ሕፃናትና ወጣቶች ከየቦታው ተሰብስበው ስማቸው ተመዘገበ። ወጣት ወጣቶቹ ከኩባንያው ሠራተኞች ጋር ያለደሞዝ አብረው ለመሥራት ፈቃደኛ ሆኑ።

በአጭር ጊዜ ውስጥ የዚሁ የሙያ ት/ቤት ግንባታ ተጠናቆ ብዙ የጐደና ተስተዳዳሪ ሕፃናትና ወጣቶች ገቡበት። የት/ቤቱም ስም በታላቁ ደራሲ መታሰቢያ እንዲሆን ተወስኖ «ከበደ ሚካኤል የሙያ መለስተኛ ማሰልጠኛ ት/ቤት» ተባለ። ደራሲውም በሕይወት ስላሉ የት/ቤቱ የመጀመሪያ ምርቃት በዓል ቀን ተገኝተው መረቁ። በእለቱ በርካታ ተማሪዎችና ባለሥልጣኖች ሌላም ብዙ ሰዎች በተገኙበት በዓሉ በታላቅ ሥነ ሥርዓት ተከበረ። ለበዓሉ ድምቀት እንዲሰጡ ልዩ ልዩ ቀለማት ያላቸው የላስቲት ፊኛዎች ወደሰማይ ተለቀቁ። የተዘጋጁ እርችቶችም ተለኩሰው የቀለም ባሩዱ አብለጭልጮ ቷ! ቧ! ዷ! እያለ ፈንድቶ ጮኸ።

ጆኒ በተኩሱ ጩኸት ከተኛበት እንቅልፍ ባኖ ተነሳ። የተደረገው ያየው ሁሉ የማይጨበጥ የሕልም ሲሳይ መሆኑን አውቆ ቆጨው። ከአልጋው ተነስቶ እያዛጋ ወደመተጣጠቢያ ክፍሉ ገባ።

ያ ተናፋቂው የዘመን መለወጫ በዓል ዋዜማ ደርሶ እለቱ ዲሰምበር 31 ሆነ። የብሬመን የታክሲ የለሊት ሹፌሮች ጦር ሜዳ እንደሚሄድ ወታደር መኪናቸውን ይዘው በየቦታው ተኮለኮሉ። ይህ በዓል በአውሮፓ በታላቅ ፈንጠዝያና ጭፈራ በደስታና በእልልታ የሚከበር ዋዜማ ነው። የአሮጌው አመት እርኩስ መንፈስ አስደንግጦ ለማሸሽ መጪውን አዲስ ዓመት ከጥሩ ተስፋ ጋር በደስታ ለመቀበል የቀለም እሳት የሚተፉ ርችትና ፈንጂ ሮኬቶችን መተኮስ የተለመደ ባህል ነው።

በዚህ እለት ሕዝቡ ከየቤቱ ወጥቶ በከተማው አደባባይ ይኮለኮላል። ዜክት ሻምፓኝ አረቄና ቪኖ ተከፍቶ እየተገባበዘ ይጐነጫጫል። ይጠጣል። ይሰከራል። ጠጥቶ መንዳት ፍጹም የተከለከለ በመሆኑ አብዛኛው የግል መኪናዎች በዚህ ምሽት በከተማው እንብዛም አይንቀሳቀሱም። በዚህም ምክንያት የታክሲዎች ገበያ የጦፈ ነው።

በዚሁ ቀን እስከ እኩለ ለሊት ምሽት ሕዝቡ ደግና ገር ይሆናል። የሚተዋወቀው ቀርቶ የማይተዋወቀው ተቃቅፎ ይሳሳማል። የያዘውንም መጠጥ ተገባብዞ ይቀማመሳል። ዘመን ተለውጦ ወደንጋቱ ሲቃረብ ግን የጭቃ ጅራፉን መተኮስ ይጀምራል። ያዙኝ ልቀቁኝ እያለ ጠብ የሚጭረው ሰካራም ብዙ ነው። ይህን የሚያውቁ የፀጥታ አስከባሪ ፖሊሶችና የአንቡላንስ መኪናዎች የእሳት አጥፊ ብርጌዶች እንደታክሲ ነጅዎች ሕዝቡን ለማገልገል ተዘጋጅተዋል። ወሬም የሚለቃቅሙት የእለቱን ሁኔታ በፊልም ለመቅረጽ ካሜራቸውን በየቦታው እንደመድፍ አቁመው ደግነዋል።



ብሬመን መሐል ከተማ በሮላንድ ሀውልት አደባባይ ሥፍራ እንደደመራ የተተከሉ የቀለም እሳት የሚተፉ እሮኬቶችና ርችቶች ተጠምደው በሰዓቱ ሊለኮሱ ተዘጋጅተዋል። እስከዛው ሕዝቡ በግሉ የገዛውን ትንንሽ ፈንጂ ባሩዶች እየለካሰ ወደሰማይ ይለቃል። ሕፃናትና ወጣቶች አንዱ ሌላውን በዚሁ ተቀጣጣይ ችቦ እያስደነገጡ አብረው ይጫወታሉ። በየቦታው የተኩስ ጩኸት እሩምታ ይሰማል። አንዳንድ ሽማግሌና አሮጊቶች ይሄ የጩኸት ፈንጠዝያ የጦርነት ትዝታ ስለሚያመጣባቸው ነው መሰለኝ ቤታቸውን ዘግተው በዓሉን በቴሌቪዥን ይከታተላሉ።

በሮላንድ የታክሲ ድርጅት ውስጥ የሚሠሩት የሴንተራል ፋንክ ተናጋሪዎች ሦስት ሲሆኑ ስልክ ተቀባዮች ደግሞ አራት በአጠቃላይ ሰባት ሰዎች ቦታ ቦታቸውን ይዘው ተቀምጠው አገልግሎት መስጠት ጀምረዋል። የብሬመን ከተማ በ15 ክፍተኛ ቀበሌ የተከፋፈለች ስለሆነ እንደ አዘቦቱ ቀን በአንድ ካናል በአንድ ፋንክ ተናጋሪ ሁሉን ማዳረስ ባለመቻሉ በሦስት ካናሎች መጠቀም ግዴታ ሆኗል።

የድርጅቱ ባለቤት አቶ ሀሮልድ ይህ ታላቅ በዓል ለሳቸው የመደሰቻ ሳይሆን የልፋት የሥራ ቁጥጥር የሚያደርጉበት የድካም ምሽት ነው። ፋንክ ባለው የግል መኪናቸው ከቦታ ቦታ እየዞሩ የድርጅቱ ደንበኞች በሥርዓት መገልገል ይቆጣጠራሉ። የሴንትራልም ሠራተኞች በቅልጥፍና መናገር በሦስቱም ካናሎች እየለዋወጡ ያዳምጣሉ። ልጆቻቸውም ቢሆን ድንገት ለሚበላሹ መኪናዎች አስቸኳይ ጥገና ለማድረግ ትልቁ ጋራዥ ተከፍቶ በተጠንቀቅ ቆመዋል።

ሮዚና ጆኒ አንድ ላይ ሆነው እራት በልተው ወፍራም ቡና ጠጥተው በንቃት ሥራቸውን ጀምረዋል። ፋጡማም በሌላ ድርጅት ውስጥ ሆና መኪናዋን ከወዲያ ወዲህ እያቅለበለበች በሮዚ ለመታየት ትጥራለች። ክላውዝ ወደሌላ ከተማ ስለሄደ በእለቱ ሥራ አልገባም።

ምሽቱ ነፋሻማ ሆኖ ይበርዳል። የዳመነው ሰማይ እንደተፈራው ሆኖ ዝናብና በረዶ አልጣለም። ይህም ለታክሲዎች ሥራ ቅልጥፍና ስለሚያመች የለሊት ሹፌሮች በሁኔታው ተደስተዋል። እስካሁን ግን አጣዳፊ ሥራ አልገጠማቸውም።

የበዓሉ ዋዜማ ምሽት ተገባዶ ዘመን ሊለወጥ ጥቂት ደቂቃዎች ቀሩት። ሕዝቡ አደባባዩን ሞላው። የተጠመዱ እሮኬትና ርችቶች ልክ

ከሌሊቱ አጋማሽ 24 ወይም ዜሮ ሰዓት ላይ ተለኩሰው ብሬመን የጦር ሜዳ መሰለች። ሰማዩ በልዩ ልዩ ቀለማት አሸብርቆ የነጋ መሰለ። የቤተክርስቲያን ደወሎች በየቦታው ተደውለው ድምጻቸውን አስተጋቡ። ሕዝቡ ያመጣውን መጠጥ እየከፈተ ተጎነጫጨ። ለአዲሱ በዓል መልካም ምኞቱን እርስ በእርሱ እየገለጠ ተቃቅፎ ተሳሳመ። ለበዓሉ የተዘጋጀ ሙዚቃ ተከፍቶ ሕዝቡን አስጨፈረው። የባሩዱ ጭኽት የርችቱ ብርሃን ከተማዋን አደበላልቆ ሌሊቱ የነጋ መሰለ።

ለምሽቱ ዝግጅት ብሬመን ውስጥ በየቦታው ትልልቅ የሙዚቃ አዳራሽ ተዘጋጅተዋል። ሕዝቡ ከቦታ ቦታ በታክሲ እየተዘዋወረ ከመዝናናት አልፎ ፈነጠዘ። የሰከረውም ወድቆ ተንከባለለ።

በዚህ ወቅት የታክሲዎች ሥራ እጅግ አጣዳፊ ሆነ። ያን አድርሶ ይሄን ወስዶ ከቦታ ቦታ መቅለብለብ ሩጫ ጥድፊያ አንዱ ባንዱ ተደራርቦ ታክሲውን የሙጥኝ ይላል። ከስንቱ ተሟግቶ አንዱን ጭኖ ሌላውን ትቶ ማስተናገዱ ይከብዳል። ዘሎ መኪና ውስጥ ከሚገባም ሰካራም አምልጦ በሕዝብ ትርምስ መሐል ተሽሎክልኮ መንዳት የነቃ አዕምሮና ትእግሥት ይጠይቃል። ለሹፌሩ ዘሎ የሚገባ ተሳፋሪ ቢጠቅመውም ለድርጅቱ ሲል የግድ በፉንክ የሚሰጡትን በሮች ተቀብሎ በቅድሚያ ማገልገል ግዴታው ነውና በጥንቃቄና በፍጥነት በመዟዟር የታክሲ የቀድሞ ደንበኞችን ጥሪ ያሟላል።

የበዓሉ ምሽት በዚሁ ሁኔታ ቀጥሎ ሕዝቡ በየቦታው በታክሲና በአቶቢስ እየተዘዋወረ ደስታውን በመግለጥ እስከ ንጋቱ ድረስ አከበረ።

የታክሲ ሹፌሮችም በዚሁ ድብልቅልቅ በዓል ብዙ ገንዘብ ቢያካብቱም አልፎ አልፎ አደጋም የደረሰባቸው ነበሩ። ሮዚና ጆኒ ፋጡማና ሙራት ይድከማቸው እንጂ በሰላም ሥራቸውን ጨርሰዋል።

በአጠቃላይ በጀርመን ሀገር ውስጥ ለዚህ ታላቅ በዓል ለሚተኮሱ ርችትና ባሩዶች በየዓመቱ ከ16 ሚሊዮን ዶች ማርክ ወጪ ይደረጋል። ገንዘቡ ብቻ ሳይሆን እንዲህ ያለው መጥፎ ልማድ የአካባቢን ማቆሸሽ ብክላን ያስከትላል ተብሎ ቢታመንም ሕዝቡ ይህን ባህል የሙጥኝ ብሎ አጥብቆ ይዟል።

አውሮፓ ዘመን ተለውጦ መስከረም ጠባ። ሰማዩ ግን ካለፈው ዓመት የተለዩ መልክ አላሳየም። ያው የጨፈገገ ክረምት ነው። እንደ ኢትዮጵያ ፀሐይ ተፈንጥቃ አልወጣችም። አደይ አበባ በየቦታ በቅለውና አብበው አልታዩም።





# ክፍል አሥራ ስድስት

አካባቢው እንደሰፊ ባህር ተንጣሎ ሜዳው በኑግ የታሰሰ ምጣድ መስሎ ያብለጨልጫል። አየሩ ሞቃት ወቅቱ ብራማ ነበር። ብዙ አይሮፕላኖች እንደ ታክሲ ተደርድረው ይታያሉ። አንዱ አይሮፕላን ሞተሩን አግሎ ተንደርድሮ ወደላይ ሲከንፍ ሌላው ሞተሩን እያበረደ አፍንጫውን ወደታች ደፍቶ ጐማዎቹን ዘርግቶ ይመጣል።

ከማዶ ለሕዝብ መስተናገጃ በተሠራው ሠገነት ላይ ሆነው ብዙ ሰዎች እጃቸውን ያርገበግባሉ። የሚመጣውን እንግዳ ናፍቀው ለማየት ጓጉተው ይጨነቃሉ። እቅፍ አበባ ይዘው ዘመድና ወዳጃቸውን ይጠብቃሉ። አንዳንዶቹ የፍቅራቸው ብዛት የናፍቆታቸው ጋት ሞልቶ ይርበተበታሉ።

ተለይቶ የሚሄድ ወዳጅ ተሸኝቶ ሲከንፍ ተናፍቆ የሚጠበቅ ዘመድ መጥቶ ይደርሳል። ሁኔታው እንደ ልደትና ሞት ዓይነት የኅብረተሰቡ የፍቅር መግለጫ ባህላዊ ልማድ ሆኖ ቆይቷል።

ቦታው አሜሪካ ካሊፎርኒያ ኬኔዲ አየር ጣቢያ ነው። ሮዚ አሜሪካ ስትገባ የመጀመሪያ ጊዜዋ ነበር። ሰውነቷ በጉዞ አሰልችነት ስለደከመ ከአውሮፕላኑ ፈጥና ለመውረድ አልቻለችም። ቀስ ብላ የመውረጃውን በረንዳ በእጆቿ ጨብጣ እየተራመደች እመሬቱ መሐል ላይ ደረሰች። ወቅቱ ሞቃት ቢሆንም በአካባቢው ቀዝቃዛ አየር ስለሚነፍስ የሰውነቷን ሙቀት አራገበላት። አዲስ ሀገር የተለየ አካባቢና ሁኔታ እስከሚለመድ ለጊዜው ያደናግራልና ትንሽ ግር ብሏት ሰውነቷ ፈራ።

ሮዚ የፓስፖርቱ ቁጥጥር አልቆ በናፍቆት ከሚጠብቋት ታላቅ እህቷ ከባለቤቷና ከሌላም ሰዎች ጋር ተደባልቃ የናፍቆትና የፍቅር ሰላምታ ተለዋወጠች። በቅርቡ የተወለደችውንም የእህቷን ልጅ ሕፃን ታቅፋ አገላብጣ ሳመቻት። ለእንግድነቷ ክብር የቀረበላትን ስጦታና አበባዎች ተቀብላ በተዘጋጀላት የሾፍሬሌት ሽንጣም የአሜሪካን መኪና ውስጥ ገብታ ሙሽራ መስላ ተጓዘች።